# ደህንነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ምህረት

ጃኪይ ኦስክ

## ከመፅሃፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ፣ መፅሃፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ፣እንደዚሁም ከመፅሃፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ እና ካልዕ መጻሕፍት የተወሰዱ ታሪኮች

ትምህርት 1፡ ዳዊት እና ሳሙኤል - እግዚአብሄር ልብን ያያል

ትምህርት 2፡ ዳዊት እና ፍልስጥኤማዊው - ሰልፉ የእግዚአብሄር ነው

ትምህርት 3፡ ዳዊት፣አቢጊያ እና ሳኦል - እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ነበር

ትምህርት 4፡ ዳዊት እና እስራኤል - እግዚአብሄር የእስራኤል አምላክ ነው

ትምህርት 5፡ ሰለሞን እና ነገስታቶች - እስራኤል በእግዚአብሄር ላይ ኃጢአትን አደረገች

ትምህርት 6፡ ኤልያስ እና ኤልሳዕ - እግዚአብሄር እርሱ አምላክ ስለሆነ ተከተለው

**“………እንዳልበድልህ ቃልህን በልቤ ሰወርኩ…..”**

## *መቅድም*

*ቀሪውን የህይወታችሁን ዘመን መልክ የሚያስይዘውን አስደናቂ ጉዞ ጀምራችኋል፡፡ ጉዞአችሁ እጅግ አስገራሚ እና ልዩ ነው ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ያላችሁ ጉጉት እና ፍላጎት በአግባቡ የመረዳት ወይንም ያለመረዳት ነገራችሁን ሁኔታ ይወስነዋል፡፡ ይህን ጥናት ከልባችሁ ጊዜን በመስጠት ማጥናታችሁ እግዚአብሄር በጥናቱ ውስጥ የሚናገራችሁን በመስማት የተለወጠ ህይወት እንዲኖራችሁ ይረዳችኋል፡፡*

*ይህንን ጥናት በአግባቡ ለማጥናት የሚከተሉትን የመርጃ መሳሪያዎችን መያዝ ይኖርባችኋል፡፡*

1. *"ደህንነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ምህረት"* የሚለው የጥናት ክፍል ጥራዝ፡፡
2. አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ ይህን መጽሐፍ ገና ያልገዛችሁ ከሆነ ስትገዙ የሚከተሉትን ነገሮች የያዘ ቢሆን ይመረጣል፡፡
    - ሀ. ማጣቀሻ ጥቅሶችን በእያንዳንዱ ገፅ መሀል የያዘ
    - ለ. በጀርባው ላይ የቃላት ማውጫ ያለው እንዲሁም
    - ሐ. ጥቂት ጠቃሚ የሆኑ ካርታዎችን በጀርባው ላይ የያዘ ቢሆን ይመረጣል፡፡
3. እስኪርብቶ ወይንም እርሳስ
4. ዋና ዋና የሆኑ ጥቅሶችን ይዛችሁ የምታጠኑበት 3 በ 5 ወይንም 4 በ 6 የሆነ ካርድ፡፡

*መጽሐፍ ቅዱሳችሁ በተራ ቁጥር ሁለት ላይ የተዘረዘሩትን ሶስት ነገሮችን የያዘ ከሆነ ጥናታችሁን በአግባቡ እና በቀላሉ ማጥናት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠኑ ይህ ጥናት የመጀመሪያችሁ ከሆነ "መጽሐፍን ቅዱስ መቃኘት" የሚለውን የጥናት ክፍል በማጥናት ብትጀምሩ መልካም ነው፡፡ ይህ የጥናት ክፍል መጽሐፍ ቅዱስን በአግባቡ ማጥናት የምትችሉበትን መንገድ ያሳያችኋል ፡፡*

*ልታጠኑት የገዛችሁት የራሳችሁ መጽሐፍ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ለማድረግ እንዳይከብዳችሁ፡፡ በላዩ ላይ ማስታወሻዎችን በመያዝ ፣የነኳችሁ እና አዲስ ነገር ያገኛችሁባቸውን ክፍሎች ማስመር ፣ማክበብ ምልክት አድርጉባቸው፡፡ የማስታወሻ*

ደብተራችሁን፣ ሞባይላችሁን ወይንም ሌሎችን መንገዶች በመጠቀም የሚያጋጥሟችሁን ጥያቄዎች ፣አዳዲስ ሃሳቦች በእነርሱ ላይ መያዝ ትችላላችሁ፡፡

እነዚህ የጥናት ክፍሎች በቀላሉ መረዳት እንድትችሉ ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ይህን ጥናት ፕሮግራም አውጥታችሁ በአግባቡ ያለምንም ችግር ማጥናት ትችላላችሁ፡፡ ጥናቱንም ስታካሂዱ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች ፣አዳዲስ ሃሳቦች ፣አዳዲስ መረጃዎችን ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡ ይህን ጥናት ስታጠኑ ጓደኞቻችሁን መጋበዝ አትርሱ፡፡

ጥናታችሁ አስደሳች ይሆንላችሁ ዘንድ እንደዚሁም እግዚአብሄር በቃሉ ሲናገራችሁ የምትሰሙበትን ልብ እንዲሰጣችሁ እንመኛለን፡፡ በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ እግዚአብሄር በልጁ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የገለጠውን ፍቅር የበለጠ የሚያረጋግጡላችሁን እውነቶች መማር ይሁንላችሁ፡፡

# ትምህርት አንድ

# እግዚአብሄር ልብን ያያል

## መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 16- ዳዊትና ሳሙኤል

---

### የትምህርት 1 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 1፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 16

- የሳሙኤል አዲሱ የቤት ስራ
- የእግዚአብሄር መስፈርት
- የንጉስ ወግ
- የሳኦል አለመታዘዝ
- በእግዚአብሄር ፈቃድ መደሰት

## *መግቢያ*

*"መንገዳችን የሆነው የእግዚአብሄር ፈቃድ"* በሚለው በቀደመው ክፍል እስራኤላውያን በዙሪያቸው እንደሚገኙት ህዝቦች ንጉስ እንዲሾምላቸው ጥያቄ እንዳቀረቡ ተመልክተናል፡፡ ልዩ የእግዚአብሄር ህዝቦች እንደዚሁም በእግዚአብሄር የአባትንነት ስልጣን እና አገዛዝ ስር ልጆች በመሆን በደህንነት ይኖሩበት የነበረውን ስርአት ንቀው እንደሌሎቸ ህዝቦች በምድራዊ በንጉስ መተዳደር ፈለጉ፡፡ ንጉስ መፈለጋችው የእግዚአብሄርን አገዛዝ መናቃቸውን እና እግዚአብሄርን አለመፈለጋችውን ያሳያል፡፡ እግዚአብሄርም የንጉስን ወግ ከነገራቸው በኋላ የጠየቁትን ንጉስ ሰጣቸው፡፡ ለነቢዩ ሳሙኤልም ሳኦልን ንጉስ አድርጎ እንዲቀባው እግዚአብሄር አዘዘው፡፡ እግዚአብሄርም መንፈሱን ሰጠው እንደዚህ በሚልም ቃል አፅናናው *"እግዚአብሄር ካንተ ጋር ስለሆነ በእጅህ የምታገኘውን ሁሉ አድርግ፡፡"*

በንግስናው ላይ ብዙም ሳይቆይ ሳኦል ባለመታዘዝ እግዚአብሄርን እንዳሳዘነ ባለፈው ክፍል ተመልክተናል፡፡ ሳኦል የእግዚአብሄርን ትእዛዝ በመናቁ እግዚአብሄርም ሳኦልን ናቀው ንግስናውም ተሻረ፤ የእግዚአብሄር መንፈስም ተለየው፡፡

በዚህ ትምህርት እግዚአብሄር እንደ ልቡ የሆነለት ሰው ሲፈልግ እንመለከታለን፡፡ ሳኦልን የሚተካው ንጉስ ማን እንደሆነ እንደዚሁም እግዚአብሄር ንጉስ አድርጎ ሊቀባው የፈለገው ሰው ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታ ወይንም በስፈርት ተመልከቱ፡፡ እግዚአብሄር ዳዊትን እንዴት እንደተጠቀመበት እና የሳኦልን ሽልማት እንዴት እንዳሸነፈ ተመልከቱ፡፡ ሳኦልን ንጉስ አድርጎ በመሾሙ ምክንያት እግዚአብሄር እንዴት እንደተፀፀተም ልብ በሉ፡፡

<u>**ከፍል1**</u>

***መግቢያ:*** ሳሙኤል እና ንጉስ ሳኦል ተለያይተዋል (*መፅሃፈ ነገስት ቀዳማዊ ምእራፍ* 15)። ሳሙኤል ወደ ራማ ሔደ ሳኦል ደግሞ ወደትውልድ ሃገሩ ጊብአ ሔደ ። ለሳኦል አለቀሰለት ሳሙኤልም እስከሞተበት ጊዜ ሳኦልን ለማየት አልተመለሰም። እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ ንጉስ አድርጎ ስለሾመው ስለ ሳኦል ተጸጸተ።

ሁላችንም ልናውቀው የሚገባን ነገር ሳኦል ንግስናውን እንዲያጣ ምክንያቱ እግዚአብሄር አለመሆኑን ነው። *መፅሃፈ* ሳሙኤል ቀዳማዊ 15፡26 ሳኦል የእግዚአብሄርን ቃል እንዳልታዘዘ ይነግረናል። እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ሊፈጥር የነበረውን ግንኙነት እንደሚገባ አልተቀበለውም። ስለዚህ ሳኦል እግዚአብሄርን ስለናቀ እግዚአብሄርም እርሱን ናቀው።

**የቤት ስራ** ፡ታሪኩ ቀጥሏል ። ሳሙኤል ቀዳማዊ 16፡1-13 አንብቡ።

- እግዚአብሄር ሳሙኤልን ወዴት ላከው?
  እግዚአብሄር ሳሙኤልን ለምን ነበር የላከው?
  እግዚአብሄር ሳሙኤልን ምን ነበር ያደረገው?

***መልመጃ:***

1. በቁጥር 1 ላይ እግዚአብሄር ሳሙኤልን ምን ጠየቀው?______________________

   ____________________________________________________________

2. እግዚአብሄር አዲስ የቤት ስራ ለሳሙኤል ሰጥቶታል። ለእስራኤል አዲስ ንጉስ መርጧል። ይህንን ንጉስ ሳሙኤልም እንዲቀባለት ትእዛዝ ሰጥቶታል። ቁጥር 1 መካከል ላይ እግዚአብሄር ሳሙኤልን ምን አዘዘው?_________________________

   ____________________________________________________________

**ትምህርት :** ”በቀንድህ ዘይትህን ሞልተህ ሂድ” የሚለው ትእዛዝ ንጉስ ሊቀባ እንዳለ ይጠቁመናል:: በሳሙኤል ቀዳማዊ 10:1 ሳሙኤል የእግዚአብሄር ርስት በሆነው ህዝብ ላይ ንጉስ እንዲሆን ሳኦልን ቀባው:: በሳኦል ላይ የፈሰሰውን ዘይት ይህ ሰው ልዩ ለሆነ አገልግሎት ተለይቷል ወይንም ተቀድሷል የሚል መልእክት ነው ያለው:: በምዕራፍ 10 ላይ አዲሱ ሰው ሳኦል ቅዱስ ለሆነው ለእግዚአብሄር ስራ ተለይቷል::

**መልመጃ:**

1. በቁጥር 1 ላይ እግዚአብሄር ሳሙኤልን ወዴት ላከው? ______________________
   ______________________________________________________________
2. እሴይን እናውቀዋለን:: መጽሐፈ ሩት 4:21 እና 22 እንደገና አንብቡት:: የዘር ሃረጉን አመጣጥም ተመልከቱ::
   ሀ. ሩት እና ቦኤዝ የ______________________________ቤተሰቦች ናቸው::
   ለ. ኑኃሚን የ_________________________________________አያት ነች::
   ሐ. የእሴይ ልጅ ማን ነው?______________________________________
3. በቁጥር 1 ሳሙኤል ወደ ቤተልሔም የተላከው ለምን ነበር? _________________
4. በቁጥር 2 ላይ የሳሙኤል ፍርሃት ምን ነበር? ___________________________
5. እግዚአብሄር ሳሙኤልን ምን እንዲያደርግ አዘዘው፣ ምንስ አለው?

   ሀ.________________________________________________________

   ለ.________________________________________________________

6. በቁጥር 3 ማለቂያ ላይ እግዚአብሄር ለሳሙኤል የሰጠው ለየት ያለው ትእዛዝ ምን ነበር?_________________________________________________________
   _____________________________________________________________
7. በቁጥር 4 ላይ እግዚአብሄር እንደአዘዘው ወደ ቤተልሔም ከተማ በመሄድ የከተማይቱን ሽማግሌዎች አገኛቸው:: ያለጥርጥር እነዚህ ሽማግሌዎች እንደ ከተማይቱ ጠባቂዎች ጭምር ሳያገለግሉ አይቀሩም ምክንያቱም ሳሙኤል ሲደርስ ያገኛቸው በከተማይቱ መግቢያ ላይ ነበር:: በቁጥር 4 ላይ በፍርሃት ሆነው ሳሙኤልን ምን ብለው ጠየቁት?____________________________________
8. በቁጥር 5 ላይ ሳሙኤል ለምን እንደመጣ ነበር የነገራቸው?__________________

9. ለሽማግሌዎቹ የሰጣቸው መመሪያ ምን ነበር ወዴትስ ጋበዛቸው?_______________

___________________________________________________________________

10. ከሽማግሌዎቹ ጋር አብሮ የጋበዛቸው እነማንን ነው? _________________________

**<u>ክፍል 2</u>**

**የገለፃ ጥያቄ፡** እግዚአብሄር ንጉስ እንዲቀባለት ሳሙኤልን ወደ ቤተልሔም ከተማ ላከው፡፡ እናንተን እንደዚን አይነቱን ምርጫ እንድታደርጉ ዕድሉን ያገኛችሁት እናንተ ብትሆኑ ይህንን ንጉስ ለመምረጥ ምን አይነት መስፈርት ታወጡ ነበር? ይህን ንጉስ ያልጠበቃችሁትን ነገር ሊያደርግ እንደሚችል አትዘንጉ፡፡

ሀ. _______________________________________________________________

ለ.________________________________________________________________

ሐ.________________________________________________________________

**መልመጃ፡** እስቲ እግዚአብሄር ማንን እንደመረጠ እንመልከት፡

1. ሳሙኤል እግዚአብሄር የመረጠውን ሰው እየፈለገ ነው፡፡ በቁጥር 6 ላይ ሳሙኤል ማንን ተመለከተ? _____________________________________________
2. ሳሙኤል ስለተመለከተው ሰው የነበረው አመለካከት ምን ነበር?_________________
3. በቁጥር 7 ላይ ሳሙኤል እንደ መስፈርት እንዳይጠቀምበት የነገረው ነገር ምንድነው? ______________________________________________________
4. ስለ ሳኦል መልክ እና ቁመና የምናውቀው ምንድነው ? 1ሳሙኤል 9፡2 ተመልከቱ፡፡_________________________________________________

እግዚአብሄር ኤሊያብን አልመረጠውም፡፡ የሚቀጥለው ቃል የእግዚአብሄር ሃሳብ ምን እንደሆነ መረዳትን ይሰጠናል፡፡ ይህንን ሁኔታ የሚያስታውሰንን ቁጥር 7 ላይ ያለውን ቃል ጻፉ፡_________________________________________________________

5. በፊቱ በየተራ ለቀረቡት የእሴይ ልጆች የሳሙኤል ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 8-10)?

___________________________________________________________________

6. በመጨረሻም በቁጥር 11 ላይ እሴይን ሳሙኤል የጠየቀው ምን ነበር? ________

________________________________________________

7. የእሴይ ምላሽ ምን ነበር?______________________________

8. በቁጥር 11 ላይ ሳሙኤል የሰጠው መመሪያ ምን ነበር? ______________

9. በግ ይጠብቅ የነበረው ትንሹ ልጅ መጣ፡፡ ይህ ሁኔታ ቁጥር 12 ላይ የተገለፀው እንዴት ነበር? ______________________________

10. እግዚአብሄር ሳሙኤልን ያዘዘው ምን ነበር?______________________

11. ሳሙኤል ዳዊትን በወንድሞቹ ፊት ቀባው፡፡ በቁጥር 13 ላይ ስለዳዊት የተነገረን ምን ነበር? ______________________________

    ይህ ታሪክ ሁላችንም የምናውቀው ታሪክ ነው፡፡ በመፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 11፡6 ላይ ስለ ሳኦል የተነገረን ምንድነው?

    ______________________________

12. በቁጥር 13 ላይ ሳሙኤልም የተሰጠውን ስራ ከሰራ በኂላ ከቤተልሔም ሔደ

________________________________________________

________________________________________________

**የምናሰላስለው፡** ሰዎችን በውስጣዊ ሳይሆነ በውጪያዊ ማንነታቸው መዝናችሁ ታውቃላችሁ? ቁጥር 7 በማስታወሻ ካርዳችሁ ላይ በመፃፍ እንድታሰላስሉት የቤት ስራ ይሁንላችሁ፡፡ እግዚአብሄር ለሳሙኤል ቀጥተኛ ምክር ነው የሰጠው "ሰውን በውጪያዊ ነገር አትመዝን........ሰው እንደሚያይ እግዚአብሄር አያይም "ሰው ውጪያዊ ማንነት በማየት ይሳሳታል እግዚአብሄር ግን የውስጥን ዘልቆ ልብን ያያል፡፡ ልብ የሰውን ልክ፣ባህሪይ፣ማንነት የሚገልፅ ነገር ነው፡፡

1. እግዚብአብሄር ለሳሙኤል ምን ነገረው?______________________
2. ሌሎች ልባችንን እንዲያውቁት ልናሳያቸው የምንችለው እንዴት ነው?__________

   ________________________________________________

3. ልብ ስለ ሰው ማንነት ሊነግረን የሚችለው እንዴት ነው?______________

   ________________________________________________

4. ልቤን ለሰዎች ስገልፅላቸው ሰዎች ሊረዱኝ የሚችሉት እንዴት ነው?__________

   ________________________________________________

**ልንገነዘበው የሚገባንነ ነገር፡** እስከዚህ ነጥብ ድረስ ሳኦልና ዳዊት የሚመሳሰል ነገር ነበራቸው።ሁለቱም የማይረቡ እና የማይጠቅሙ ሰዎች ተደርገው ተቆጥረዋል።

1. በመፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 9፡21 ላይ ስለ ሳኦል ምን እንማራለን?
____________________________________________
____________________________________________
2. በሳሙኤል ቀዳማዊ 16፡11 ስለዳዊት የምንማራቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?
   ሀ. ____________________________________________
   ለ. ____________________________________________
3. በመጨረሻም በሳሙኤል ቀዳማዊ 9፡2 እና 16፡12 ላይ ስለእነዚህ ሁለት ሰዎች የተነገረን ምንድነው?____________________________________________

**ክፍል 3**

**መግቢያ፡** በሳኦልና በዳዊት መካከል ያለውን መመሳሰል ተመልክተን ጨርሰናል። የሚቀጥለው ቁጥር በሁለቱ መካከል ልዩነት ስለፈጠረው ነገር ይነግረናል ። ሳሙኤል ቀዳማዊ 15፡23 እና 26 ላይ በእግዚአብሄር ላይ በማመፁ እንደዚሁም ባለ መታዘዙ ምክንያት እግዚአብሄር ንጉስ እንዳይሆን ናቀው ስለዚህም በእስራኤል ላይ ንጉስ እንዳይሆን ተሻረ። መፃፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 16፡14-23 የሳኦል ድርጊት ስላስከተለው ነገር ይነግረናል።

**የቤት ስራ፡**ሳሙኤል ቀዳማዊ 16፡14-23

- በሳኦል ህይወት ውስጥ የእግዚአብሄርን መንፈስ በምን ተተካ?
- ሳኦልን እንዲያገለግል የተጠራው ማነው?
- ሳኦልን እንዲያገለግል የተጠራው ሰው ምን እንዲያደርግ ነበር የተጠራው?

**መልመጃ፡**

1. በቁጥር 14 መሰረት ከሳኦል የተለየው ማን ነበር? ____________________
2. የእግዚአብሄር መንፈስ ሳኦልን አስታጥቆት ነበር (ሳሙኤል ቀዳማዊ 11፡6)። ነገር ግን እርሱ ሲለየው ያገኘው ክፉ መንፈስ አጥፊ እና በህይወቱ ላይም ያሳደረው ተፅእኖ የተለየ ነበር።በቁጥር 14 ላይ እንደተነገረን ይህ ክፉ መንፈስ ____________________ነበር ?

3. ችግሩን የተረዱት የሳኦል አገልጋዮች ለሚያሰቃየው መንፈስ ያቀረቡት መፍትሄ ምን ነበር (ቁጥር 15-16)?________________________________________________

________________________________________________

4. በቁጥር 17 ላይ ሳኦል የአገልጋዮቹን ኃሳብ በመቀብል ጥሩ አድርጎ በገና የሚደረድር ሰው ፈልገው እንዲያመጡለት ተስማማ። ከአገልጋዮቹ መካከል አንዱ የእሴይን ልጅ ዳዊትን ያውቀው ነበር ። ይህ ሰው ስለ ዳዊት ተናገረ (ቁጥር 18)?

   ሀ. ________________________________________________

   ለ.______________________፣______________________

   ሐ.______________________፣______________________

   መ.________________________________________________

5. በቁጥር 19 ላይ ሳኦል ያደረገው ነገር ምን ነበር? ______________________

6. በቁጥር 20 ላይ እሴይ ምን አይነት ምላሽ ሰጠ? ______________________

   የእሴይን ደግነት እና ለንጉሱ ያለውን አክብሮት ልብ በሉ።

7. በቁጥር 21 ላይ ዳዊት ንጉሱን ያገለግል የነበረው በምንድነው? ____________

   ________________________________________________

8. ስለ ሳኦልና ዳዊት ግንኙነት ምን እንማራለን?______________________

   ________________________________________________

9. ሳኦል የዳዊትን አባት እሴይን ምን ጠየቀው (ቁጥር 22)? ________________

10. ሳኦል አሁን ከእግዚአብሄር ዘንድ ለሚያሰቃየው ክፉ መንፈስ መፍትሔ አግኝቷል (ቁጥር 23) ዳዊት ______________ሳኦል__________ነበረ እናም ክፉው መንፈስ________።

**ትምህርት፡** የእግዚአብሄርን ቃል መታዘዛችን ለእግዚአብሄር ያስፈልገዋል። ምንም ያህል ስለ እግዚአብሄር ጥሩ ብናስብ እንኳን እግዚአብሄር በእኛ ሊደሰት የሚችለው ስንታዘዘው ብቻ ነው። ቃሉ ለእኛ የተሰጠ ስጦታ ነው። ክፉው ከሚያመጣብን ጥፋት እንድናመልጥ ዘንድ ምሪት እና ትክክለኛ አቅጣጫን ይሰጠናል። በህይወት ዘመናችን ሁሉ ቃሉ መውጣት እና መግባታችንን ይቆጣጠራል ። ዘፀአት 20 ላይ ስለአስርቱ ትእዛዛት እናነባለን ፤ እነዚህ ትእዛዛት በህብረት እና በፍቅር በመኖር በዙሪያችን ላሉት ህዝቦች ለእርሱ ያለንን ፍቅር እንድንገልጥላቸው ያደርጉናል። ትእዛዛት ከእግዚአብሄር የፍቅር ልብ ወጥተው ለህዝቡ የተሰጡ በረከቶች ናቸው

ህዝቡ እስራኤል ግን እግዚአብሄርን ሊታዘዙ አልቻሉም፡፡ አለመታዘዛቸው እግዚአብሄር አምላካቸው እንዳይሆን መፈለጋቸውን ያሳያል፡፡

ሳኦልንም ስንመለከት በፈቃዱ አለመታዘዝ መርጧል አለመታዘዝ ደግሞ ውጤት አለው፡፡ በእርሱ ላይ ከመታመናችን በላይ እግዚአብሄርን ሊያስደስተው የሚችል ምንም ነገር የለም መታመናችንንም በመታዘዛችን እንገልፅለታለን፡፡ መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15፡22 መታዘዝ ከ___________ይበልጣል ቁጥር 23 ላይ አለመታዘዝ ደግሞ አመፅ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ለእግዚአብሄር ድምፅ እና ቃል አለመታዘዝ እግዚአብሄር እንዲሁም ስልጣኑን መቃወም ነው፡፡

**<u>ክፍል 4</u>**

**ገለፃ፡**

1. የእግዚአብሄርን ቃል እንዳልጠብቅ እና እንዳልታዘዝ የሚያደርጉኝ ሁኔታዎች ምንድናቸው ጊዚያቶቹስ የትኞቹ ናቸው?___________________________________
2. እግዚአብሄር በቃሉ ሲናገረኝ እኔም ስሰማው___________________________________
3. እግዚአብሄርን በህይወታችን ላይ ስልጣን ያለው እርሱ ብቻ እንደሆነ በማመን ህይወታችንን ሙሉ በመሉ ለእርሱ ማስገዛት በጣም ይከብደናል፡፡ በዘፍጥረት 3 ላይ አዳምና ሄዋን በመታዘዝ ከሚገኘው ህይወትና በረከት ይልቅ የተሻለ መንገድ ያገኙ መስሏቸው ባለመታዘዝ በደሉ፡፡ አለመታዘዝ እና አመፅ አስቸጋሪ ነገሮች ናቸው፡፡ በመታዘዝ ህይወት መኖር እጅግ ከባድ ይሆንብናል፡፡ የሳኦል አለመታዘዝ ንግስናውን አሳጥቶታል፡፡እናንተስ ባለመታዘዝ እግዚአብሄርን ባለማክበር የተጓዛችሁበት መንገድ አለ? ያደረጋችሁት ወይንም የተናገራችሁትስ ነገር አለ? የተናገራችሁት ወይንም ያደረጋችሁት ነገር ምንድነው?

**ማሰላለሰል፡** መዝሙር 1 ይናገረናል፡፡ የተለያዩ ጥቅሶችን የምትይዙበትን ካርድ አውጥታችሁ ይህንን ጥቅስ ተመልከቱት፡፡ የማስታወሻ ካርድ ላይ ስትፅፉ ይህ የመጀመሪያችሁ ከሆነ ደግሞ በመዝሙር 1 ላይ ያሉትን ስድስት ቁጥሮች በካርዳችሁ ላይ ፅፋችሁ አጥኗቸው፡፡ *"በእግዚአብሄር ህግ ደስ ይለዋል "* የሚለውን ቁጥር ሁለት ላይ ያለውን ቃል የተለየ ትኩረት ሰጥታችሁ ተመልከቱ፡፡ እግዚአብሄር ቃሉን ስንታዘዝ ይደሰታል፡፡ ለምንድነው እግዚአብሄር ትእዛዛቱ ሲጠበቁ ይህን ያክል የሚደሰተው? ___________________________________

መዝሙረ ዳዊት 1፡2 አካሄዱን ከእግዚአብሄር ጋር ያደርገ ሰው የእግዚአብሄርን ቃል በመታዘዝ እና በማሰላሰል ይደሰታል፡፡ ይህ ሰው በክፉዎች፣በኃጢአተኞች፣በተሳዳቢዎች ከእግዚአብሄር ጋር ህብረት በሌላቸው ሰዎች ምክር አይሄድም ከእነርሱም ጋር ህብረት በማድረግ አይደሰትም፡፡ እግዚአብሄርን ስንታዘዘው በእኛ ደስ ይሰኛል፡፡

**ፀሎት፡** ምህረትህ የበዛ አባት ሆይ ባለመታዘዝ የተጓዝኩበትን የአመፅ መንገድ በፊትህ ለመናዘዝ እንኳን ፈራሁ፡፡ ለሰራሁት በደል ሁሉ ተጠያቂ ነኝ፡፡ ማድረግ የምፈልገውን እንዲሁም የማልፈልገውን ነገር የምወስነው እራሴው ነኝ፤ ፈቃዴን ለአንተ አላስገዛሁም፡፡ አሁን ግን ቃልህን በመታዘዝ ደስታን እንደማገኝ ተረድቻለሁ፡፡ እባክህን ታዛዥነት እና ለቃልህ ክብርን መስጠት የደስታዬ ምንጭ እንዲሆን እርዳኝ፡፡ ልቤም አንተን በማሰብ እና በመታዘዝ በደስታ ይሞላ ዘንድ እርዳኝ፡፡______________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

# ትምህርት ሁለት

# ሰልፉ የእግዚአብሄር ነው

## ሳሙኤል ቀዳማዊ 17- ዳዊት እና ፍልስጥኤማዊው

---

የትምህርት 2 ቅኘት

ቅኘት

መግቢያ

ትምህርት 2፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 17

- ግዙፉ ፍልስጥኤማዊ
- ጎልያድ የማስፈራሪያ ጩኸቱን ጮኸ
- የሰው ዕቃ ጦር
- የእግዚአብሄር ዕቃ ጦር
- ጌታ ያድናል
- ማጠቃለያ

## መግቢያ

ጥቂት ቆይቶ ሳኦል እና እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን እና ከጎልያድ ጋር ተፋጠጡ። እስራኤላውያን በጎልያድ ተግዳሮት እና የማስፈራሪያ ቃላት ፈሩ ተሸበሩም። ለመሆኑ እስራኤላውያን የሳቱት ምን ነበር? እስራኤላውያን ጠላቶቻቸው ከሆኑት ፍስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ውስጥ ያስገባቸው ምን ነበር? ትንሹ ዳዊት ግን ፍልስጥኤማዊው ጎልያድ የእግዚአብሄር ሰራዊት በሆነው እስራኤል ላይ ያደረሰውን ውርደት ተመልክቶ ዝም ሊል አልቻለም። ምንም እንኳን ይህ በጣም ታዋቂ የሆነ ታሪክ ቢሆንም ስታጠኑት ከዚህ በፊት ሰምታችሁ እንደማታውቁት አዲስ ታሪክ አድርጋችሁ አጥኑት። የዳዊት ዕቃ ጦር ምን ነበር? የተጠቀመበት የጦር መሳሪያስ ምን ነበር? ከዚያ ግዙፍ ፍልስጥኤማዊ ጋር የተደረገው ውጊያ ውጤትስ ምን ነበር?

ክፍል 1

**ትምህርት** ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆነውን በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 17 ውስጥ የሚገኘውን ታሪክ ቀጥለን ልናጠና ነው፡፡ ይህ ታሪክ የዳዊት እና የጎልያድ ታሪክ ነው፡፡ የታላቁ አውሮፓዊ የጥበብ ሰው ሚኪያኤል አንጄሎ ሀውልት እስኪሰራለት ድረስ የነካው የዳዊት እና የጎልያድ ታሪክ ሌሎችም ቬሮቺዮን የመሳሰሉ ታላላቅ የአውሮፓ የቅርጻ ቅርፅ ባለሙያዎችን ቀልብ የሳበ ድንቅ ታሪክ ነው፡፡

ነቢዩ ሳሙኤል ለእግዚአብሄር በመታዘዝ በወንድሞቹ ፊት በራሱ ላይ ዘይት አፈሰሰበት፡፡ ይህ ትንሽ ብላቴና አሁን ለእግዚአብሄር ታላቅ ስራ የተለየ የተቀባ የእስራኤል ንጉስ ነው፡፡ እግዚአብሄር መንፈሱን በኃይል አፍስሶለታል፡፡ ከተቀባም በኂላ በእስራኤል ላይ እስኪነግስ ረጅም የስልጠና ጊዜን ያሳለፈ ብላቴና ነው፡፡

በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 17፡1-3 የተለያዩ እንግዳ ስሞች ተጠቅሰዋል፡፡ በሜዲትራኒያን ባህር ዳርቻ የሚበኙት ስኮት፣ ዓዜቃ ፣ ኤፌስደሚም እና የዔላ ሸለቆ የተባሉት ስፍራዎች ተጠቅሰዋል፡፡ ብዙ ካርታዎች የጥንታዊ ከተሞችን ትክክለኛ ስፍራ አይጠቁሙም፡፡ አብዛኛዎቹ ካርታዎች በሜዲትራኒያንን የባህር ዳርቻ ጠባብ ሆነው በስተሰሜን በዮባ እንዲሁም በስተ ደቡብ ባለው ጋዛ መካከል ያለውን የፍልስጥኤምን ምድር ነው የሚያሳዩት፡፡ ይህ ምድር የእስራኤል ጠላት በሆኑት ፍልስጥኤማውያን የተያዘ ስፍራ ነው፡፡ በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ እና ካልዕ ውስጥ ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ደጋግመው ጦርነት ማድረጋቸውን እና የእስራኤል ቋሚ ጠላቶች መሆናቸው ነው የተገለፀው፡፡

በሳሙኤል ቀዳማዊ 17፡3 ውስጥ የፍልስጥኤምና የእስራኤል ሰራዊቶች በመካከላቸው ባለው ሸለቆ ተለያይተው በተቃራኒ አቅጣጫ ባሉ ተራራዎች ላይ ተፋጥጠው ተቀምጠው ነበር፡፡ ይህ መድረክ ነበር የዳዊት እና ጎልያድን ታሪክ የፈጠረው ፡፡ ይህንን ታሪክ ከዚህ ቀደም አንብባችሁት የማታውቁ ከሆነ ማስታወሻ ደብተራችሁን አዘጋጅታችሁ የምታገኟቸውን አዳዲስ

ትምህርቶች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው፡፡ ይህ አስደናቂ ታሪክ እግዚአብሄር በዚህ ታናሽ እረኛ ብላቴና ህዝቡን ለማዳን የሰራውን ተአምራት ታገኛላችሁ፡፡

**የቤት ስራ ፡**

1. ካነበባችሁት ክፍል የምታስታውሷቸውን ታሪኮች፣እውነታዎች፣እንደዚሁም ግለሰቦችን ማጠቃለያ ፃፉ፡፡. ____________________

   ____________________
2. ሳሙኤል ቀዳማዊ 17 በማንበብ ጎሊያደን የሚገልፁ ቃላትን፣ሃረጎችን ፣እንዲሁም ድርጊቶችን በማስታወሻችሁ ላይ ፃፉ፡፡ እንደዚሁም በተጨማሪ ስለዳዊት ያገኛችሁትን አዲስ ነገር እንደዚሁ በማስተወሻችሁ ላይ ፃፉ፡፡

**መልመጃ:**

1. ከቁጥር 4-7 ባለው ክፍል ላይ ጎልያድ ፍልስጥኤማውያን አለን የሚሉት ጀግናቸው ነው፡፡ ስለዚህ ፍልስጥኤማውያን መመኪያቸው ጎልያድ ነበር፡፡ እስቲ ጎልያድን አስቡት
   - ሀ. ቁመናው:____________________
   - ለ. ትጥቁ:____________________
   - ሐ. የጦር መሳሪያው:____________________
   - መ. ጥንካሬው:____________________
2. ከላይ ከተመለከታችሁት ሁኔታ አንፃር መደምደሚያችሁ ምን ሊሆን ይችላል ?____

   ____________________
3. በጎልያድ እይታ በቁር 8 መሰረት ጠላቶቹ እነማን ነበሩ?____________________

   ____________________
4. ጎልያድ የተሸነፈ ሰው ነው፡፡ በእስራኤላውያን ላይ ሲደነፋ የነበረው ምን ነበር?____________________
5. ጎልያድ እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ የመሆኑ ነገር የሚያስገርም ነው፡፡ ጎልያድ በቁጥር 8፣9፣እና 10 ላይ ያሉትን ተውላጠ ስሞች በሙሉ አስምሩባቸው፡፡
6. ጎልያድ ተግዳሮት ገጠመው (ቁጥር 10): ____________________

   ____________________

7. ጎልያድ ከማን ጋር እንደሚጋጠም ነው ያሰበው?______________________________

8. ጎልያድ አሁን የተረዳው ምንድነው?________________________________________

9. ቁጥር 11 እንብቡ። እስራኤላውያንን በዚህ ክፍል በምን አይነት ቃል ነው የተገለፁት?___________እና ________________

*ማስታወሻ፡ እስራኤላውያን የሳዩት ፍርሃት እግዚአብሄር ዳዊትን ባያስነሳላቸው ኖሮ እጅ መስጠታቸውን የሚያሳይ የሽንፈት ፍርሃት ነበር ያሳዩት የነበረው።*

***ገለፃ፡*** *ምን እየሆነ ነው? ምንስ እየተካሄደ ነው? ይህ ታሪክ የስነ ልቦና ጨዋታ ይመስላል። ከታላቁ ጀግናቸው ጋር ያሉት ፍልስጥኤማውያን እና ከንጉሳቸው ከሳኦል ጋር ያሉት እስራኤላውያን ሁለት ቡድን ሰርተው አሉ። ጎልያድ በየእለቱ ግዝፈቱን፣የጦር መሳሪያ ትጥቁን ፣መሳሪያውን፣ጡንቻውን እንደዚሁም ከፊት ለፊቱ የሚሄደውን ጋሻ ጃግሬውን እየያዘ በእስራኤላውያን ፊት ይንጎራደድ ነበር። በዚህ ጊዜ ያልፈራ ማነው?*______________________

1. *የጎልያድ ግዝፈቱ እና ትጥቁ ብቻ አይደለም ነገር ግን በእስራኤል ሰራዊት ላይ የማስፈራሪያ ዛቻውን በየማለዳው ያሰማቸው ነበር። "ነገሩ ቀላል ነው። እኔ ፍልስጥኤማውያንን ወክዬ እቀርባለሁ እናንተም ጀግና የምትሉትን የእናንተን ሰው ወክሉ ሁለታችን እንጋጠማለን እኔ ከተሸነፍኩ ፍልስጥኤማውያን ለእናንተ ይገዛሉ የእናንተ ሰው ከተሸነፈ ደግሞ እናንተ ለፍልስጥኤም አገልጋይ ትሆናላችሁ።" ይላቸው ነበር። እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባው የእስራኤል ጀግና ማን እንደሆነ ነው። ሳሙኤል (ቀዳማዊ*19፡2) *በሳሙኤል ቀዳማዊ* 17፡11 *ላይ ስለዚህ ሰው ምን እናነባለን?* ________________________________________
2. *የእስራኤል ንጉስ እንደፈራና እንደ ተሸበረ ተነግሮናል። ለጎልያድ በሰጠው ምላሽ ትደነቁ ይሆን? እንደዚህ አይነት ሁኔታ እናንተን ቢገጥማችሁ ንጉሳችሁ ወይንም መሪያችሁ ምን አይነት ምላሽ የሚሰጥ ይመስላችኋል? በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ምን አይነት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል? በንጉስና በህዝብ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ አስቡ።*____________________________

   ___________________________________________________________________
3. *በእስራኤል ሰራዊት መካከል እንደነበራችሁ አስቡ እና ያ ግዙፍ ሰው በሚያሰማው አስፈሪ ንግግር የሚሰማችሁን ስሜት ምን በሚል ቃል ትገልፁታላችሁ?*_______

**የትግበራ ጥያቄዎች፡**

1. በህይወቴ ውስጥ እንደ ጎልያድ የገዘፉብኝ ነገሮች ምንድናቸው?________________
2. ህይወቴ በእንደዚህ አይነት ግዙፍ ችግሮች በምትከበብበት ወይንም በምትቸገርበት ጊዜ ምን አይነት ስሜት ሊኖረኝ ይገባል?_______________________________

   ____________________________________________________________________
3. ለዚህ አይነት አስጨናቂ ሁኔታስ መስጠት ያለብኝ ምላሽ ምን ሊመስል ይገባል?_____

   ____________________________________________________________________
4. በህይወቴ ላይ ለገዘፈው ለዚህ ችግር በምሰጠው ምላሽ ላይ የሚንፀባረቀው ስሜቴ ምን ይመስላል?______________________________________________________

   ____________________________________________________________________

**ፀሎት፡** ጌታ ሆይ በህይወቴ አስፈሪ ሆነውብኝ ስለነበሩት ግዙፍ ችግሮች አሁን በፊትህ እናዘዛለሁ፡፡ የእኔ ነገር እንዳበቃ ፣ነገሬ እንደተቀረጠ፣እንደተሸነፍኩ ተሰምቶኝ ነበር፡፡ ግዙፎቹ ችግሮቼ የተለያየ መልክ እና ቅርፅ ነበራቸው፡፡ እኔም በምንም ሁኔታ ላሸንፋቸው እንደማልችል አምኜ ተሸንፌ እጅ ሰጥቼ ነበር፡፡ አንተ የእኔ መከታ ፣ጋሻ ፣ነጻ አውጪዬ እንዲሁም አዳኜ መሆንህን በመዘንጋቴ ይቅር በለኝ፡፡ በህይወቴ ለሚገጥሙኝን ግዙፍ ችግሮች ድል የምትነሳልኝ አቅሜ አንተ ነህ፡፡ ለእኔ ስላለህ ጥንቃቄ እና ጥበቃ አመሰግንሀለሁ፡፡ አንተ የእኔ ጀግና ነህ፡፡______________________________________________________________

______________________________________________________________________

____________________________________________________________________

**<u>ክፍል 2</u>**

**የቤት ስራ፡**ሳሙኤል ቀዳማዊ 17 አንብቡ፡፡

**መልመጃ፡**

1. የዳዊት አባት እሴይ ታዋቂ ሰው ሆኗል ፡፡ ዳዊትን ጨምሮ ስምንት ልጆች አሉት፤ የመጀመሪዎቹ ሶስቱ ሳኦልን ተከትለው ለጦርነት እንደወጡ አንብበናል፡፡ እነዚህ

ሶስት ወንድማማቾች ስማቸው ___________________፣ ____________________፣ እና_____________ይባለል፡፡

2. በቁጥር 14 እና 15 ላይ ስለ ዳዊት የተነገረን ምንድነው?____________________
_____________________________________________________________________

3. የግዙፉ ፍልስጥኤማዊ ዛቻ እና ማስፈራሪያ በቀን ሁለት ጊዜ ለ_____________ቀን ቀጠለ!

4. እሴይ ዳዊትን በመጥራት በጦር ሰፈሩ ወደ ነበሩት ወንድሞቹ ስንቅ አስይዞ ላከው፡፡ ይህ አባት በጦር ሜዳ ስላሉት ልጆቹ ደህንነት መስማት በጣም ጓጉቷል፡፡ ዳዊትም አባቱ ወደላከው ሄደ፡፡በቁጥር 20 እና 21 ላይ ዳዊት በዚያ ሲደርስ የተፈጠረው ነገር ምንድነው?____________________________________________________

5. ዳዊት ከወንድሞቹ ጋር ሲነጋገር የተገለጠው ማነው?______________________

6. ዳዊትም ጎልያድን በህያው እግዚአብሄር ሰራዊት ላይ የስድብ እና የእርግማን ቃል ሲናገር ሰማው፡፡ በዚህን ወቅት የእስራኤላውያን ሰራዊት ምላሽ ምን ነበር ቁጥር 24?_______________________________________________________________

7. በቁጥር 25 ላይ የእስራኤል ንጉስ ይህንን ግዙፍ ሰው ለሚገድልለት ቃል የገባው ምንድነው?

   ሀ. ___________________________________________________________

   ለ. ____________________________________________________________

   ሐ ____________________________________________________________

8. ዳዊትም በእስራኤል ላይ ይህን አይነት ውርደት የሚያደርሰውን ይህንን ግዙፍ ፍልስጥኤማዊ ለሚገድል ንጉሱ የገባውን ቃል በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ይጠይቅ ነበር፡፡ በቁጥር 26 ላይ ዳዊት ጎልያድን በምን መልክ ነበር የገለፀው?____________ ዳዊት እንደዚህ ነበር ያለው "የሕያውን አምላክ ጭፍሮች የሚገዳደር ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ማን ነው?"____________________________________________
_____________________________________________________________________

9. በቁጥር 28 ላይ ኤሊያብ ዳዊትን ተቆጣው፡፡ ኤሊያብ ዳዊትን የተቆጣበት ምክንያት ምንድነው በዳዊትስ ላይ ያቀረበው ክስ ምንድነበር?__________________________
_____________________________________________________________________

10.በቁጥር 31 እና 32 ላይ ዳዊት በዙሪያው ካሉት ሰዎች ማረጋገጫን ጠየቀ፡፡ ሳኦልም ስለዳዊት ሰምቶ ዳዊትን ወደራሱ አስመጣው፡፡ ዳዊት ለሳኦል ምን ነገረው?______________________________________________________________

____________________________________________________________________

11.ዳዊት በፈቃደኝነት ሊያደርግ ያሰበው ምን ነበር?______________________________

____________________________________________________________________

12.የሳኦል ምላሽ ምን ነበር?_______________________________________________

ሳኦል ከጎልያድ ጋር ለሚደረገው ውጊያ ያስፈልጋሉ ብሎ ትኩረት የሰጣቸው ጉዳዮች የአካል ብቃት እና የውጊያ ልምድ ላይ ብቻ ነበር፡፡ የዳዊት ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 34-35)?___________________________________________________________

ሀ. ዳዊት በምድረ በዳ በባዶ እጁ የገደላቸው አራዊት ምንድናቸው?_____እና_____

ለ. ይህን ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ የተረዳው እንዴት ነው?__________________

ሐ. ለምን እንደዚህ ሊያስበው ቻለ?______________________________________

13.የዳዊት ታዳጊ ማነው (ቁጥር 37) _________________________________________

____________________________________________________________________

14.ሳኦልም ዳዊትን ባርኮ ሸኘው ነገር ግን ከመሸኘቱ በፊት ምን አደረገ (ቁጥር 38-39)?

____________________________________________________________________

15.ሳኦል ላቀረበለት ትጥቅ የዳዊት ምላሽ ምን ነበር?____________________________

____________________________________________________________________

16.በዚያ ፈንታ ምን አደረገ (ቁጥር 39-40)? ____________________________________

____________________________________________________________________

**ገለፃ፡** በሳሙኤል ቀዳማዊ 17፡38-40 ውስጥ ዳዊት ግዙፉን ፍልስጥኤማዊ ሲገጥም ምን መልበስ እንዳለበት በዳዊት እና በሳኦል መካከል የመረዳት ልዩነት ነበረ፡፡ ሳኦል ዳዊትን የጦር እቃዎችን ሁሉ እንዲለብስ ግድ አለው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዳዊት ያለው አማራጭ የተባለውን ማድረግ ነበር፡፡ ስለዚህ በእስራኤል መካከል የረጅሙን እና ግዙፉን የሳኦልን የጦር ልብስ እንደዚሁም ሰይፍ ሞከረው፡፡ ነገር ግን ዳዊት የነበረው የጦር ልምድ ጎልያድን ለመግጠም ይህንን አይነት የጦር ትጥቅ መታቅ የሚጠይቅ አልነበረም፡፡ ነገር ግን በጎችን በምድረበዳ ሊነጥቁት የሚመጡትን አንበሳ እና ድብ ሲገጥም የሚታጠቀውን ትጥቅ ነው ፡፡ ወደ ወንዝ በመሄድ አምስት ጠጠሮች እና ወንጭፉን ታጠቀ፡፡

ዳዊት በጎች የሚጠብቅበትን ዘንግ ፣አምስቱን ጠጠሮች ፣እንደዚሁም ወንጭፉን ይዞ ወደ ፍልስጥኤማዊው ቀረበ። እኛንም እግዚአብሄር በህይወታችን ወደገጥሙን ግዙፍ ነገሮች ሲያስጠጋን እንደ ጠላቶቻችን ውጪያዊ ማንነታችንን በማግዘፍ ሳይሆን እግዚአብሄር እራሱ ነገሮችን በሚያይበት እይታ እና መረዳት በእምነት እንድንቀርባቸው ነው የሚደርገን። ዳዊት ወንጭፉን ይዞ ከግዙፉ ፍልስጥኤማዊ ጋር ለመፋለም ወደ ውጊያው መድረክ ቀርቧል። ሁለቱ ተፋላሚዎች ፊት ለፊት ተገናኙ። እስቲ ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ በሁለቱ መካከል ልዩነት ስለፈጠረው ነገር አስቡ ። ምን ይሆን ዳዊትን በግዙፉ ፍልስጥኤማዊ ላይ እንዲገዝፍበት ያደረገው?

**ክፍል 3**

**የትግበራ ጥያቄዎች፡** ከዚህ ታሪክ ውስጥ ለህይወታችን ትምህርት የሚሆን ነገር ማግኘት አለብን። በክፍል አንድ ውስጥ በህይወታችን ውስጥ ስለገጠሙን ግዙፍ ተግዳሮቶች መመልከት የምንችልበትን ትምህርት አግኝተን ነበር። ቀጥሎ ባለው ክፍል ደግሞ እነዚህን ተግዳሮቶቻችንን ስንገጥም መልበስ የሚገባንን ዕቃ ጦር እንመለከታለን።

1. በህይወታችሁ ውስጥ ገዝፈው የሚስጨንቋችሁን ፣የሚያስፈራሯችሁን ነገሮች መልሳችሁ አስቡ።________________________________________
2. በቁጥር 24 ላይ እስራኤላውያን ግዙፉ ፍልስጥኤማዊ ተገልጦ ሲናገር በፍርሃት ሸሹ። እናንተስ በህይወታችሁ ውስጥ እናንተንም ሆነ የእግዚአብሄርን ህዝብ የሚገዳደር ግዙፍ ጠላት ሲገጥማችሁ የምትወስዱት እርምጃ ምንድነው?__________

   ________________________________________________________
3. ሳኦል እና ጎልያድ ሁለቱም ሙሉ የጦር ትጥቅ አላቸው። እናንተስ የህያው እግዚአብሄርን ሰራዊት ሊገጥም የሚመጣውን ግዙፍ ጠላት ለመግጠም የምትታጠቁት ትጥቅ ምንድነው?__________________________________________

   ________________________________________________________
4. ጎልያድ የፍልስጥኤማውያን ጀግና ነው። የእናንተስ ጀግና ማነው? ስለእናንተ የሚዋጋው ማነው? ከጠላቶቻችሁስ የሚታደጋችሁ ማነው?______________________

   ________________________________________________________

**ማሰላሰል፡**

1. በአዲስ ኪዳን ውስጥ በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ ጳውሎስ ስለ የእግዚአብሄር የጦር እቃ ተናግሯል። ኤፌሶን 6፡10-17 ያለውን ክፍል አንብቡ። በዚህ ክፍል ውስጥ

በጌታ እና በኃይሉ ችሎት የበረታን እንድንሆን ይመክረናል። በቁጥር 11 ላይ የእግዚአብሄርን እቃ ጦር በሙሉ እንድንለብስ ይነግረናል። የትኛውም የሰውነታችን ክፍል ለክፉው ስራ የተጋለጠ ሆኖ እንዳይገኝ የእግዚአብሄርን እቃ ጦር በሙሉ ለብሰን እንድንገኝ ይመክረናል። እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች ዋናው ጠላታችን ሰይጣን እንደሆነ ያስተምረናል። በቁጥር 12 ላይ ውጊያችን ከማን ጋር እንደሆነ ይነግረናል። በዚህ ክፍል መሰረት የምንዋጋው ከማን ጋር ነው?

ሀ. ______________________________________________

ለ. ______________________________________________

ሐ ______________________________________________

መ. ______________________________________________

2. የክፉውን ፍላፃ መቋቋም እንችል ዘንድ የእግዚአብሄር አቅርቦት ምንድነው (ቁጥር 14-18) ? ስለዚህ

ሀ. ______________________________________________

ለ. ______________________________________________

ሐ ______________________________________________

መ. ______________________________________________

ሠ. ______________________________________________

ረ. ______________________________________________

ሰ. ______________________________________________

እግዚአብሄር ብርታቱን ያስታጥቀናል ፣ታላቅ የሆነውንም ኃይሉን ይሰጠናል እንደዚሁም የሚንበለበሉትን የክፉ ፍላፃዎች የምንቋቋምበትን ዕቃ ጦር ያስታጥቀናል። የጦር እቃዎቹ በልካችን የተሰሩ ናቸው። የሚያስፈልገን ስፍራችንን ይዘን መቆም ብቻ ነው። እነዚህን የጦር እቃዎች በየእለቱ ለብሰናቸው መገኘት ይኖርብናል። ከቁጥር 13 - 18 ያለውን ክፍል በካርዳችሁ ላይ በመፃፍ አጥኗአቸው በዚህ ክፍል የእግዚአብሄር መንፈስ ስለ እያንዳንዱ የጦር እቃ ምንነት እና እነዚህን እቃዎች በአግባቡ በመልበሳችን ልታገኙት ስለምትችሉት ድል ሲያስተምራችሁ በንቃት አድምጡት።

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር ሆይ በየእለቱ ህይወቴ በተለያዩ ጦርነቶች ውስጥ አልፋለሁ፡፡ ከእኔ አቅም በላይ የሆኑ ተግዳሮቶች ይገጥሙኛል፡፡ ስለዚህም አንዳንዶች ስምህን በማስከበር ፈንታ በፍርሃት ሸሽቼ መደበቅን የመረጥኩ እስኪመስላቸው እፈራለሁ፡፡ አብዛኛዎቹ ጠላቶቼም ሃሳቤን በመቆጣጠርና በማርከስ እንደዚሁም ምርጫዬን በማበላሸት የሚገለጡ ናቸው፡፡ ቃልህ ጠላት ሊያጠቃው የማይችል የጦር እቃ ነው፡፡ ስለዚህም ማለዳ ስነሳ የእውነትን ቀበቶ ታጥቄ ፣የፅድቅን ጥሩር ለብሼ፣በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት ተጫምቼ በመቆም፣የእምነትን ጋሻ ይዤ ፣የመዳን የራስ ቁር የሆነውን ቃልህን ማጥለቅ ይሆንልኝ ዘንድ አስችለኝ፡፡ ስለዚህም እያንዳንዱን ቀን አዳኜ እና ታዳጊዬ አንተ ብቻ መሆንህን አውቄ ካለአንተ ምንም ማድረግ እንደማልችል አውቄ አና ተረድቼ እንድኖር አድርገኝ፡፡ በአንተ ሁሉን ማድረጌን በማወቄ ምክንያት በህይወቴ ስላገኘሁት ሰላም አመሰግንሀለሁ፡፡________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## ክፍል 4

**መግቢያ፡** ጥናታችንን ቀጥለናል በሳሙኤል ቀዳማዊ 17፡41 ላይ የዳዊት ጠላት ወደ እርሱ እንደ ቀረበ አንብበናል፡፡ በምዕራፍ 16፡7 ሰው እንደሚያይ እግዚአብሄር እንደማያይ ተመልክተናል፡፡ ግዙፉ ፍልስጥኤማዊ ጎልያድ ስለሚገጥመው ሰው ልብ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡

**የቤት ስራ ፡** መጽሐፈ ሳሙኤል 17፡41-51 ያለውን ክፍል በድጋሚ አንብቡት፡፡

**መልመጃ፡**

1. በቁጥር 41 መሰረት ጎልያድ ወደ ፍልሚያው ስፍራ ሲመጣ ማንን ነበር ይዞ ነው የመጣው?_________________________________________________________

   _________________________________________________________________
2. ሰው ውጪን ሲመለከት እግዚአብሄር ግን?________________________________
3. ፍልስጥኤማዊው በተመለከተው ነገር የተሰማው ስሜት ምን ነበር(ቁጥር 42)?____

4. ጎልያድ የእርሱን ልብ ሊገልፅ የሚችል የተናገረው ቃል ምን ነበር (43-44)?______
5. የዳዊት ምላሽ ምን ነበር? ሁለቱም ተዋጊዎች ይዘው የመጡት ምንድነበር?_______

   ሀ. ጎልያድ:_______________________________________________

   ለ. ዳዊት:_______________________________________________

   ዳዊት ወደ ውጊያው መድረክ ሲመጣ የያዘው የጦረ መሳሪያ ጠጠርና ወንጭፍ ሳይሆን ሁሉን የሚችለውን የእስራኤል አምላክ የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሄርን ስም መሆኑ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው።

6. ጎልያድ ወደ ውጊያው መድረክ የመጣው ዳዊትን ገድሎ ታላቅ መሆኑን ሊያስመሰክር ነው። ዳዊትስ በዚህ ውጊያ ፍልስጥኤማውያንም ሆኑ የእስራኤል ሰራዊት ምን እንዲያውቁ ነው ወደ ውጊያው የመጣው? ______________________

   ______________________________________________________

7. ዳዊት የውጊያውን ውጤት አውቋል (ቁጥር 47)። የእስራኤል ጀግና ማን ነበር?____

   ______________________________________________________

8. ውጤቱ ምንድነበር?__________________________________________
9. በቁጥር 48- 49 ላይ ፍልስጥኤማዊው በአንድ አቅጣጫ ዳዊት ደግሞ በሌላ አቅጣጫ

   ______________________________________________________

10. ዳዊትም ድንጋዩን በወንጭፉ አስወነጨፈው ግዙፉ ፍልስጥኤማዊም ምን እንደተፈጠረ እንኳን ሳያውቅ ተዘረረ።ቁጥር 50 የተፈጠረውን ነገር እንደዚህ በማለት ማጠቃለያ ይሰጠናል።________________________________

    ______________________________________________________

    ጎልያድ ሰይፉን ከሰገባው እንኳን የመምዘዝ እድል አላገኘም። ዳዊት ግን የጎልያድን ሰይፍ ከሰገባው መዝዞ የጎልያድን እራስ ቆረጠበት።

**ገለፃ**: ጠላቶች የተመኩበት ጀግና ሞቷል። እኔስ ከገጠመኝ ግዙፍ ጠላት ጋር ስለመዋጋት ሳስብ ከእኔ ጋር የሚዋጋው ጠላት ዋጋው ምን ሊሆን እንደሚገባ ነው የተረዳሁት።

1. ጠላትን እየተጠጋሁት ያለሁት "እንደ ትንሽ ፣መልኩ ያማረ አቅመቢስ ብላቴና ሆኜ ይሆን?"
2. ወይንስ ጠላት የሚንቀኝ እና የሚስቅብኝ ምስኪን ?

3. ወይንስ ጠላቱ በጣም ኃይለኛ በመሆኑ  በራሱ አቅም ምንም ሊያደርግ እንደማይችል በማወቅ ወደ ውጊያው እንደሮጠው እንደ ዳዊት?
4. ወይንስ ደግሞ ውጊያው የእግዚአብሄር እንደሆነ እና እግዚአብሄር ታዳጊ መሆኑን አውቆ ነው?

<u>**ክፍል 5**</u>

**የቤት ስራ፡**መጽሐፈ ሳሙኤል 17፡51-58 ያለውን ክፍል አንብቡ።

**መልመጃ፡**

1. አሁን ጎልያድ ሞቷል ፡፡ ስለዚህ የሚሸሹት እነማን ናቸው?__________________
2. የእግዚአብሄር ሰራዊት፣ እስራኤላውያን እና የይሁዳ ሰዎች ምን ነበር ያደረጉት ቁጥር 52?______________________________________________________
   ፍልስጥኤማውያንን እስከ ጎልያድ የትውልድ ከተማ እስከ_______________ድረስ አሳደዷቸው (ስሙኤል 17፡4)እስከ____________________በር ድረስ አሳደዷቸው።
   *ማስታወሻ፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ካርታ ካለ ጌት እና ኤክሮን  ምድራቱ ለአስራ ሁለቱ ነገዶች ስትከፋፈል በዚያ ስፍራ ላይ ተገልፀዋል።*
3. እስራኤላውያን በፍልስጥኤማውያን ሰፈር ምን አደረጉ ቁጥር 53?_____________
   ፍልስጥኤማውያን ወደኋላ ዞረው ሸሹ። በዳዊትና በጎልያድ መካከል የተካሄደውን ውጊያ ሲመለከቱ ድል የእነርሱ እንደሆነ እርግጠኞች ነበሩ። ነገር ግን ውጊያው ሲጠናቀቅ ህይወታቸውን ለማትረፍ ሁሉም ሸሹ ሲሸሹም መሳሪያቸውን ጥለው ነበር የሸሹት። በዚያን ዘመን ፍልስጥኤማውያን በተለይ ከብረት ጋር የተያያዙ ስራዎችን በተሻለ ሁኔታ መስራት የሚችሉ ስለነበሩ የያዟቸው መሳሪያዎች ከእስራኤላውያን መሳሪያዎች  የተሻሉ ነበሩ። እስራኤላውያን የፍልስጥኤማውያንን የጦር ሰፈር ሲቆጣጠሩ ምን ሊያገኙ እንደሚችሉ አስቡ።
4. የተቆረጠው የጎልያድ ጭንቅላት ምን ሆነ ቁጥር 54?______________________
5. የፍልስጥኤማውያን መሳሪያ የት ነበር?________________________________

**ማጠቃለያ፡**

1. ከቁጥር 55-58 ድረስ ያሉት ቁጥሮች ማጠቃለያ ይመስላሉ። ይህንን ታሪክ አንድ ጥያቄ በመጠየቅ እንደምድመው። በሳሙኤል ቀዳማዊ 16፡14-23 ውስጥ ሳኦልን ክፉ መንፈስ ሲያስቃየው በነበረበት ወቅት ሲያገለግለው የነበረው ዳዊት ከሆነ ለምንድነው ሳኦል በውጊያው ሜዳ ሊያውቀው ያልቻለው? ሳኦልም ሆነ አበኔር ዳዊትን አልለዩትም ።በቁጥር 58 ላይ ሳኦል እንደዚህ ብሎ ጠየቀ፡____________________ ዳዊትም እንደዚህ ብሎ መለሰ፡__________________________________________
2. ሳኦል ለምን ሊያውቀው እንዳልቻለ አናውቅም ። የሳኦል አገልጋይ በሳሙኤል ቀዳማዊ 16፡18 ላይ የተናገረውን ነገር አስታውሱ

**የቤት ስራ ፡** የጎልያድን እና የዳዊትን ታሪክ ከዚህ በፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብባችሁት የማታውቁ ከሆነ በመስማት ደረጃ ብቻ ከሆነ ያላችሁት ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከቱ።

1. ከዚህ ታሪክ ውስጥ ያገኛችኋቸውን እውነታዎች።
2. ስለእግዚአብሄር ማንነት እና ከሰዎች ጋር እንዲኖረው ስለሚፈልገው ግንኙነት ያገኛችሁትን መረዳት።
3. የሰው ልጅ አቅም ምን ያህል እንደሆነ ያገኛችሁትን መረዳት።
4. ከህይወታችሁ ጋር ልታዛምዱት የምትችሉትን ተግባራዊ ልምምድ።

# ትምርት ሶስት

# እግዚአብሄር ከእኔ ጋር ነው

## ከመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 18-31 የተወሰደ ታሪክ

## ዳዊት ፣አቢጊያ፣ሳኦል

---

የትምህርት 3 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 3፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 18 - 31

- የሳኦል ቀናተኛ አይን
- የዳዊት ስኬት
- ዳዊት እና ናባል
- ዳዊት እና አቢጊያ
- የሳኦል መሞት
- የእግዚአብሄር የተስፋ ቃል፡ ፍፃሜ እና ተስፋ

### መግቢያ

የዳዊት ስኬት ያስገኘው ውጤት ምን ነበር? በሚሰራው ሁሉ መከናወን የሆነለት በምን ምክንያት ነበር? የሳኦል ምላሽ ምን ነበር? በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ መጨረሻ ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተደረገ ጦርነት የዳዊት ወዳጅ በነበረው ዮናታን እና በአባቱ በሳኦል ላይ የደረሰውን ነገር አንብበናል፡፡

እናንተስ ለሌሎች ስኬት የምትሰጡት ምላሽ ምንድነው? ዳዊት ከስኬቱ እና ሳኦል ሊገድለው ከሚያደርገው ሙከራ በተቃራኒው ከተቀባው የእስራኤል ንጉስ ከሳኦል ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር ተመልከቱ፡፡ ከእግዚአብሄር በሆነው ጥበብ እና አንድ ሰው የራሱንም ሆነ የሌሎችን ስኬት በምን መልኩ እንደሚመለከት ከዚህ ክፍል ተማሩ፡፡

**ክፍል 1**

**ትምህርት፡** ምዕራፍ 18 ዮናታን የሚባል አዲስ ሰው ያስተዋውቀናል፡፡ ዳዊትና ዮናታን በጣም የተቀራረቡ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ዮናታን ከዳዊት ጋር በመንፈስ አንድ እንደነበረ እናነባለን፡፡ ዳዊትን እንደራሱ የሚወደው ሲሆን ከዳዊት ጋርም ቃል ኪዳን አድርጓል ሳሙኤል፤ ቀዳማዊ 20፡16-17፡፡ በመርህ ደረጃ ዮናታን የንጉስ ልጅ እንደመሆኑ አባቱ ሲሞት ተተኪ ንጉስ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለዳዊት ብዙ ነገሮች በመፃፋቸው ምክንያት ስለዳዊት እና ስለ ዮናታን በጥልቀት አናጠናም፡፡ በአጭሩ ልንል የምንችለው ጓደኝነታቸው እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ የዘለቀ ነበር፡፡ ስለዮናታን የበለጠ ማወቅ ከፈለጋችሁ የሚከተሉትን ክፍሎች ተመልከቱ፡፡

1. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 19፡1-7 ዮናታን እንደ ዳዊት ጠበቃ
2. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 20 ዮናታን አባቱ ሳኦል ሊገድለው እንደፈለገ ነግሮት አስጠነቀቀው
3. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 31፡2-የዮናታን መሞት
4. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 4፡4 የዮናታን ልጅ ሜምፊቦስቴ (መጽሐፈ ሳሙኤል 9)

**የቤት ስራ፡**ሳሙኤል ቀዳማዊ 18፡5-17

**መልመጃ፡** እነዚህ ጥቂት ቁጥሮች በዳዊት እና በሳኦል መካከል ስለነበረው ግንኙነት ይነግሩናል፡፡

1. ዳዊት በሳኦል ዘንድ የነበረው ስፍራ ምን ይመስል ነበር?____________________
2. ስለዳዊት ምን አወቃችሁ?________________________________________
3. ህዝቡና ሳኦል ለዳዊት የሰጡት ምላሽ ምን ይመስል ነበር?__________________
4. ዳዊት ከጦርነት ሲመለስ ሴቶቹ እንዴት ነበር የተቀበሉት ቁጥር 6-7?__________

   ________________________________________________________
5. ምን ብለው ነበር የዘፈኑት?_______________________________________

6. ሳኦልስ ለዚህ ሁኔታ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር ቁጥር 8? ___________________

7. ቁጥር 9 ትርጉም ያለው ቃል ይጠቀማል፡፡ ቃሉ ምን የሚል ነበር?_____________ ሳኦል "ተመቅኝቶ ተመለከተው" ይላል አዲሱ መደበኛ ትርጉም ደግሞ "በቅናት አይን" ተመለከተው ይላል *"ነፃነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ጥሪ "* በሚለው የጥናት ክፍል "ቅናት" ስለሚለው ቃል ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሰረት ቅናት ማለት በሌላው የመተካት ፍርሃት ማለት ነው፡፡ ታዲያ ሳኦል ለምንድነው ዳዊትን ተመቅኝቶ የተመለከተው? ለምንድነው ሁልጊዜ በቅናት አይን የሚመለከተው?

8. በቁጥር 10 እና 11 ቀጥሎ የሆነው ነገር ምንድነው?

   ሀ. ለሳኦል :_____________________________________________

   ለ. ለዳዊት፡_____________________________________________

9. የሳኦል ትልቁ ፍራቻው ምን ነበር ቁጥር 12______________________________

10. ሳኦል ለፍርሃቱ መፍትሄ አድርጎ የወሰደው ምን ነበር ቁጥር 13?_____________

11. ዳዊት ተዋጊ ሆነ፡፡ በሚመራቸው ሰዎች መካከል ከፍተኛ ስፍራን አገኘ የሚሰራው ነገር ሁሉ ይከናወንለታል ምክንያቱም ደግሞ ቁጥር 14?___________________

12. ዳዊት ስኬታማ ነበር ታዲያ ሳኦል ለዚህ ሁኔታ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር ቁጥር 15?_____________________________________________________

<u>**ክፌል 2**</u>

**ትምህርት፡** በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስኬት የሚለው ቃል ተደጋግሞ ይጠቀሳል፡፡ ስኬትን ከተለያዩ ነገሮች አንፃር ልንመለከተው እንችላለን ብዙ ገንዘብ ከማግኘት ጋር፣ትልቅ ቦታን ከመያዝ ጋር፣ ትልቅ ክብርን ከማግኘት ጋር ከመሳሰሉት ሁኔታዎች ጋር፡፡ ስለዳዊት ስኬት ስናነሳ ግን የምናወራው ስለ ጥበቡ ነው፡፡ ቁጥር 4 "ዳዊትም በአካሄዱ ሁሉ አስተውሎ ያደርግ ነበር እግዚአብሄርም ከእርሱ ጋር ነበረ፡፡" ቁጥር 15 ደግሞ "ሳኦልም እጅግ ብልህ እንደሆነ አይቶ እጅግ ፈራው" ይላል፡፡

በመዝሙር 111፡10 ላይ እንደዚህ የሚል ቃል እናነባለን "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሄርን መፍራት ነው፡፡" የዳዊት ህይወት ከእግዚአብሄር ጋር የተጣበቀ ነው፡፡ እግዚአብሄርን የሚያከብር ህይወት ነው ያለው፡፡ ለእግዚአብሄር ህጎች እና ትዕዛዛት ይገዛል እግዚአብሄርም ደግሞ በእነዚህ ህጎች እና ትእዛዛት ጥበብ እና ማስተዋሉን ያፈስስለታል፡፡ ሳኦል ደግሞ የእግዚአብሄር መንፈስ ከእርሱ እንደራቀ ተረድቷል አሁን በክፉ መንፈስ እየተሰቃየ ነው፡፡

ስለዚህ ዳዊትን ለማስወገድ የአንድ ሺህ ሰዎች መሪ በማድረግ ወደ ውጊያ ላከው፡፡ የዳዊት ጥበብ የተሞላበት አካሄድ እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ለሳኦልም ሆነ ለህዝቡ ምስክር ነበር፡፡ "እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ስለነበረ የሚሰራው ሁሉ ይከናወንለት ነበር፡፡"

**ገለፃ፡** በሳሙኤል ቀዳማዊ 18 ውስጥ እነዚህ ሁለት ሰዎች ምን ያህል የተለያዩ እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡ ዳዊት በሚያደርጋቸው ጦርነቶች የተሳካለት ባለድል ሲሆን ሳኦል ግን በዳዊት ስኬት የሚቀና እና ፈሪ ነበር፡፡ እግዚአብሄር ከእርሱ እንደተለየ ነገር ግን ከዳዊት ጋር እንዳለ ያውቅ ነበር፡፡ ዳዊት በገናን በመደርደር ሲያገለግለው ሳኦል ግን ሊገድለው ከግድግዳም ጋር ሊያጣብቀው ብዙ ጊዜ ጦሩን ወርውሮበታል፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ ይሁዳና እስራኤል በሙሉ ዳዊትን ይወዱት ነበር (ቁጥር 16)፡፡_____________________________________

በቁጥር 17 ላይ ሳኦል "የፍልስጥኤማውያን እጅ እንጂ የእኔ እጅ በእርሱ ላይ አትሁን ይል ነበር፡፡ ዳዊትን ወደ ጦርነት ከላከው እርሱ ማድረግ የፈለገውን መግደል ፍልስጥኤማውያን ይፈፅሙለታል ማለትም ዳዊትን ይገድሉለታል ፡፡ ሳኦል ዳዊትን ለማስወገድ ከመፈለጉ የተነሳ ልክ እንደፍልስጥኤማውያን ለዳዊት ጠላት ሆኖት ነበር፡፡ የሳኦል ታላቅ ቅናት ዳዊትን እንዲገድል አነሳሳው፡፡

**ትግበራ፡**

1. እስቲ እናንተ በግላችሁ ነገሮችን በጥበብ የሚያደርጉ ሰዎችን ታውቁ ይሆን?______
2. በእናንተ ህይወት ውስጥስ ምን አይነት ፍርሃት ነው ያለው?__________________
3. እናንተስ በህይወታችሁ ውስጥ ፍርሃት እና ዝቅተኝነት እንዲሰማችሁ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድናቸው?____________________________________________
4. እግዚአብሄር ከእናንተ ጋር መሆኑን ማወቃችሁ በህይወታችሁ ውስጥ ምን ልዩነት ያመጣል?__________________________________________________

   __________________________________________________

## <u>ክፍል 3</u>

**በጥልቀት መመልከት፡** ቀሪዎቹ የመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ክፍሎች ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ስላደረጋቸው ሙከራዎች ይነግሩናል፡፡ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ጦር ሜዳ መላክ እና የመሳሰሉትን ዘዴዎች ቢጠቀምም ዳዊት ግን ሳኦልን ብዙ ጊዜ ከሞት ታድጎታል፡፡ ይህንን

ክፍል ማጥናት በጣም አስደሳች ነው። ምክንያቱም ማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ የምትፅፏቸው ብዙ አዳዲስ ስሞችን እና ስፍራዎችን ይዟል። እነዚህን ስሞች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ መያዛችሁ ሌላ ጊዜ መፅሐፍ ቅዱስን ስታጠኑ እንዳትቸገሩ ያደርጋችኋል። በመጽሐፍ ቅዱሳችሁን ሁልጊዜ መያዝ አትርሱ ምክንያቱም የተለያዩ ስፍራዎችን ከካርታችሁ ላይ መመልከት ትችላላሁ።

**የቤት ስራ፡** ሳሙኤል ቀዳማዊ 25 አንብቡ። በሳሙኤል ቀዳማዊ 25፡1 ላይ ዳዊትን ንጉስ እንዲሆን የቀባው ሳሙኤል መሞቱን ይነግረናል። እርሱንም በአርማቴም ከቀበሩት በኋላ ዳዊት ወደ ፋራን ምድረበዳ እንደሄደ ይነግረናል። እስቲ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰውን አስገራሚ ታሪክ እንመልከት።

1. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱን ሰዎች ዘርዝሩ።
2. ዳዊት ናባልን የጠየቀው ምን ነበር የናባልስ ምላሽ ምን ነበር?
3. አቢጊያስ ምን አደረገች?
4. የዚያ ታሪክ ውጤትስ ምን ነበር?

**መልመጃ:**

1. የናባል ታሪክ ምን ያስረዳናል ቁጥር 2 — 3 ?____________________________

   ____________________________________________________________
2. ስለ አቢጊያስ ምን እንማራለን ቁጥር 3?___________________________________
3. በቁጥር 4- 8 ላይ ዳዊት ወደናባል ሰዎችን ላከ። ናባልን በመጀመሪያ ምን ብለው ነው የጠየቁት ቁጥር 5-6?__________________________________________

   ____________________________________________________________
4. የመልዕክቱስ ሁለተኛ ክፍል ምን የሚል ነበር ቁጥር 7-8?___________________

   ____________________________________________________________
5. ናባል ምን ብሎ መልእክተኞቹን መለሳቸው ቁጥር 10-11?____________________

   ____________________________________________________________
6. ለናባል ምላሽ ዳዊት ሊወስድ የነበረው እርምጃ ምን ነበር፡ቁጥር 12-13?__________

   ____________________________________________________________
7. ለናባል ሚስት ለአቢጊያ ከአገልጋዮቿ አንዱ ምን ብሎ ነገራት ቁጥር 14-17?____

8. አቢጊያም ወዲያውኑ እርምጃ ወሰደች ምን ነበር ያደረገችው?__________________

______________________________________________________________________

9. በቁጥር 20- 22 ላይ ዳዊት ምን ብሎ ተናገረ?____________________________

______________________________________________________________________

10. አቢጊያ በዳዊት ፊት ምን አደረገች ቁጥር 23-24?___________________________

11. ዳዊትን ምን እንዲያደርግ ጠየቀችው ስለናባልስ ምን ነገረችው ቁጥር 25?________

______________________________________________________________________

12. ቁጥር 26-31 ዳዊትን በምን አይነት መልኩ አናገረችው ለራሷስ የሰጠቸው ስፍራ ምን ይመስል ነበር?__________________________________________________

______________________________________________________________________

## <u>ክፍል 4</u>

**ገለፃ፡** ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ አቢጊያ ስለተናገረችው እና ስላደረገችው ነገር መጠነኛ ገለፃ አድርጉ፡፡ አቢጊያ በዳዊት ፊት እራሷን ያቀረበችው በውጪአዊ ማንነት ብቻ አልነበረም ከውስጥ በሆነ ትህትና እና ቅንነት ነበር፡፡ እራሷን ከዳዊት ጋር ለማነፃፀር የተጠቀመችው ቃል በጌታ እና በአገልጋይ መካከል ባለ ግንኙነት ምሳሌ ነው፡፡ በዚህ ቁጥር ውስጥ ጌታዬ የሚለው ቃል ስንት ጊዜ እንደተጠቀሰ ተመልከቱ፡፡ ከዳዊት ጋር ሰላምን ለማድረግ ነው የመጣችው፡፡ በናባል ብልግና ምክንያት ለተፈጠረው አደጋ ነቀፋውን ሁሉ እርሷ ተሸክማ ነበር፡፡

አቢጊያ ዳዊትን በቀሉን ለእግዚአብሄር እንዲተው በእጁ ደም እንዳይፈስ አስጠነቀቀችው፡፡ በቁጥር 18 ላይ ለዳዊት እና ለሰዎቹ ያዘጋጀችውን ስጦታ በሙሉ ሰጠችው፡፡ እግዚአብሄር በዳዊት በኩል ለሚመሰርተው መንግስት በሚታገለው በዳዊት እና በሰዎቹ ላይ የእርሷ ባል ችግር በመፍጠሩ ይቅርታ ጠየቀች፡፡ የእርሱን ህይወት የሚፈልጉ ሰዎች ቢኖሩም እግዚአብሄር አሳልፎ እንደማይሰጠው ነገረችው፡፡ ጠላቶቹንም እግዚአብሄር በእርሱ ህይወት በወንጭፍ ብቻ የሰራውን ታላቅ ስራ እንዲያስታውሱ አሳሰበቻቸው፡፡ በመጨረሻም ጊዜው ደርሶ የመሪነት በትሩን ሲጨብጥ ያለ አግባብ የፈሰሰው ንፁህ ደም እንዲሁም በራሱ እጅ የተበቀለው ባለመኖሩ ህሊናው ነጻ እንደሚሆንለት መከረች፡፡

**የትግበራ ጥያቄ፡** በሌሎች ሰዎች ስህተት የተፈጠረን ችግር ነቀፋውን እራሴ በመሸከም ሰላም ለመፍጠር እና ችግርን ለማስወገድ ምን ያህል ዋጋ እከፍላለሁ?________________________

_____________________________________________________________________________

_____________________________________________________________________________

**መልመጃ፡**

1. የዳዊት ምላሽ ለእግዚአብሄር ፀጋ በአራት መልኩ እውቅና ይሰጣል፡፡
   ሀ. ቁጥር 32፡ ለእግዚአብሄር__________________________________________
   ለ. ቁጥር 33፡ ለአቢጊያ______________________________________________
   ሐ. ቁጥር 34፡ ለዳዊት ______________________________________________
   መ. ቁጥር 34፡ ለናባል እና ለዳዊት ሰዎች___________________________________

   ዳዊትም ስጦታዋን ተቀብሎ ቃሏን እንደሚያከብር ነግሯት ወደ ቤቷ ላካት(ቁጥር 35)
2. አቢጊያ እቤት ስትደርስ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 36)?__________________________
3. በቀጣዩ ቀን ማለዳ ምን ሆነ (ቁጥር 37-38) ?____________________________
4. ታሪኩ የተጠናቀቀው እንዴት ነበር (ቁጥር 39-42)?_________________________

**ትግበራ፡**

1. ዳዊት ናባል ከሞተ በኋላ አቢጊያ ሚስት እንድትሆነው ጥያቄ አቀረበ ቁጥር 41 ምላሿ ምን ነበር?_____________________________________________________
2. አቢጊያ የዳዊት ሚስት መሆን ለእርሷ ክብር እንደሆነ በትህትና ተናገረች፡፡ እርሱን ለማገልገል እና የአገልጋቹንም እንኳ እግር ለማጠብ የተዘጋጀች እንደሆነች ተናገረች፡፡ በትህትና እርሷ ከአገልጋዮቹ በታች እንደሆነች ተናገረች፡፡
   ሀ. የአቢጊያ ከዳዊት ጋር በጋብቻ የተጣመረችበት ስረዐት ከምትኖርበት ማህበረሰብ ልማድ ጋር እንዴት ሊጣጣም ይችላል?_____________
   ለ. እናንተስ ስለትዳር የጥምረት ስርአት ካላችሁ መረዳት ጋር የአቢጊያን ሁኔታ እንዴት ታዩታላችሁ?________________________________

<u>**ክፍል 5**</u>

***መግቢያ፡*** *ሳኦል ሊታወስ የሚችለው እንዴት ነው? ዳዊት ጎልያድን ከገደለበት ቀን ጀምሮ ሳኦል በቅናት አይን እንደተከታተለው ነበር የኖረው። ሳኦል በፍርሃት እና በቅናት ተከቦ የኖረ ሰው ነው። በአንድ ወቅት ከእርሱ ጋር  የነበረው የእግዚአብሄር መንፈስ አሁን ከዳዊት ጋር እንደሆነ ያውቃል። እግዚአብሄርም ቀጣዩ የእስራኤል ንጉስ ይሆን ዘንድ እረኛውን እና ትንሹን ብላቴና በነቢዩ ሳሙኤል በኩል ቀብቶታል። ሳኦል ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጋ እንዲሞት ብዙ ጥረት አድርጓል ነገር ግን በፍልስጥኤማውያን ክፉኛ ቆስሎ እስኪሞት ድረስ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ማሰብ አላቆመም ነበር።*

**የቤት ስራ፡** *መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ  31 አንብቡ።*

***መልመጃ:***

1. ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤላውያን ጋር እየተዋጉ ነበር ።በቁጥር 1 - 3 ምን ተፈጠረ?
   ሀ. በእስራኤላውያን፡________________________________________
   ለ. በዮናታን እና በወንድሙ፡__________________________________
   ሐ. በሳኦል ፡_______________________________________________
2. ሳኦል ጋሻ ጃግሬውን ምን እንዲያደርግለት ጠየቀው (ቁጥር 4)?_______________
3. ነገር ግን ጋሻ ጃግሬው ይህንን ማድረግ አልቻለም እጅግ ፈራ። ታዲያም ሳኦል ምን ማድረግ    መረጠ?_______________________________________________
4. ሳኦል ሲሞት ጋሻ ጃግሬውስ ምን አደረገ?_____________________________
5. ቁጥር 6 በዚያን ቀን ምን እንደተከናወነ ማጠቃለያ ይሰጠናል?_________________
6. የእስራኤል መሸነፍ እና የሳኦል መሞት ምን ነበር ያስከተለው (ቁጥር 7) ?_______
7. ከቁጥር 8 -10 ያለው ክፍል ስለጦርነቱ አጠቃላይ ገፅታ ዝርዝር ይነግረናል። ፍልስጥኤማውያን እሬሳዎቹን ለመገፈፍ ሲመጡ ምን ነበር ያገኙት?___________
8. ምን አደረጉ?___________________________________________________
9. የኢያቢስ ገለአድ ሰዎች (እስራኤላውያን )ፍልስጥኤማውያን በሳኦል ላይ ያደረጉትን ሲሰሙ ምን አደረጉ?_____________________________________________

**ገለፃ፡** ይህ ወቅት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ አሳዛኙ ወቅት ነበር፡፡ ታዲያ ሳኦል በምን መልኩ ይታወሳል? መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ሁሉ ነገር ስለተሰጠው ነገር ግን ያለምንም ውጤት ስለሞተው ሰው መልካም ያልሆነ ምስል ይሰጠናል፡፡ የሰውነቱ ጥንካሬ እና የትከሻው ስፋት እንዲሁም ንግስናው ሁሉ አልፈዋል፡፡ ልጁም ዮናታን ሞቷል፡፡ በአንድ ወቅት ይመራው የነበረው አሁን ግን ተሸንፈው ምድራቸውን እና ህዝባቸውን ጥለው ለሸሹት ሰራዊቶች ምሳሌ የሆነ መሪያቸው ነበር፡፡ ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን አሸነፉ የሳኦልን እና የልጆቹን ሬሳ በቤተሳን ግንብ ላይ ሰቀሉ፡፡

የሳኦል የንግስና ዘመን እስራኤል በተደጋጋሚ በፍልስጥኤማውያን ጥቃት እና ሽንፈት የደረሰባትን ለእስራኤል የጨለማ ዘመን የሆነውን ጊዜ ያንፀባርቃል፡፡ ሳኦል እግዚአብሄር ከዳዊት ጋር እንዳለ አውቋል፡፡ ህዝቡ በውጊያ ጀግና ለሆነው ለዳዊት የዘፈኑትን ዘፈን ሰምቷል ፡፡ የሳኦል በራሱ ሰይፍ ላይ ወድቆ መሞቱ ያለጥርጥር የመጨረሻውን ሽንፈቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ሳኦል ያለምንም ተስፋ ህይወቱን አጣ፡፡ በውጊያውም ልጆቹም ሞተዋል፡፡ የሳኦል ጦር ሸሸ ስለዚህን ፈራ እንደዚህም አለ "እነዚህ ቈላፋን(ያልተገረዙ) መጥተው እንዳይወጉኝና እንዳይሳለቁብኝ ሰይፍህን መዝዘህ ውጋኝ አለው፡፡"

## ክፍል 6

**ትግበራ፡** ምንም ተስፋ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ህይወት ምን አይነት ገፅታ ይኖራታል? ህይወት አላማ እና ትርጉም ከሌላት ተስፋ ከየት ይመጣል? በእነዚህ ሁለት ሰዎች መካከል ያለውን ሁኔታ በንፅፅር ስናስቀምጠው ሳኦል ተስፋ አድርጎ ይኖር የነበረው የዳዊትን ሞት ነበር፡፡ የዳዊት የህይወቱ ተስፋ ግን ህያው ከሆነው አምላኩ ጋር ባለው የጠበቀ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ (ሳሙኤል ቀዳማዊ 17፡36)

1. ተስፋዬን የማገኘው ከየት ነው ? ተስፋዬስ መመስረት ያለበት በምን ላይ ነው?_____

   ________________________________________________________________
2. ፍፃሜ እና ተስፋዬ በህይወቴ ውስጥ በምን መልኩ ነው እየተንፀባረቁ ያሉት?______

   ________________________________________________________________
3. እግዚአብሄር ለሁላችንም ያለውን የምስራች እንመልከት፡፡ በኤርሚያስ 29፡11 እንደዚህ የሚል ቃል ተፅፏል "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለ"ቁጥር 12 እና

13 ላይ እንደዚህ እያለ ያበረታታናል እናንተም___________________÷ ____________ ወደ እኔ _____________÷ እኔም ________________:: እናንተ _____________÷ ____________ ከሻችሁኝ ___________::

4. የእግዚአብሄር የተስፋ እና የፍፃሜ ቃልኪዳን በህይወቴ ላይ የሚጨምሩት ነገር ምንድነው?____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር በፀጋው ፍፃሜና ተስፋ ያለው ህይወት ስለሰጠኝ ክብር እና ምስጋናን አቀርብለታለሁ።:________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ማሰላሰል፡** መዝሙር 42 እና 43 አንድን ጥቅስ ሶስት ጊዜ ይደግሙታል። መዝሙር 42 ፡5 እና 11 እንደዚሁም መዝሙር 43፡5 በካርዳችሁ ላይ ፃፏቸው። የዳዊትን ህይወት እንደ ተዋጊ ጦረኛ እንደዚሁም ከሳኦል እየሸሸ እንዳለ ሰው አጥንታችሁታል። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ክፍሎች ስታነቡ መዝሙረኛው የወደቀን ሰው የውስጥ ጩኸት ይገልፃል ።መዝሙር 42 እና 43 በሙሉ አንብባችሁ አሰላስሏቸው። አንዳንድ ጊዜ ህይወታችን ሙሉ በሙሉ በጠላቶቻችን ቁጥር ስር እንደወደቀች ይሰማናል። ተስፋ ልንቆርጥ እና ልንጨነቅ እንችላለን። የዳዊትም ከዚህ የተለየ አልነበረም። ዳዊት የተስፋ መቁረጥ ተቃራኒው ወይንም መድኃኒቱ ህያው እና ታዳጊያችንን ለሆነው አምላክ ምስጋናን ማቅረብ እንደሆነ ገብቶታል። ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣውን ቃል በካርዳችሁ ላይ ፃፉ። ሀለዎቱን፣ጥበቃውን፣ሰላሙን፣እንደዚሁም ኃይሉን ለሚሰጠን አምላክ ለእግዚአብሄር ትልቅነት እና ክብር መስጠት የሚያስችሏችሁን ቃላቶች በካርዳችሁ ላይ ፃፏቸው።

# ትምህርት አራት

# እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ አምላክ ነው

## መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 1-13 ዳዊት እና እስራኤል

---

የትምህርት 4 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 4፡ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 1-13

- የዳዊት መንገስ
- ዳዊት እና ቤርሳቤህ
- ዳዊት እና ናታን
- ዳዊት እና አቤሴሎም

## መግቢያ

እነሆ በመጨረሻም ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሰ። ሂደቱ ረጅም እና አስቸጋሪ ነበር።የቀደሙት አመራሮች በዳዊት ምርጫ በአዳዲሶች መተካት አለባቸው።ይህ ሁኔታ ዳዊት ወደ ንግስናው ሳይመጣ በምድሪቱ ላይ ሰላም ሰፍኖ በነበረበት ጊዜ እንዴት እንደተከናወነ ተመልከቱ።

እንደ ሙሉ ሰው ፣እንደ አባት፣ እንደ ንጉስ ሲኖር የዳዊት ህይወት ምን ይመስላል? ዳዊት እንደ እግዚአብሄር ልብ የሆነ ሰው እንደነበር ተነግሮናል ነገር ግን ህይወትን በፍፁምነት አልኖረም።እንደ ሙሉ ሰው እና እንደ አባት በማጣት ፣በውድቀት የህይወት ውጣውረዶች ውስጥ አልፏል።በቤርሳቤህ ጉዳይ እግዚአብሄር ከዳዊት ጋር የነበረውን ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ያስከተለበትስ ችግር ምን ነበር?እግዚአብሄርስ ይቅር ብሎት ይሆን? ከእግዚአብሄር ጋር የነበረውስ ግንኙነት ታድሷል?የዳዊት ዙፋን ፀናለት?

የእግዚአብሄር ምህረት ብዙ ነው። ዳዊት በታላቅ መከራ ወስጥ እንኳን ሆኖ እንደዚህ አለ "ምህረቱ ብዙ ነውና........በእግዚአብሄር እጅ መውደቅ ይሻላል።" እግዚአብሄር መሃሪ ነው። የእግዚአብሄር ምህረት በሰው ሁኔታ እና ማንነት ላይ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሄር ማንነት ላይ ነው የተመሰረተው። ከእግዚአብሄር ባህሪያት አንዱ መሃሪ መሆኑ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሄር ምህረት የኃጢአትን ውጤት ያስቀር ይሆን? እግዚአብሄር ምህረትን የሚሰጠው ምህረት ስለሚገባን ወይንም ምህረት ስለወደደን አይደለም፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ተስማምተው የሚኖሩትን ይቅር ከማለት ውጪ አማራጭ የለውም። ስለሚወዳቸው ይምራቸዋል።

**ክፍል 1**

**ትምህርት፡** እስራኤል ያለንጉስ ናት ምክንያቱም ሳኦል ሞቷል። ዳዊት ስለሚወደው ጓደኛውና አባቱ ንጉስ ሳኦል መሞት ሰምቷል። በሳሙኤል ካልዕ 2፡1 ዳዊት ወዴት መሄድ እንዳለበት እግዚአብሄርን ጠየቀው። እግዚአብሄርም ወደ ኬብሮንን እንዲሄድ ነገረው። እርሱም ቤተሰቦቹን በመያዝ በዚያ ከተመ፤ ኬብሮንንንም ከተማው አደረጋት። የይሁዳ ሰዎችም በዚያ መጥተው በይሁዳ ላይ ንጉስ እንዲሆን ቀብተው አነገሱት። እስቲ ኬብሮንን በካርታችሁ ላይ ፈልጓት ኬብሮን ከቤቴልሔም በስተ ደቡብ እንደዚሁም ከሙት ባህር (ከጨው ባህር) በስተ ምዕራብ ትገኛለች።

በጣም ጠቃሚ የሆነው ነገር እስራኤል እና ይሁዳ ሁለቱም ተጠቅሰዋል ለዚህ ማሳያ የሚሆነን በሳሙኤል ቀዳማዊ ካልዕ 12፡4 ላይ "የይሁዳም ሰዎች መጥተው በይሁዳ ቤት ይነግሥ ዘንድ ዳዊትን በዚያ ቀቡት።" አስራሁለቱ ነገዶች የተከፋፈሉትን ምድር በሚያሳየው ካርታ ላይ የይሁዳን ሰፊ መሬት በካርታው ላይ በግልፅ መመልከት ይቻላል። ኬብሮንንም በዚሁ ካርታ ላይ በይሁዳ ምድር ውስጥ ታገኟታላችሁ። አሁን የተቀረው የእስራኤል ህዝብ በዳዊት ንጉስነት መስማማት ይገባቸዋል። እነዚህን ለሁለት የተከፈሉ ህዝቦች ማለትም ይሁዳ እና እስራኤል ከዳዊት የንግስና ዘመን ጀምሮ እስከ ሰለሞን የንግስና ዘመን ድረስ አንድ ሆነው ነበር።

ቀጥሎ ባሉት ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ የተከናወነው ነገር ዳዊትን ወደ ንግስና ዙፋኑ ማምጣት ነው። ይህ ሽግግር የቀድሞ መንግስት ባለስልጣናትን ፣ቤተሰቦችን ፣የጦር አዛዦችን፣እንደዚሁም ለቀድሞው ንጉስ ታማኝ የነበሩ ሰዎችን ማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም መግደል ያስፈልግ ነበር። የሳኦል ቁባቶች ከነበሩ ሴቶች ቁጥጥር ስር ያሉትን ማንኛውንም አይነት ይዞታዎች እንደዚሁም በአጠቃላይ ለአዲሱ መንግስት ስጋት የሆኑትን በሙሉ ማስወገድ ያስፈልጋል። የመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕን የመጀመሪያ ስድስት ምዕራፎች ስናጠና ስለዚህ ጉዳይ በጥልቀት እንመለከታለን።

**የቤት ስራ፡** መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 2፡4-7 ያለውን ክፍል እንብቡ።

**መልመጃ፡**

1. የኢያቢስ ዘገለአድ ሰዎች ምን አድርገው እንደ ነበር አስታውሱ (መጽሐፈ ሳሙኤል 31፡11-13)____________________________________________

   ____________________________________________________________

2. ለእነዚህ ሰዎች ዳዊት ሶስት መልዕክቶችን አስተላልፏል፡

   ሀ. ቁጥር 5፡____________________________________________________

   ለ. ቁጥር 6፡____________________________________________________

   ሐ. ቁጥር 7፡____________________________________________________

**ትምህርት፡** መልዕክቱ ለሳኦል ስላሳዩት ታማኝነት ምስጋና እና ስላደረጉት በጎነት ከእዚአብሄር ዘንድ በረከት እንዲሆንላቸው የበረከት ቃል የያዘ ነበር። እግዚአብሄር ጥብቅ የሆነውን ፍቅሩን እና ታማኝነቱን እንዲያሳያቸው ፀለየ። እርሱም በተመሳሳይ መልካም ሊያደርግ ቃል ገባ። ከአበረታታቸው በኋላ ይሁዳ ተስማምተው ቀብተው እንዳነገሱት ነገራቸው።

ይህ መልዕክት በስተ ሰሜን ያሉትን እስራኤላውያን የዳዊትን ንግስና እንዲቀበሉ ማሳሰቢያ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ተመራማሪዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ሰሜናዊው የእስራኤል ክፍል ለዳዊት ጥሪ ምላሽ የሰጠው ከአምስት አመት በኋላ እንደሆነ ይናገራሉ። ከአንደኛው አህጉር ወደሌላው አህጉር ምልዕክት በቅፅበት በሚተላለፍበት በአሁኑ አለም የእነዚህ ሰዎች ለዳዊት ምላሻቸውን ለመስጠት አምስት አመት መፍጀታቸው ሞኝነት ሊመስል ይችላል።

**መልመጃ፡** አሁን ችግር ተፈጥሯል አበኔር የሳኦል የጦር አዛዥ ነው። ኢያቡስቴ ደግሞ የሳኦል ልጅ ነው። አበኔር የሳኦልን ልጅ ኢያቡስቴን በተቀረው የእስራኤል ህዝብ ላይ አነገሰው የአባቱንም የሳኦልን መንግስት ሊያስቀጥል ፈለገ (ሳሙኤል ካልዕ 2፡8-11)።

1. በዳዊት ቤት እና በሳኦል ቤት ጦርነቱ ለረዥም ጊዜ ቀጠለ (ሳሙኤል ካልዕ 3፡1) ። በቁጥር አንድ ላይ ስለእነዚህ ቤቶች የተነገረን ምን ነበር?______________________

   ____________________________________________________________

2. ኢያቡስቴ አበኔርን በመክሰሱ ምክንያት አበኔር እርሱን ከድቶ ወደ ዳዊት ተቀላቀለ (ሳሙኤል ካልዕ 3፡6-11) ክሱ ምን ነበር? ______________________________

   ____________________________________________________________

**ትምህርት፡** አበኔር የቀረበበት ክስ የሳኦል ቁባት ከነበረችው ሪጽፋ ጋር ተኝተሃል የሚል ነው። ይህ ማለት ደግሞ የሳኦልን የንግስና ቦታ ልትወስድ አስበሃል ማለት ነው። በቁጥር 6 ላይ እንደምናነበው በሳኦል ቤት አበኔር እየበረታ ማለትም ስልጣኑ እየጨመረ ሄዶ ነበር። ስለዚህ አበኔር ለኢያቡስቴ ስጋት ሆኖበት ነበር። አበኔርም በዚህ ምክንያት እልህ ይዞት ከሳኦል ቤት ወደ ዳዊት ቤት ተመለሰ ዳዊትንም ከዳን (ሰሜን) እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ዳዊት በእስራኤል ላይ እንዲነግስ መስራት ጀመረ።

**መልመጃ፡** ሳሙኤል ካልዕ 3

1. አበኔር እስራኤልን በዳዊት ግዛት ስር ለማድረግ ወሳኝ ሰው ነበር (ከ ቁጥር 12 ጀምሮ)። ነገር ግን ዳዊት ከአበኔር የፈለገው ምን ነበር(ቁጥር 13-16)?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

2. እዮአብ የዳዊት ሰራዊት አዛዥ ነበር። በምዕራፍ 2 እንደምናነበው አበኔር የእዮአብን ወንድም ገድሎ ነበር። በመዕራፍ ሶስት መጨረሻ ላይ እዮአብ የወንድሙን ሞት ለመበቀል አበኔርን እንደገደለው እናነባለን። ዳዊት ግን የአበኔርን ሞት ለመበቀል አበኔርን አልገደለውም። የተቀባው ዳዊት ግን አሁንም ደካማ ይመስላል ዛሬም እግዚአብሄርን ይጠይቃል። በቁጥር 39 ላይ ምን ነበር እግዚአብሄርን የጠየቀው?

   ______________________________________________________________

3. በሳሙኤል ካልዕ 4 ላይ የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ እንደሞተ እና በምዕራፍ 5 ላይ ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ እንደነገሰ እንመለከታለን።" በቁጥር 2 ላይ "አንተ ሕዝቤን እስራኤልን ________________________________ ፥ በእስራኤልም ላይ __________________ትሆናለህ ብሎህ ነበር" አሉት።
4. በቁጥር 6 መሰረት በእየሩሳሌም ይኖር የነበረው ማን ነበር?__________.እየሩሳሌም __________________በሚባለው ተራራ ላይ የተመሰረተች ከተማ ናት።
5. ኢያቡሳዊያን ዳዊት የፅዮንን ምሽጎች አልፎ እየሩሳሌምን ሊቆጣጠር አይችልም የሚል እምነት ነበራቸው። ቁጥር 7 ምን ይነግረናል? ______________________
6. በቁጥር 9-16 ስለዳዊት ምን እንማራለን? ____________________________

   ______________________________________________________________

7. በሳሙኤል ካልዕ 6፡14-15 ባለው ክፍል ላይ የቃልኪዳኑ ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ሲገባ ስለነበረው ደስታ ይነግረናል፡፡ ይህንን ታላቅ በአል ሊገልፁልን የሚችሉ ቃላቶች ምን ነበሩ?______________________________________________

______________________________________________________________

8. በምዕራፍ 7፡2 ዳዊት የተመለከተው ነገር ምን ነበር? _____________________

9. ቁጥር 5-6 ላይ የእግዚአብሄር ቃል ወደ ነቢዩ ናታን መጣ፡፡ ይህን ክፍል አንብባችሁ እግዚአብሄር ለዳዊት ሊያስተላልፍለት የፈለገውን መልእክት በራሳችሁ ቃል ፃፉ? _________________________________________________

______________________________________________________________

10. ናታን መልዕክቱን አስተላልፎ ከጨረሰ በኋላ "ዳዊት በእግዚአብሄር ፊት ተቀመጠ ቁጥር 18 ፡፡" ዳዊት ስለ እግዚአብሄር የተናገራቸው ጥቂት ነገሮች ምንድናቸው (ከቁጥር 22 ጀምሮ)?____________________________________________

______________________________________________________________

11. ዳዊት በተዳጋጋሚ አገልጋይ የሚለውን ቃል እንደተጠቀመበት ተመልከቱ፡፡ ምንም እንኳን ንጉስ ቢሆንም ዳዊት ግን እራሱን የሚቆጥረው የእግዚአብሄር አገልጋይ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ አመለካከቱ እስራኤልን ሲመራ የሚፈጥረው ልዩነት ምን ሊሆን ይችላል? ______________________________________________

______________________________________________________________

12. የዳዊት ንግስና በድል የተሞላ ነበር (ቁጥር 8 እና 10) በእነዚህ ምዕራፎች መካከል ሌሎች አዳዲስ ሰዎችን እንተዋወቃለን፡፡ በሳሙኤል ካልዕ 9፡1 ላይ ዳዊት የጠየቀው ጥያቄ ምን ነበር?__________________________________________________

______________________________________________________________

13. ሲባ የተባለው የሳኦል ቤት አገልጋይ ወደ ዳዊት አመጡት፡፡ በቁጥር 3 ላይ ይህ አገልጋይ ለዳዊት ምን ነገረው?________________________________________

______________________________________________________________

14. ሜሚፊቦስቴን ወደ ዳዊት አመጡት (ቁጥር 6)፡፡ ዳዊት ለሜምፊቦስቴ ምን ቃል ገባለት? እንዴትስ ነው ያስተናገደው (ቁጥር 7-13__________________________

***ማጠቃለያ፡*** የዳዊት መንግስት የተመሰረተው በእግዚአብሄር ነው ። የዚህ መንግስት አመሰራረት እንደምናስበው ቀላል እና በአንድ ጀንበር የተከናወነ አልነበረም። ቀጥሎ ባለው ትምህርት ዳዊትን በንግስና ዙፋኑ ላይ እንዳለ ትተን ሌሎችን ታሪኮች መመልከት እንጀምራለን። እግዚአብሄር የሚያስፈልገውን ሁሉ ሰጥቶታል ። ዘወትር የሚጠይቀው ጥያቄ አንድ ነው። እርሱም “እስከዚህ ያደረስከኝ እኔ ማነኝ ቤቴስ ምንድነው?”የሚል ጥያቄ ነው። የቃልኪዳኑ ታቦት አሁን በእየሩሳሌም ነው። በምድሪቱ ላይም ሰላም ሰፍኗል። ጠላቶቻቸው በሙሉ ተሸንፈዋል። እግዚአብሄርም ዳዊትን በህዝቡ ላይ የራሱ ንጉስ ህዝቡን ደግሞ የራሱ ህዝብ አድርጓል። እርሱም አምላካቸው ነው! የዳዊት የቀን ተሌሊት ትኩረቱ እና ሃሳቡ እግዚአብሄር ለዘላለም በህዝቡ ላይ ይከብር ዘንድ ነው። ”እንዴት ታላቅ እምላክ ነህ!እንደ አንተ ያለ ማንም የለም አምላክ አንተ ብቻ ነህ……..።” የዳዊት ፀሎት የእናንተም ፀሎት ይሁንላችሁ። እርሱ የእኛ አምላክ እኛም ደግሞ የእርሱ ህዝቦች ነን። ክብር እና ምስጋና ለእግዚአብሄር ለዘላለም ይሁን።

**<u>ክፍል 2</u>**

***መግቢያ፡*** ልክ እንደ ዳዊት እና እንደ ጎልያድ ታሪክ የዳዊት እና የቤርሳቤህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታዋቂ ታሪክ ነው። ይህንን ታሪክ የሚነግረን በሳሙኤል ካልዕ 11-12፡25 ያለው ክፍል ነው። እግዚአብሄር ዳዊትን በሚያስፈልገው ነገር በሙሉ ባረከው። አገኛለሁ ወይንም ይሆንልኛል ብሎ ካሰበው በላይ እግዚአብሄር አድርጎለታል። እግዚአብሄር እስራኤልን በጠላቶቻቸው ሁሉ ላይ ድልን ሰጣቸው። እግዚአብሄርም ስለህዝቡ ይዋጋል በዚያን ጊዜ ህይወትም ጊዜውም መልካም ነበር።

**የቤት ስራ፡** *መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 11፡1-27 ያለውን ክፍል አንብቡ።*

- ሰዎቹ እነማን ነበሩ?
- ምን ስህተት ተፈጠረ?
- ድብብቆሹ ምንድነው?
- እዮአብ ለዳዊት የሰጠው መረጃ ምን ነበር?

**መልመጃ፡**

1. ይህ ወቅት የትኛው የዓመቱ ክፍል ነው (ቁጥር 1)?____________________በዚህ የዓመቱ ክፍል ምን ተፈጠረ?_______________________________________
2. ንጉሱ_________________እና አገልጋዮቹን______________________ላካቸው፡፡
3. በቁጥር 1 ላይ ስለዳዊት የተነገረን ምንድነው?___________________________
4. ዳዊት ጊዜውን እየተጠቀመ ነበር፡፡ ዳዊት የገጠመው ፈተና ምን ነበር (ቁጥር 2)?_ _________________________________________________________________
5. ቤርሳቤህ ማናት (ቁጥር 3)? ስለ እርሷ ምን እንማራለን?____________________ _________________________________________________________________
6. በቁጥር 4 ላይ የዳዊት ትእዛዝ ምን ነበር?
7. ቤርሳቤህን ወደ ዳዊት አስገቧት ዳዊትም ከእርሷ ጋር ተኛ እቤቷ ከገባች በኋላ ምን የሚል መልእክት ላከችበት (ቁጥር 5) ______________________
8. በቁጥር 6 ላይ ዳዊት ለእዮአብ ኦርዮንን ወደ እየሩሳሌም እንዲልክለት አዘዘው፡፡ ኦርዮንንም በጦር ሜዳ ነገሮች እንዴት እየሄዱ እንዳለ ስለ ወታደሮቹ ከጠየቀው በኋላ ኦርዮንን ምን እንዲያደርግ ነገረው (ቁጥር 7-8)?______________________ _________________________________________________________________
9. ቁጥር 9 "ነገር ግን" በሚል ቃል ይጀምራል፡፡ ሁሉም ነገር ልክ ዳዊት እንዳቀደው ተከናወነለት፡፡ ነገር ግን ምን?_______________________________________
10. በቁጥር 10 እና 11 ላይ ዳዊት ኦርዮንን ለምን ወደ ቤት እንዳልሄደ ሲጠይቀው የኦርዮን ምላሽ ምን ነበር?____________________________________________
11. ዳዊትም ተስፋ በመቁረጥ እንደገና ተጨማሪ ቀን እንዲቆይ አደረገው፡፡ ኦርዮንንም እራት ጋበዘው እስኪሰክርም ድረስ እንዲጠጣ አደረገው፡፡ እዚህም ስፍራ ላይ ***ነገር ግን*** የሚል ቃል አለ እዚህስ ጋር "ነገር ግን" ምን ሆነ (ቁጥር 13)?____________
12. የዳዊት የመጀመሪያው እቅዱ ከሸፈበት፡፡ ስለዚህም ኦርዮንን ደብዳቤ አስይዞ ወደ ኤልያብ ላከው፡፡ ከዳዊት የተላከው ደብዳቤ ምን የሚል ነበር?________________ _________________________________________________________________ _________________________________________________________________
13. በቁጥር 16-17 ባለው ክፍል ኦርዮን ምን ሆነ?___________________________

14. እዮአብ ለዳዊት የላከው መልእክት ምን ነበር (ቁጥር 18-21)?_______________

___________________________________________________________

15. መልእክተኛውም እዮአብ እንደላከው ለዳዊት መልእክቱን አደረሰ፡፡ዳዊትም መልእክቱን ተቀበለ ወደ ዳዊት የመጣው መልእክት ምን ነበር (ቁጥር 25)?_____

16. የዚህ የታሪክ ክፍል የተጠናቀቀው እንዴት ነበር ቁጥር (26-27)?_____________

___________________________________________________________

17. በምዕራፍ 11 ማለቂያ ላይ _________________________እንደሆነ ተነግሮናል፡፡

**ገለፃ፡** ጊዜ ወስዳችሁ ታሪኩን በማንበብ ምን እንደተፈጠረ ግለፁ፡፡ ይህ የታሪክ ክስተት እስኪከሰት ድረስ ዳዊት ጥሩ ምሳሌነት ያለው ንጉስ ነበር፡፡ በሳሙኤል ቀዳማዊ 13፡14 ላይ “እግዚአብሄር በፈቃዱ መሰረት የሚሄድ እንደልቡ የሆነ ሰው እንዳገኘ እና እርሱንም በእስራኤል ላይ ንጉስ እንዲሆን እንደሾመው ይናገራል፤ ይህ ሰው ደግሞ ዳዊት ነበር፡፡ አሁን ታዲያ ይህ ሰው ያደረገው ነገር ምንድነው? ይህን ታሪክ ስትሰሙ ምን አይነት ስሜት ተሰማችሁ?____________________________________________________

___________________________________________________________

ስለፈተና ከዚህ ክፍል የምንማረው ምንድነው? ዳዊት ወቅቱን ያውቅ ነበር እራሱንም በቤርሳቤህ እንዲፈተን አጋልጦ ሰጠ፡፡ የእስራኤል ጀግና እና ንጉስ በእርግጥ ይህንን አደረገ? ጎልያድን የዘረረው፣ሳኦል ከግድግዳ ጋር ሊያጣብቀው ሲል በእግዚአብሄር እርዳታ ያመለጠው፣ለሞት ሲያሳድደው የነበረውን ሳኦልን አግኝቶ እግዚአብሄር የቀባው ላይ እጄን አላነሳም በማለት ያለፈው………. እግዚአብሄር ሁሉን የሰጠው ዳዊት!?!? ለምን የእርሱ ያልሆነችውን ሴት የኦርዮንን ሚስት ተመኘ? ምኞቱም ከእርሷ ጋር እንዲያመነዝር አደረገው፡፡ በእርግጥ ዳዊት የሚስት እና የቁባት ችግር ነበረበት? መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 5፡13 ስለሚስቶቹ እና ስለቁባቶቹ ይነግረናል፡፡ እና ዳዊት ሆይ ምን ነካህ?____________________

___________________________________________________________

አንደኛው ስህተት ሌላኛውን ወለደ ዳዊት ኃጢአቱን ለመሸፈን ፈለገ፡፡ ስለዚህ ኦርዮን ከሚስቱ ከተለየ ረጅም ጊዜ ስለሆነው ከሚስቱ ጋር ለመተኛት እንደሚጓጓ እርግጠኛ ሆኖ ነበር፡፡ ዳዊት ኦርዮንን ከጦር ሜዳ ወደ እየሩሳሌም እንዲመጣ ያደረገው፡፡ይህ እቅዱ አልሆን ሲለው ሌላ ሃሳብ አሰበ ኦርዮንን አጠጥቶ ካሰከረው ከሚስቱ ጋር እንደሚተኛ አሰበ፡፡ነገር ግን አሁንም ዳዊት እንዳሰበው አልሆነለትም፡፡ ስለዚህ ዳዊት ለኦርዮን ሞት ደገሰለት፡፡ ኦርዮንንም የራሱን

የሞት ፍርድ የተወሰነበትን ደብዳቤ ይዞ እንዲሄድ አደረገው። የኦርዮን ሞት የኃዘን ጊዜ ሲያበቃ ዳዊት ቤርሳቤህን ወደ ቤተመንግስቱ አመጣት ሚስቱም አደረጋት ልጅም ወለደችለት።

<u>ክፍል 3</u>

**ትምህርት፡** እስቲ ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን ታሪክ እንመልከት። ከእነዚህ ተከታታይ ትምህርቶች ውስጥ የመጀመሪያው የሆነው *"የእግዚአብሄር እቅድ የሆነው የእኛ ምርጫ"* ።ዘፍጥረት 1 እና 2 እግዚአብሄር ፍጥረታትን ፈጥሮ ለአዳም እና ለሔዋን እንደሰጣቸው ይነግረናል። እግዚአብሄር የኤደን ገነትን " ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።" ከሚል ትዕዛዝ ጋር ሰጠው። ነገር ግን የታሪኩን ፍፃሜ ሁላችንም እናውቀዋለን። እግዚአብሄር የፈቀደላቸውን ትተው አይኖቻቸው እግዚአብሄር ወዳልፈቀደላቸው በመመልከት ፈተና ውስጥ ወደቁ። በኤደን ገነት ውስጥ ሁሉም ነገር መልካም ነበር ከዚያ የተሻለ ነገር ማግኘት አይችሉም ነበር እግዚአብሄር በቂ ነገር አጥቶአቸው ነበር።

እንደሚታወቀው ኃጢአት ከማድረጋቸው በተጨማሪም ለመደበቅ ያደረጉትን ሙከራ ታስታውሱታላችሁ። ለሰሩትም ኃጢአት አንዱ በአንዱ ሲያሳብብ ነበር። ነገሩን ሊደብቁ ሞክረዋል። እርቃናቸውን እንዳሉ በማወቃቸው የበለስ ቅጠል ወስደው እርቃናቸውን ሊሸፍኑ ሞክረዋል። የሰሩትን በደል ለመሸፈን ሌላ በደል እየጨመሩ ሔዱ። ነገር ግን ሊደበቁት የሚጣጣሩት አምላክ በምንም መልኩ ከእርሱ ሊሰወሩ አይችሉም። ኃጢአት ከእግዚአብሄር እንዲሁም ከሰዎች እንድንሸሽ የደርገናል። ኃጢአት ጥፋታችንን እና በደላችንን እንዳንቀበል ያደርገናል።

እግዚአብሄር ሲመለከተን ሊቀጣን ሳይሆን ሊመልሰን ነው። ቀጥሎ የሆነው ነገር ቅጣት ሳይሆን ኃጢአታቸው ያስከተለው ውጤት ነው። ለአዳም እና ለሔዋን እግዚአብሄር የኃጢአታቸው ውጤት ሞት እንደሚያስከትልባቸው ነግሯቸዋል ታሪኩ እዚህ ላይ አያበቃም። እግዚአብሄር ፍቅሩን አረጋግጦላቸዋል። አዳኝ እንደሚልክላቸው ፣በእነርሱ ምትክ የሚሞትላቸው የዘላለም ህይወት የሚሰጣቸው ከእግዚአብሄር ጋር ለዘላለም እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው አዳኝ እንደሚልክላቸው ተስፋ ሰጥቶአቸዋል። ወደ ዳዊት እና ቤርሳቤህ ታሪክ ስንመለስም ኃጢአት ያመጣውን ውጤት እና በነብዩ ናታን በኩል እግዚአብሄር ዳዊትን ለመታደግ ያደረገውን የፍቅሩን ስራ እንመለከታለን።

**የቤት ስራ ፡** ሳሙኤል ካልዕ 12፡1-19 ያለውን ክፍል አንብቡ።

***መልመጃ:***

1. ከቁጥር 1 እስከ 4 ባለው ክፍል ውስጥ ነብዩ ናታን ለዳዊት አንድ ታሪክ ነገረው። እስቲ ይህንን ታሪክ በራሳችሁ ቃል ግለፁት። ናታን የነገረው ታሪክ ምንድነው? _
   ____________________________________________________________
2. ዳዊት ለተነገረው ታሪክ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 5)?________________
3. ዳዊት በታሪኩ ላይ ለተነገረው ሰው ለሰራው ኃጢአት ይገባዋል ያለው ፍርድ ምን ነበር ከቁጥር 5 እስከ 6?________________________________________________
   ____________________________________________________________
4. ከዚያም ናታን ለዳዊት እንደዚህ አለው , "_______ _________ _________ ___!"
5. ናታንም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር ምን እንዳለው ነገረው።ከቁጥር 7 እስከ 8

   ሀ.__________________________________________________________

   ለ.__________________________________________________________

   ሐ. _________________________________________________________

   መ.__________________________________________________________
6. ቁጥር 8 እንዴት ነው የሚያልቀው?____________________________________
7. በቁጥር 9 ላይ ያለው ታላቁ ጥያቄ ምንድነው?______________________________
8. እግዚአብሄር እንደዚህ ያለ ይመስላል "ዳዊት እስቲ ያደረከውን ነገር በክለሳ መልክ እንመልከተው" በቁጥር 9 ላይ ያለው የናታን ቃል ምን የሚል ነበር?___________
   ____________________________________________________________
9. ዳዊት የሰራው ኃጢአት በእግዚአብሄር ፊት የሰራው ክፋት ያስከተለበት ነገር ምን ነበር (ቁጥር 10)? _____________________________________________
10. ቁጥር 11 እና 12 ለጆሮ የሚከብዱ ቃላት ናቸው። እግዚአብሄር ለዳዊት ኃጢአቱ የሚያስከትልበትን ነገር ነገረው። በዳዊት ላይ መከራ ሊመጣበት ነው። ምን ነበር ሊሆንበት ያለው?_______________________________________________

*ማስታወሻ፤* የዚህን ታሪክ ፍፃሜ በሚቀጥለው ክፍል እንመለከታለን።

11. በቁጥር 13 ላይ ዳዊት ለናታን የተናዘዘው ነገር ምን ነበር?________________
12. በዚሁ ቁጥር 13 ላይ ናታን ወዲያውኑ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?____________
13. በቁጥር 14 ላይ በመጨረሻ ናታን ከዳዊት ከመለየቱ በፊት ምን ነበር የነገረው?___

    ________________________________________________________

14. ከቁጥር 15-19 ያለው ክፍል ወዲያውኑ ስለሆነው ኃዘን እና ምሬት ይነግረናል፡
    ሀ. በተወለደው ልጅ፡______________________________________
    ለ. በዳዊት፡___________________________________________
    ሐ. በዳዊት ቤት ሽማግሌዎች፡፡_______________________________
    መ. በአገልጋዮቹ፡________________________________________

**ገለፃ፡** ምን አይነት የሃዘን ቀን ነው፡፡ሁሉ የሞላለት ንጉስ አሁን ክብሩ እና ሞገሱ ተገፈፈ አሁን ስለ ህፃኑ ነፍስ እግዚአብሄርን ይለምን ጀመር፡፡ ምግብም አልበላም አለ፤ በንጉሳዊ አልጋው ላይም ከመተኛት ይልቅ መሬት ላይ መተኛትን መረጠ እራሱንም አጎሳቆለ፡፡ በቤቱ ያሉ ሽማግሌዎችም በምንም መልኩ ሊያሳምኑት አልቻሉም አገልጋዮቹንም አልሰማም አለ ስለዚህም አገልጋዮቹ የልጁን መሞት እንዴት እንደሚነግሩት ሲያስቡ ፈሩ፡፡ ዳዊት ግን እግዚአብሄር አደርጋለሁ ያለውን እንዳደረገ በልቡ አውቋል፡፡

ስለዚህ አባት፣ ስለ ህፃኑ እናት እና ስለ ህፃኑ ልባችን ያዝናል፡፡ እግዚአብሄር እንደጨከነባቸውም ልናስብ እንችላለን፡፡ እግዚአብሄር ምህረት ማድረጉ ካልቀረ ልጁንም በህይወት እንዲኖር ማድረግ አለበት ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡ ናታን መጣ እግዚአብሄርም ዳዊትን ኃጢአቱን እንዲያምን አደረገው “ ያ ሰው አንተ ነህ” ዳዊትም ኃጢአቱም ቅጣቱንም ወሰደ፡፡ የታረደችንም በግ አራት እጥፍ መክፈል አለበት ምክንያቱም ድርጊቱን የፈፀመው ያለርራሄ ነውና፡፡ ናታን ሌሎችም መርዶዎች ነገረው፡፡

1. ከቤትህ ሰይፍ አይጠፋም
2. የቅርብህ በሆነ ሰው እፍረት በአደባባይ ይሆንብሀል
3. የተወለደውም ህፃን ይሞታል

እግዚአብሄር ዳዊትን ኃጢአቱን እንዲናዘዝ አደረገው፡፡ ”እግዚአብሄርን በድያለሁ” ዳዊት እግዚአብሄርን እንደበደለ ግልፅ ነው ከሁሉም በላይ ግን የዳዊት በደል ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት አበላሽቶበታል፡፡ በእግዚአብሄር እና በዳዊት መካከል ባለው ግንኙነት መካከል

የተፈጠረው ችግር ዳዊት እግዚአብሄርን እንደበደለ አለመናዘዙ ይሆን? የግንኙነታቸው መበላሸት በሁለቱ መካከል መለያየትን ይፈጥራል። እግዚአብሄርም ዳዊትን ኃጢአት በማድረጉ ምክንያት ዋጋ እንደሌለው እና እንደማይጠቅም ሳይሆን ኃጢአቱን ተናዞ ወደእርሱ እንዲመለስ ለማድረግ ይቅር እንደተባለ ልጅ ግንኙነታቸው እንዲታደስ  ነበር ነቢዩን የላከበት።

<u>ክፍል 4</u>

**መግቢያ፡** በሳሙኤል ካልዕ 12፡11-12 ባለው ክፍል ውስጥ ነቢዩ ናታን ዳዊትን የሚያሳፍር ነገር ከገዛ ቤቱ እንደሚወጣ ተናግሮታል። ይህ ታሪክ የሚጀምረው በሳሙኤል ካልዕ 13 ሲሆን ፍፃሜው ደግሞ ምዕራፍ 18 ላይ ነው።አሁን ታሪኩን በዝርዝር አናጠናውም እናንተ በግላችሁ ይህንን ክፍል ብታጠኑት ምን እንደተፈጠረ መረዳት ትችላላችሁ ስለዚህ ጊዜ ወስዳችሁ አንብቡት። ታሪኩ ሲጀምር ሶስቱን የዳዊትን ልጆች ያሳተፈ ነው። የዳዊት የበኩር ልጅ አምኖን፣በዳዊት አባትነት ብቻ የሚገናኙ ከሌላ እናት የምትወለድ የአምኖን እህት ትእማር፣እንዲሁም ከሌላ እናት የሚወለድ ወንድማቸው አቤሴሎም ናቸው።

**የቤት ስራ፡** መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ  13፡1-22 ያለውን ክፍል አንብቡ።

**መልመጃ፡**

1. ከቁጥር 1-2 የተፈጠረው ችግር ምንድነው?______________________________
2. ከቁጥር 3-9 ኢዮናዳብ የዳዊት የወንድሙ ልጅ ሲሆን የአምኖን የአጎቱ ልጅ ነው። አምኖንን ምን አይነት ምክር መከረው?__________________________________

   ____________________________________________________________
3. ከቁጥር 9-19 አምኖን እህቱን ትእማርን ከደፈራት በኋላ ከቤት አስወጣት። አፍራ እና ተዋርዳ ሄደች።
4. ከቁጥር 20-22 አቤሴሎም ምን እንደተፈጠረ እና በእህታቸው ላይ አምኖን ምን እንዳደረገባት ከትእማር ተረዳ ከዚያስ ምን አደረገ?________________________

   ____________________________________________________________
5. አቤሴሎም ለወንድሙ ለአምኖን ምንም አላለውም ነገር ግን አቤሴሎም ምን ሆነ?

   ____________________________________________________________
6. ዳዊት ስለተፈጠረው ነገር ሰምቷል በጣም ተቆጥቶ እንደነበርም ክፍሉ ያናገራል። አምኖን ያደረገው ነውር አቤሴሎምን ምን እንዲያስብ አደረገው?_______________

7. አቤሴሎም በወንድሙ ላይ ጥላቻ አደረበት፡፡ ከቁጥር 23 — 33 ባለው ክፍል ውስጥ ምን ተፈጠረ?________________________________________________

__________________________________________________________________

8. ዳዊት የተቀበለው መልእክት ምን ነበር (ቁጥር 30)?_________________________
9. ኢዮናዳብ ዳዊትን ልጆቹ ሁሉ እንዳልሞቱ አረጋገጠለት ቁጥር 3-5 ያለውን ክፍል ተመልከቱ፡፡____________________________________________________

__________________________________________________________________

አቤሴሎም ወደእናቱ ቤተሰቦች ወደአያቶቹ ሃገር ሸሽቶ ሄደ፡፡(ዜና መዋዕል3፡2) አቤአሴሎም በአያቶቹ ቤት ለሶስት አመት ያህል ተቀመጠ ዳዊትም ኃዘኑን አረስቶ ልጁ አቤሴሎም ናፈቀው፡፡

**ትምህርት፡** እዮአብ የእስራኤል ሰራዊት መሪ ንጉስ ዳዊት አቤሴሎም እንደናፈቀው አወቀ፡፡ አቤሴሎም ወንድሙን እንደገደለ አምኖን ደግሞ ይህን አይነት ፍርድ ይገባው እንደነበር ያውቃል፡፡ በምዕራፍ 14 ላይ እንደምንመለከተው ዳዊት እዮአብን ወደ ጌሹር አቤሴሎምን ወደ እየሩሳሌም እንዲያመጣው ላከው፡፡ ይሁን እንጂ አቤኤሎም ወደ እየሩሳሌም ሊመጣ ወደራሱ ቤት እንዲሄድ እንጂ ወደ ቤተመንግስቱ ንጉሱ ያለበት ስፍራ እንዲገባ አልተፈቀደለትም ነበር፡፡

**መልመጃ፡**

1. ከቁጥር 25-26 ባለው ክፍል ውስጥ የአበሴሎም ገፅታ ምን ይመስል እንደነበር ተነግሮናል ለመሆኑ ስለእርሱ የተገለፀው ምን ነበር?__________________________

__________________________________________________________________

2. በቁጥር 27 ላይ ስለቤተሰቡ የተነገረን ምንድነው? __________________________

__________________________________________________________________

**ቅኝት፡**አቤሴሎም በአባቱ በዳዊት ላይ አመፅን ያስብ ጀመር፡፡ ሰዎችን ወደ ራሱ ለመሳብ ስነልቦናዊ አካሄዶችን ይጠቀም ነበር፡፡ የአባቱን የዳዊትን አገዛዝ ያጣጥል እና ወደ ዳዊት ለፍርድ የሚመጡትን ሰዎች በመያዝ ችግራቸውን ቀርቦ ይሰማ ነበር ፡፡ መልኩን እና ውበቱን በመጠቀም የእስራኤልን ህዝብ ልብ ሰረቀ፡፡ የተከታዮቹም ቁጥር እየጨመረ መጣ በዚህን ጊዜ ዳዊት ከአቤሴሎም ለማምለጥ ለህይወቱ ሰግቶ ከእየሩሳሌም እስኪሸሽ ድረስ አቤሴሎም በረታበት፡፡ ዳዊት ከተማይቱን ለቅቆ ወጣ አቤሴሎምና እና የእርሱ ተከታዮች ከተማይቱን

ተቆጣጠሯት፡፡ አኪጦፌል የሚባለው የአቤሴሎም አማካሪ አቤሴሎምን ከአባቱ ከዳዊተ ቁባቶች ጋር ህዝቡ ሁሉ ሊመለከት በሚችልበት በሰገነቱ ላይ ድንኳን ተተክሎለት በዚያ አብሯቸው በአደባባይ እንዲተኛ አባቱንም እንዲያዋርደው መከረው፤ ሳሙኤል ካልዕ 16፡20-22፡፡ የአኪጦፌል ምክር ኩሲ በሚባለው በስውር የዳዊት መልዕክተኛ በሆነው ሰው ምክር ተገለበጠች፡፡ ሳሙኤል ካልዕ 17፡14 እንደዚህ ይላል "የአርካዊው የኩሲ ምክር ከአኪጦፌል ምክር ይሻላል አሉ። እግዚአብሔርም በአቤሴሎም ላይ ክፉ ያመጣ ዘንድ እግዚአብሔር መልካሚቱን የአኪጦፌልን ምክር እንዲበትን አዘዘ።"

ዳዊትም የአቢሴሎምን እቅድ ሰማ በጦር አዛዦቹ በእዮአብ ፣አቢሳ እና ኢታይ ስር ምድብ ጦር አደራጀ፡፡ ወደ ውጊያው ሲንቀሳቀሱም ዳዊት እንዲበረቱ ነገር ግን የብላቴናውን የአቤሴሎምን ነፍስ እንዳያጠፉ አሳሰባቸው፡፡ የአቢሴሎም ሞት ግን እጅግ ዘግናኝ ነበር፡፡ሳሙኤል ካልዕ 18፡9-17 እንደዚህ የሚል ታሪክ ይነግረናል፡፡ በቁጥር 33 ላይ ስለ ልጁ ስለ አቤሴሎም ያለቀሰውን ለቅሶ እናገኛለን፡፡

## ትምህርት አምስት

# እስራኤል በእግዚአብሄር ላይ ኃጢአትን አደረች

### መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 20 - መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 17 ሰለሞን እና ነገስታቶቹ

---

የትምህርት 5 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 5፡ ሳሙኤል ካልዕ 20-መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 17

- መዝሙረ ዳዊት 18
- እግዚአብሄር ፅድቃችን
- መዝሙረ ዳዊት 18
- የሰለሞን መንግስት ተመሰረተች
- ጥበብ እና እውቀት
- ሁለት እናቶች አንድ ህፃን
- የግንባታው እቅድ
- የነገስታት ውድቀት

## መግቢያ

የዳዊት የንግስና ዘመን በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ወደር የማይገኝለት ነው። ዳዊትን ልጁ ሰለሞን ተክቶት ነገሰ። ሰለሞን የንግስና ዘመኑን የጀመረው እንደ አባቱ እንደ ዳዊት አካሔዱን ከእግዚአብሄር ጋር በማድረግ ነበር። ህዝቡን ከእግዚአብሄር በተሰጠው ጥበብ ይመራ ነበር። የሰሎሞንን መንግስት ውድቀት የጀመረበትን እንደዚሁም ከእርሱ በኋላ የነገሱት ነገስታት የሄዱበትን መንገድ ልብ በሉ። እስራኤል በአመፅ እና ባመታዘዝ የተጓዘበት ይህ ወቅት ነበር። እስራኤልም ለሁለት ተከፈለች በስተ ሰሜን እስራኤል በስተ ደቡብ ያለው ደግሞ ይሁዳ ተብሎ ለሁለት ተከፈለ። እስራኤል እንዴት እግዚአብሄርን እንደተወ እና እግዚአብሄርም እስራኤልን ከፊቱ እስኪያጠፋቸው ድረስ እንዴት እንደተዋቸው እንማራለን።

ህዝቡ በእግዚአብሄር መንገድ በማይሄዱ ነገስታቶች ምክንያት ምንኛ ታላቅ ጥፋት እንዳገኘው እግዚአብሄር ደግሞ በዚህ ምክንያት ህዝቡን በህዝቡ ላይ በመጣው ቅጣት ምክንያት በምህረቱ ህዝቡን በባርነት ከያዙት ህዝቦች እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው እንመለከታልን። እግዚአብሄርም በስሙ የተጠራውን የሚወደውን ህዝብ ለማቅናት ይቀጣል ይገስፃል ህዝቡንም መልሶ ገንዘቡም ያደርጋል።

**ክፍል 1**

***መግቢያ፡*** *ሳሙኤል ካልዕ* 20-24 *ሌሎችም ተጨማሪ ታሪኮች ተዘግበው ይገኛሉ፡፡ ዳዊት ወደ እየሩሳሌም ተመልሶ መንግስቱን እንደገና አቋቋሞ ወደ ንግስናው ተመለሰ፡፡ ህዝቡ አምጿል፣ረሃብ ምድሪቱን ጠርንታል ፣እስራኤልም ከፍልስጥኤም ጋር ጦርነቷን ቀጥላለች፡፡ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ዳዊት እግዚአብሄርን ከጠላቶቹ ስለታደገው እያመሰገነ ይዘምራል ሳሙኤል ካልዕ* 22፡፡ *እነዚህ የዝማሬ ቃሎች በመዝሙረ ዳዊት* 18 *ውስጥም በድጋሚ ተጠቅሰዋል፡፡*

*ይህ መዝሙር መልካም የሚሆንልን ጠላቶቻችንን ለይተን አውቀን እንደሆነ ነው፡፡ የዳዊት ጠላቶች ከሳኦልም ከፍልስጥኤማውያንም በላይ ናቸው፡፡ ከስልጣን ሊያስወግደው የገዛ ልጁም ያደረገውን የጠላትነትን ስራ በዚህ ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ ዳዊት የገጠመው ጠላት ፍርሃት፣ጭንቀት፣ውርደት፣እንዲሁም ፈተናን ያጠቃለለ ነበር፡፡ ጠላቶቹ በአካል ሰይፍና ጦር ይዞ ከሚገጥማቸው የሚታዩ ስጋ ለባሽ ጠላቶች የበረቱ ነበሩ፡፡ ጠላቶቹ የክፉው ሰራዊቶች ነበሩ፡፡ ዳዊትን ያዋረዱት ክፉዎች ናቸው ዛሬም የእኔ እና የእናንተ ጠላቶች ተመሳሳይ ናቸው፡፡*

***የቤት ስራ፡*** *ወደ መልመጃው ከመሄዳችሁ በፊት እስቲ በህይወታችሁ ውስጥ የለያችኋቸውን ሁለት ወይንም ሶስት ጠላቶቻችሁን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቧቸው፡፡ ጠላቶች ልክ እንደ ፀበኛ ሰዎች ናቸው፡፡አንዳንድ ጊዜ በዙሪያችን ያለው ምቾታችን ጠላት ሊሆንብን ይችላል፡፡ በዙሪያችን ከብበው ያጠፉናል ይውጡናልም* (*መዝሙር* 18፡1-4)፡፡

***መልመጃ፡***

1. *ዳዊት በመፅሐፈ ሳሙኤል ካልዕ* 22 *ውስጥ ብዙ ስእላዊ ቋንቋዎችን ተጠቅሟል፡፡ እግዚአብሄር ለእርሱ ማን እንደሆነ ለመግለፅ የተጠቀመባቸውን ስዕላዊ ቋንቋዎችን ለይታችሁ አውጡ፡፡ በቁጥር* 2 *ላይ "እንዲህም አለ፦ እግዚአብሔር* ___________ ________ _________ *ነው*:: *እንደዚህ በማለት ቀጠለ እግዚአብሔር*_________ ፥ *በእርሱም እታመናለሁ* _________ _________፥___________ ________፥ *መድኃኒቴ ሆይ፥ ከግፍ ሥራ ታድነኛለህ፡፡*

2. የራሱን ህይወት እና የጠላቶቹን ማሳደድ ለመግለፅ የተጠቀመበትን ስዕላዊ መግለጫ ለይታችሁ አውጡ፡፡የሞት___________ ያዘኝ የዓመፅ ___________ አስፈራኝ የሲኦል ____________ ከበበኝ የሞት _____________ ደረሰብኝ፡፡
3. በቁጥር 4 እና 7 ውስጥ ጠራሁት፣ተጣራሁ፣ጮኽኩ የሚሉትን ቃላት ተጠቅሟል፡፡ ከጠላቶቻችን ለመዳን ወደ እግዚአብሄር ስንጮህ እግዚአብሄር የሚመልስልን ይመስላችኋል? እስቲ ከቁጥር 8 እስከ 16 ያለውን ክፍል አንብቡት፡፡

   ሀ. ምድርም _______________________፥ _________________________፥

   ለ. የሰማዮችም መሠረቶች _________እግዚአብሔርም________ተንቀጠቀጡ፡፡

   ሐ. __________ጢስ ወጣ፥ ከአፉም የሚበላ እሳት ነደደ ፍምም ከእርሱ በራ፡፡

   መ. ሰማዮችን ዝቅ ዝቅ አደረገ፥ ወረደም ጨለማም_________________ነበረ፡፡

   ሠ. ቁጥር 14 እግዚአብሔርም ከሰማያት__________________________፥

   ረ. ቁጥር 15 ____________________________________________________

   ሰ. ቁጥር 16 ____________________________________________________

   ሊያድነን እየመጣ ነውና!ፍጥረት ሁሉ ለቁጣው ምላሽ ይስጥ !
4. ከቁጥር 17 -19 ባለው ክፍል የተገለፀው ስዕላው ቋንቋ ምንድነው?___________

   ____________________________________________________________________
5. በቁጥር 20 መሰረት "ይህን ሁሉ ፍለጋ እና ማዳን የሚያደርገው ለምንድነው?_

   ____________________________________________________________________
6. ከቁጥር 21-25 ባለው ክፍል እግዚአብሄር ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት ይገልፅልናል፣በፊቱ ቅዱሳን አድርጎናል፣አንፅቶናል፣መንገዱን እንድንከተል እና ተእዛዛቱን በመፈፀም ታዛገሮች እንድንሆን አድርጎናል፣ከኃጢአት ጠብቆ ያለነቀፋ አድርጎናል፣እንደ ፅድቃችን መጠንም ብድራት አለን ፅድቃችን ደግሞ እርሱ ራሱ ነው፡፡

<u>ክፍል 2</u>

**ትምህርት፡** የዳዊትን የምስጋና መዝሙሮች ማጥናታችንን ለጥቂት ጊዜ ገታ እናደርጋለን፡፡ ስለ ፅድቅ ወይንም ስለ ፅድቃችን እናወራለን፡፡ እኛ ፃድቃን ነን? ከእግዚአብሄር ውጪ ምንም ፅድቅ የለንም፡፡ በሮሜ 3፡10 -12 ሁላችንም ኃጢአት እንደሰራን እና ከመካከላችን ማንም ፃድቅ

እንደሌለ ይነግረናል። ነገረ  ግን ዳዊት እግዚአብሄር በሰጠው ተስፋ ያምናል። በኤርሚያስ 23፡ 5-6 ባለው ክፍል "እነሆ፥ ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እርሱም እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥ ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል።በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፥ የሚጠራበትም ስም። እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው" ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስም በዚህ ላይ ጨምሮ "የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው።" ይለናል (1 ቆሮንቶስ 1፡30-31)።

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሄር ፊት ፃድቅ የሆንነው እኛ በሰራነው ስራ ሳይሆን እግዚአብሄር ፅድቃችን በሆነው  በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል በሰራልን ስራ እንደሆነ ይነግረናል።ከልጁ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋራ ያለን ግንኙነት እግዚአብሄር በእኛ እንዲደሰት ያደርገዋል። በእኛ ውስጥ የሚኖረው እና በእኛ ህይወት የሚሰራው ጌታ በፊቱ ያለነውር እና ያለነቀፋ መሆን እንድንችል ያደርገናል። የእርሱን ፅድቅ እንደ ሸማ  ለብሰናል። ኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን በእርግጥ ይኖራል ነገር ግን በክርስቶስ ፅድቅ ተሸፍኗል።

**መልመጃ፡** ወደ ሳሙኤል ካልዕ 22 እንመለስ....

1. ከቁጥር  26-27 ባለው ክፍል ላይ " ከ____________ ሰው ጋር______________ ሆነህ ትገኛለህ ከ_____________ ሰው ጋር ______________ ሆነህ ትገኛለህ ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ።
2.  በቁጥር 27 መሰረት ለክፉዎችስ እራሱን የሚገልፅላቸው እንዴት ነው? አንተ __________ ___________ ታድናለህና የ________________ _____________ ግን ታዋርዳለህ (ቁጥር 28)።
3. ዳዊት በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ አምላኩን እንዴት ነው የገለፀው?
   ሀ. ቁጥር 29______________________________________________
   ለ. ቁጥር 30______________________________________________
   ሐ. ቁጥር 31______________________________________________
4. የሚያስታጥቀኝ እግዚአብሄር ነው በጥንካሬ ያስታጥቀኛል ።ከጠላት ጋር ለመግጠም ጥንካሬ ያስፈልጋል። ይህ ጦርነት ነው እጆቼን_______________ቁጥር 35 እና

የማዳንህን_______________ቁጥር 36 ። ለውጊያ ታዘጋጀኛለህ ድልንም ትሰጠኛለህ።_________________ተግሳፅህም____________________

5. እግዚአብሄር ለሰልፍ ስላስታጠቀኝ ቁጥር 40 በጠላቶቼ ላይ ምን ይሆነናል?_____
______________________________________________

6. ከቁጥር 44 - 46 የንጉሱን ልብ ሰምታችሁታል? ________________________
______________________________________________

7. ዳዊትም እግዚአብሄርን አመሰገነ! ከ__________________________ታወጣኛለህ

**የትግበራ ጥያቄዎች፡**እግዚአብሄር ከጠላቶቼ አሳርፎኛል። ይህ እውነታ ጠላቶቼን ስገጥማቸው በህይወቴ የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል?________________________________

______________________________________________

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር አምላኬ ሆይ በህይወቴ ስላደረካቸው የማይቆጠሩ ነገሮች እኔም ላመሰግንህ እወዳለሁ። ምስጋናህን ለሌሎች እየነገርኩ ልዘምርልህ እወዳለሁ። ህይወቴን ሊያጠፏት እና ተስፋ ሊያስቆርጡኝ ህይወቴን የከበቧትን ጠላቶቼን አሸንፋቸው ዘንድ ጥንካሬን ስለሰጠኸኝ እጅግ ስለረዳኸኝም አመሰግንሀለሁ። ህይወቴን ታድገሃታል እና ስምህን በምስጋና እጠራዋለሁ ከፍ ልትል ይገባሃል።_________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ክፍል 3

**መግቢያ፡** በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ዳዊትን የመሰለ ንጉስ የለም። ዳዊት እንደ እግዚአብሄር ልብ የሚሄድ ሰው ነበር (የሐዋሪያት ሥራ 13፡22) በህይወቱ የእግዚአብሄር ፀጋ የበዛለት ሰው ነበር (ሐሥ 7፡46)። አሁን ሸምግሏል (ነገሥት ቀዳማዊ 1፡1)። ሌላ ንጉስ ሊቀባ ጊዜ መጣ።

**የቤት ስራ፡** መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 1 አንብቡ።

- እራሱን ንጉስ ያደረገው ማነው?
- ይህ ጉዳይ ለቤርሳቤህ እና ለሰሎሞን ምን ማለት ነው?
- ዳዊት ምን አደረገ?
- በእስራኤል ላይ ንጉስ ሆኖ ማን ነገሰ?

**ትምህርት፡** መፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 1 ስታነቡ አዶንያስ የዳዊት አራተኛው ልጅ እንደሆነ አውቃችኋል፡፡ በሳሙኤል ካልዕ 3፡4 ላይ እራሱን ንጉስ አድርጎ መሰየሙን ተመልክተናል፡፡ ነቢዩ ናታንም ይህ ለቤርሳቤህ እና ለሰሎሞን ምን ማለት እንደሆነ ከነገራት በኋላ የእራሷን እና የልጇን የሰሎሞንን ህይወት የምታተርፍበትን ምክር መከራት (ነገስት ቀዳማዊ 1፡11-14)፡፡ ወደ ንጉስ ዳዊት ገብታ በትህትና ቀጣዩ የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን እንደሚሆን የገባውን ቃል አስታወሰችው ቁጥር 17 ፡፡ እናም ካህኑ ሳዶቅ ሰሎሞንን ንጉስ አድርጎ ቀባው (ቁጥር 39)፡፡ አዶንያስም ሰሎሞን እንደነገሰ እና ህዝቡም ደስ እንደተሰኘ ሲመለከት ሰሎሞን ይገድለኛል ብሎ ፈራ (ቁጥር 49-51)፡፡ ሰሎሞንም ወደ አዶንያስ እንደዚህ የሚል መልዕክት ላከበት " ፡፡ ሰሎሞንም እርሱ አካሄዱን ያሳመረ እንደ ሆነ ከእርሱ አንዲት ጠጉር እንኳ በምድር ላይ አትወድቅም ነገር ግን ክፋት የተገኘበት እንደ ሆነ ይሞታል አለ (ቁጥር 52-53)፡፡"

**በጥልቀት መመልከት፡** ዳዊት ከመሞቱ በፊት በነገሥት ቀዳማዊ 2 ላይ ሰሎሞንን ጠንካራ እንዲሆን እና የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ እና የሙሴን ህግ እንዲጠብቅ መከረው፡፡ ሰሎሞንንም ስለ እዮአብ እና ስለ ሳሚ ፍርዳቸውን እንዲያገኙ አስጠነቀቀው፡፡ ለቤርዚሊ ደግሞ ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ ከአደረጉለት መልካም ነገር የተነሳ መልካም እንዲያደርግለት አስጠነቀቀው፡፡

በአዶንያስ ላይ በመፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 1፡1-4 ላይ የምትገኘውን ንጉስ ዳዊትን ትረዳ የነበረችውን ድንግሊቱን አቢሳን ለጋብቻ በመጠየቁ ክፉ ነገር ተገኘበት፡፡ ይህ የአዶንያስ ጥያቄ በእጅ-አዙር የንግስናውን ስፍራ መጠየቅ ነው፡፡ ከንጉሱ ጋር ግንኙነት ኖሯት በንጉስ ቤት የምትኖር ሴት እርሷ በህይወት እያለች ንጉሱ ከሞተ ዙፋኑን የመውረስ ሙሉ መብት አላት አዶኒያስም በዘዴ መጠቀም የፈለገው ይህንን መብት ነበር፡፡ አዶንያስ ከሞቱት ሶስቱ የዳዊት ልጆች ማለትም ከቤርሳቤህ የተወለደው ህፃን ፣አምኖን፣እና አቤሴሎም ቀጥሎ የሚሞት አራተኛው የዳዊት ልጅ ሆነ፡፡ ናታን እንደተናገረው አንዲቱን በግ ከደሃው ነጥቆ የበላው አራት እጥፍ አድርጎ ዳዊት መመለስ ይኖርበታል፤ ስለዚህ አዶንያስ በህይወቱ ከፈለ ተገደለም፡፡

ቀጥሎ የሞተው እዮአብ ነበር ቁጥር 28-34 ፡፡ በእርሱ ፈንታ በናያስን በሰራዊቱ ላይ ሾመው፡፡ ሳዶቅም በአቢያታር ፈንታ ካህን አደረገው፡፡ በመጨረሻም ሳሚ በዳዊት ላይ በሰራው በደል ምክንያት ተወገደ፡፡ አሁን መንግስት በሰሎሞን እጅ ፀናች (ቁጥር 46)፡፡

በጣም ብዙ ስሞች እንደዚሁም ብዙ ያልተለመዱ ስሞችን ተመለከትን፡፡ እነዚህ ስሞች አበበ፣ፍቃዱ ወይንም ገመቹ እንደሚሉት ስሞች የተለመዱ ስሞች አይደሉም ፡፡ እነዚህን ሁሉ

ስሞች ለመያዝ በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ሊረሱ የማይገባቸው ቁልፍ ስሞች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የዳዊት ልጆች (አምኖን፣አቤሴሎም፣አዶንያስ)
2. ካህናቶቹ (በዳዊት ዘመን አብያታር፣በሰለሞን ዘመን ደግሞ ሳዶቅ) እንደዚሁም
3. የጦር መሪ የነበሩት (ከሳኦል ጋር አበኔር ፣ከዳዊት ጋር እዮአብ፣እና ከሰሎሞን ጋር በናያስ ናቸው፡፡

በጥናታችሁ ቀጥሉ አትድከሙ አይሰልቻችሁ ቀሪውን ጥናት ከሰሎሞን ጋር ደግሞ ቀጥሉ፡፡

<u>ክፍል 4</u>

**የቤት ስራ፡** ቀጥሎ ያለው ታሪክ ወደ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ ይወስዳናል፡፡በነገሥት ቀዳማዊ እና ካልዕ የተፃፉ ታሪኮች በአብዛኛዎቹ በዜና መዋልዕ ተፅፈው ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ዜና መዋዕል ካልዕ 1፡1-17 የለውን ክፍል አንብቡ፡፡ ማሳሰቢያ፤- ከፈለጋችሁ መጽሐፈ ነገሥት 3፡4-15 ያለውን ክፍል ማንበብ ትችላላችሁ፡፡

**መልመጃ፡**

1. ሰሎሞን እና ጉባኤው ሁሉ በገባኦን ተሰበሰቡ፡፡ በዚያ ምን ምክንያት ነበር የሰበሰባቸው (ቁጥር 3)?__________________________________________________________________________________
2. ዳዊት ከቂርያትይዓሪም ያመጣው የቃልኪዳኑ ታቦት የት ነበር (ቁጥር 4)? ____________________________________________________
3. የነኃሱ መሰዊያ በገባኦን በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት ነበር፡፡ ሰሎሞን ምን አደረገ(ቁጥር 6)?____________________________________________
4. በዚያ ሌሊት ምን ሆነ ? እግዚአብሄር ለሰሎሞን ምን ነገረው ቁጥር 7? ______________________________________________________
5. የሰሎሞን ምላሽ ምን ነበር ከቁጥር 8-10 ? _________________________________________________________________________________
6. የእግዚአብሄርስ ምላሽ ምን ነበር ከቁጥር 11-12? _____________________________________________________________________________

7. ሰሎሞን በንግስናው ዘመን ያከማቸው ሃብት ምን ነበር ቁጥር 14-17? _____

__________________________________________________________

**ትግበራ፡** በጣም የሚያስገርም ነው ህዝቡን ከራሱ የሚያስቀድም ንጉሥ፡፡ ለራሱ የሚሆን ነገር ከመጠየቅ ይልቅ የእግዚአብሄርን ህዝብ የሚያገለግለበት ጥበብ እና እውቀት እግዚአብሄር እንዲሰጠው ጠየቀ፡፡ እውቀት መረጃን ማግኘት ማለት ነው፡፡እውነተኛው እውቀት የእግዚአብሄር ቃል ማወቅ እና መረዳት ማለት ነው፡፡ ጥበብ ማለት ደግሞ የተረዳነውን የእግዚአብሄር ቃል እለት እለት በምንኖረው ህይወት ለሚገጥመን ሁኔታ ሁሉ በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ ማለት ነው፡፡

1. ከሰሎሞን ህይወት መማር እንችላለን፡፡ ሰሎሞን እግዚአብሄር ለጠራው ታላቅ ጥሪ ምን እንደሚያስፈልገው አውቋል፡፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በያዕቆብ መልእክት ውስጥ ጥበብን ከእግዚአብሄር ዘንድ እንድንጠይቅ ተነግሮናል፡፡ ያዕቆብ 1፡5 ፃፉ፡_______________

   __________________________________________________________

2. እግዚአብሄርን እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምነው እንደሚሰጠን የምንጠይቅበት እድል ተሰጥቶናል፡፡ ለመሆኑ ጥበብን የምንጠይቅበት ምክንያት ምንድነው?_____________

   __________________________________________________________

3. በቤታችሁ ሊሆን ይችላል፤ በመሪነት ስፍራ ነው ያላችሁት? በትምህርት ቤትስ? በስራ ቦታስ? በማህበረሰቡ ውስጥስ? በቤተክርስቲያን? እግዚአብሄርን በሚያስደስት መልኩ እንድንቆጣጠራቸው የእግዚአብሄር ጥበብ የሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?_____________________________________________

   __________________________________________________________

**<u>ክፍል 5</u>**

***መግቢያ፡*** ስለ ሰሎሞን የጀመርነውን ጥናት ለጊዜው *ነገሥት ቀዳማዊ* ላይ እናቆመዋለን፡፡እግዚአብሄር ለሰሎሞን ታላቅ ጥበብን ሰጠው፡፡*ያዕቆብ* 1፡5 ስንመለከት ከእግዚአብሄር ጥበብ ለሚፈልግ ሁሉ እግዚአብሄር ሳይነቅፍ በልግስና ይሰጣል፡፡

**የቤት ስራ፡** *ነገሥት ቀዳማዊ* 4፡29-34 አንብቡ፡፡

**መልመጃ:**

1. በቁጥር 29 መሰረት እግዚአብሄር ለሰሎሞን ምን ሰጠው?

   ሀ.________________________________________

   ለ.________________________________________

   ሐ.________________________________________

2. ቁጥር 30 እና 31 እንደሚነግረን እንደሰሎሞን ያለ ጥበበኛ ሰው አልነበረም፡፡ ካደረጋቸው ነገሮ ጥቂቶቹ ምን ምን ነበሩ?

   ሀ. ቁጥር 32: __________________________________

   ለ. ቁጥር 32: __________________________________

   ሐ. ቁጥር 33: __________________________________

   መ. ቁጥር 33: __________________________________

3. እናም ውጤቱስ__________________________________(ቁጥር 34 )

**የቤት ስራ፡** መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 3፡ 16-28 አንብቡ፡፡ይህ ታሪክ የሰሎሞን የፍርድ አሰጣጥ ጥበብ የታየበት ክፍል ነው፡፡

**መልመጃ:**

1. በንጉሱ ፊት ሁለት ሴቶች እየተከራከሩ ነው፡፡ የሚያከራክራቸው ጉዳይ ምን ነበር (ቁጥር 16-22)?____________________________________

   ______________________________________________

2. በቁጥር 23 ውስጥ ሰሎሞን ለክርክሩ መቋጫ አበጀለት፡፡ በቁጥት 24-25 ባለው ክፍል ምን እንዲደረግ ትእዛዝ አስተላለፈ?____________________________

   ______________________________________________

3. በቁጥር 26 ላይ የሁለቱ ሴቶች ምላሽ ምን ነበር?__________________________

   ______________________________________________

4. ነገስታቶች የሚያስተዳድሩት ምን ነበር ቁጥር 27?__________________________

**ገለፃ፡** ይህንን ታሪክ ስታስረዱ ስለሰሎሞን ጥበብ ከሚያሳየው ከዚህ ታሪክ ህይወታችሁን የነካውን ነገር ለሌሎች አካፍሉ፡፡

1. አንድ ሰው ይህን አይነት ጥበብ እንዴት ሊያገኝ ይችላል?___________________
2. አንድ ሰው ጥበብን በተፈጥሮ ሊያገኘው ይችላል?__________________________
3. በህይወቴ ጥበብን ያገኘሁበት ጊዜ መቼ ነበር?_____________________________
4. በህይወቴ ውስጥ ጥበበኛ የምላቸው ሰዎች እነማን ናቸው?___________________

**በጥልቀት መመልከት፡** በመጽሐፈ ምሳሌ እና መክብብ ውስጥ ሰሎሞን ስለጥበብ ብዙ ነገር ተናግሯል፡፡ እስቲ ስለጥበብ ምን እያለ እንደሆነ ተመልከቱ፡፡ ስለ ጥበብ ከሚናገርባቸው ስፍራዎች ቀጥሎ ያሉትን ጥቂት ቁጥሮች እንመልከት፡መጽሐፈ ምሳሌ 1-4 እና መክብብ 7፡11-8፡1፡፡

መልካም ምንባብ!

## ክፍል 6

**ትምህርት ፡** በዚህም ክፍል እንደገና በዝርዝር አጥንተን ልንጨርሰው የማንችለውን ክፍል ገጥሞናል፡፡ ስለ ሰሎሞን የጀመርነውን ጥናት ለማጠቃለል እንዲሁም የሰሎሞንን የንግስና ዘመን ለመቃኘት ሰፊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መዳሰስ ይኖርብናል፡፡ እነዚህን ክፍሎች ከዚህ ጥናት ውጪም ሙሉውን ክፍል በጥንቃቄ እንድታነቧቸው እመክራችኋለሁ በደንብ አንብቡት የነኳችሁን ቃላቶች ሃረጎች ፣ዐረፍተ ነገሮች አስምሩባቸው ፣ምልክት አድርጉባቸው በደንብ አጥኗቸው፡፡ ቤተመቅደስ ለእስራኤላውያን የሃገሪቱን ሃብት የሚያስቀምጡበት ስፍራም ጭምር ሆኖ እንደሚያገለግል አስታውሱ፡፡

1. ሁለቱ ዋና ዋና የቤተ መቅደስ ውጥኖች ምንድናቸው? መፅሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 5-7
   ሀ. ______________________________________________
   ለ. ______________________________________________
2. የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ቤተመቅደስ ለማምጣት የሚደረገውን ዝግጅት ስታነቡ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድነው?_______________________________

   ከቁጥረ 10-11 ያሉትን ክፍሎች ከግንዛቤያችሁ ውስጥ አስገቡ ______________

3. ቤተመቅደሱ ሲመረቅ የነበሩትን  የፀሎት እና የምስጋና ቃላት በጥንቃቄ አንብቧቸው፤ መፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 8፡14- 66 ፡፡ለእናንተ ለየት ያለው ትርጉም የሰጧችሁን ቃላቶች እንደዚሁም ሃረጎች ለይታችሁ አውጧቸው፡፡_____________

_______________________________________________________________

4. ሰሎሞን ይህንን ታላቅ ህንፃ ሰርቶ ሲጨርስ እግዚአብሄር የሰጠው ተስፋ እና ማስጠንቀቂያ ምንድነበር (ነገሥት ቀዳማዊ 9፡1-9)?________________________

_______________________________________________________________

5. በነገሥት ቀዳማዊ 9፡10 እስከ ምዕራፍ 10 ባለው ክፍል ውስጥ ሰሎሞን ስላከማቸው የሃብት መጠን መገመት የምንችልበት መረጃ እናገኛለን፡፡ በነገሥት 3፡13 ላይ እግዚአብሄር ሰሎሞንን ያልጠየቀውን ሃብት እና ብልፅግና እንደሚሰጠው ተናግሮታል፡፡ እናም ሃብት አገኘ! ምዕራፍ 11 አንድ ችግር እንደተፈጠረ ይነግረናል፡፡በቁጥር 1 ላይ ያለው ማጠቃለያ ምንድነው?___________________

6. የተፈጠረው ችግር ምንድነበር ቁጥር 1-3? __________________________

_______________________________________________________________

7. ለምንድነው እግዚአብሄር ህዝቡን እስራኤልን ከወገናቸው ውጪ ሌላ ሴት እንዳያገቡ የከለከላቸው?_______________________________________________

_______________________________________________________________

8. ከቁጥር 4- 8 ያለው ክፍል ስለ ሰሎሞን ያለመታዘዝ ህይወት ይነግረናል፡________

_______________________________________________________________

9. እግዚአብሄር ተቆጥቶ ነበር፡፡በሰሎሞን ላይ ያስተላለፈው ፍርድ ምን ነበር (ቁጥር 9-13)?_______________________________________________________

***ማጠቃለያ፡*** *መፅሐፈ* በነገሥት ቀዳማዊ 11፡14-40 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ጠላት እንዳስነሳበት ይናገራል፡፡ ከጠላቶቹ አንዱ ለሆነው ለኢዮርብአም አኪያ የተባለው ነቢይ እስራኤል ለሁለት እንደምትከፈል ነግሮት ነበር፡፡ ኢዮርብአም በአስሩ ነገዶች ላይ ነገሰ፡፡ እግዚአብሄር ግን ለባሪያው ዳዊት ስለገባው ቃልኪዳን ሲል ይሁዳንና የቢንያምን ነገድ ለሰሎሞን ልጅ ሰጠ፡፡ በቁጥር 41-43 ላይ እንደምናነበው ሰሎሞን ሞተ ሲሞትም ልጁ ሮብአም በእርሱ ምትክ ነገሰ፡፡

<u>**ክፍል 7**</u>

**ገለፃ፡** በድጋሚ ታላቅ ስኬትን፣ታላቅ ጥበብን፣ታላቅ ብልፅግናን፣ታላቅ ግንባታ፣ክብር፣እግዚአብሄር ለቀባው ንጉስ ሰጥቶት ተመልክተናል። ታዲያ ምን ተፈጠረ ? የተፈጠረው ችግር ምንድነው?ለምንድነው ሰሎሞን ከእግዚአብሄር ተቃራኒ መሄድ የመረጠው? እግዚአብሄርን ባይታዘዝ እና ሌሎች አማልክቶችን ቢያመልክ ሊገጥመው የሚችለውን ችግር ነግሮ አስጠንቅቆታል ታዲያ ለምንድነው እግዚአብሄርን የሚያስቆጣ ነገር ያደረገው? እግዚአብሄርም ሁለቱን ነገዶች ብቻ አስቀርቶ መንግስቱን ከእርሱ ቀደደ። በዚህ ክፍል ላይ የእናንተ ሃሳብ ወይንም የምታነሱት ጥያቄ ምንድነው? ______________________________

______________________________________________________________________

**ትምህርት፡** ነገሮች እየባሱ ሄደዋል። በምዕራፍ 12-14 ባለው ክፍል የእስራኤል መንግስት በሰሜን የይሁዳ ግዛት ደግሞ በስተደቡብ ተመሰረተ። እነዚህ ሁለት ግዛቶች የየራሳቸው ነገሥታት ነበራቸው ነገሥት ቀዳማዊ እና ካልዕ የሚነግሩን እግዚአብሄር ወደ እነዚህ ነገሥታት ስለላካቸው ነቢያት እና ማስጠንቀቂያዎች ነው።

**በጥልቀት መመልከት፡** የእነዚህን ነገሥታት የንግስና ሁኔታ በምስል በአንድ ወይንም በሁለት ቃላት መግለፅ ልትመርጡ ትችላላችሁ። የእነዚህን ነገስታት የንግስና እንደዚሁም ይመሩበት የነበረውን ሁኔታ ማስታወስ ለዚህ ጥናት ብዙም ጠቃሚ እንዳልሆነ አስታውሱ። ከእነዚህ ነገስታት ታሪክ ዋናው እና ጠቃሚው ትምህርት ከጥቂቶቹ በስተቀር የነገሡት ነገስታቶች በሙሉ የእግዚአብሄርን ህዝብ ወደ ኃጢአት የመሩ የመሆናቸው ነገር ነው። ካደረጓቸውም ነገሮች መካክል ጥቅም የሌላቸውን አማልክት ማምለካቸው፣በከፍታ ስፍራዎች የተከለከሉ መሰዊያዎችን መገንባት፣የእግዚአብሄርን ቤተመቅደስ ንብረት ማባከን፣እራሳቸውን ለክፉ ስራ ባሪያ አድርገው መሸጣቸው እንዲሁም የሰው መስዋእት ለአማልክቶቻቸው ማቅረባቸው እግዚአብሄር በነቢያት የሚልክላቸውን ማስጠንቀቂያ አለመቀበል ብሎም ነቢያቶችን እስከ መግደል መድረስ እና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል።

**ትምህርት፡** እንዴት ነበር ታሪኩ የሚጠናቀቀው? በመፅሐፈ ነገሥት ካልዕ 17 ላይ የእስራኤልን መንግስት ውድቀት እንመለከታለን። የሶርያው ንጉስ የሰሜኑን ግዛት ህዝብ ሙሉ በሙሉ ምርኮ አድረጎ ወደ ሶሪያ ወሰደ። ቁጥር 18 ምን ይነግረናል?______________________________

______________________________________________________________________

ከቁጥር 7-23 ያለው ክፍል ስለ ምርኮው እንደዚሁም ህዝቡ በምን መልኩ ወደሶሪያ እንደተጓጓዘ ይነግረናል። ይህ ህዝብ ከዚህ በኋላ እግዚአብሄርን በኑሮው እና አገልግሎቱ የሚያሳይ ሳይሆን እግዚአብሄርን የተወ ህዝብ ሆኖ ይቀጥላል። ህዝቡ ያደረጋቸው በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች ፃፏቸው።

- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________
- ______________________________

እግዚአብሄር አምላካቸውን ስለተው እርሱም ትቷቸዋል። በይሁዳ ምድር ነገሮች ምንም እንዳልተለወጡ ሊታሰብ ይችላል ነገር ግን ቁጥር 18 እና 19 "ከይሁዳ ነገድ በስተቀር የቀረ አልነበረም "ብለው ይነግሩናል። ይሁዳም በአምላካቸው በእግዚአብሄር ህግ አልሄዱም..።" ምን ነበር የሚከተሉት? ______________________________

መፅሐፈ ነገሥት ካልዕ 24 እና 25 እንደሚነግረን ሴዴቂያስ በነገሰበት ዘመን የባቢሎኑ ንጉስ ናቡከደነፆር ሰራዊቱን ሁሉ ይዞ በመምጥት ኢየሩሳሌምን በቁጥጥሩ ስር አደረጋት። እነዚህ ቁጥሮች ባቢሎናውያን ይሁዳን እንዴት እንዳጠፏት ከተማዋን እንዴት እንዳፈራረሷት እና እንደዘረፏት ይነግሩናል ።እየሩሳሌምን ፣ቤተመቅደሱንም፣እንደዚሁም ቤተመንግስቱን ፣ቤቶችን እንደዚሁም ጠቃሚ የሆኑትን ህንፃዎች በሙሉ  አቃጠሉ ። የይሁዳንም ህዝብ በሙሉ ወደ ባቢሎን በምርኮ ወሰዱ።

**ገለፃ፡** በእርግጥ እነዚህን ምዕራፎች በጥልቀት አላየናቸውም ጥቂት ክፍሎችን ብቻ ለመቃኘት ሞክረናል። ይህንን ቅኝት የማድረጋችን አላማ የተለያዩ ነገሥታት የገዙበት የእስራኤል ታሪክ ምን ይመስል እንደነበር እንደዚሁም በዚያን ወቅት ምን እንደተከናወነ በጥቂቱ ለማሳየት ነው።ዛሬ ላይ ሆነን ይህንን ታሪክ ስናነብ  በጣም የሚያስጨንቅ ታሪክ ነው። ነገር ግን በዚያን ወቅት ለሚኖሩት ህይወት ምን ያህል ከባድ እና አስቸጋሪ እንደነበረ ማሰብ አይከብድም። ለመሆኑ ነገሥታቶቹ ህዝቡን በዚህ የውድቀት መንገድ እንዲመሩት ያደረጋቸው ምንድነው?ህዝቡስ እግዚአብሄር ከምድሪቱ ላይ ጠርጎ ያወጣቸውን እነዚህን የአህዛብ አማልክት እና ጣኦታት ለምን መከተል ወደደ? እነዚህን ጥያቄዎች እነርሱ ምን ብለው ይመልሱ ይሆን?

ምን ምክንያት ያቀርቡ ይሆን? እናንተስ ስለዚህ ሁኔታ ምን ታስባላችሁ?? ________________

______________________________________________________________________________

እግዚአብሄርን ትቶ ጣኦታትን በማምለክ እና በመከተል ጉዳይ ዙሪያ እኔ ያለኝ አቋም ምንድነው? መልሴስ ምን ሊሆን ይችላል? ምክንያቴስ ምን ሊሆን ይችላል?? ______________

_____________________________________________________________________________

# ትምህርት ስድስት

# እግዚአብሄር እርሱ አምላክ ነውና ተከተሉት

## መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17 እስከ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 5
## ኤልያስ እና ኤልሳዕ

---

የትምህርት 6 ቅኝት

**ቅኝት**

**መግቢያ**

ትምህርት 6፡ መጽሐፈ ነገሥት 17-መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 5

- ኤልያስ እና የሰራፕታዋ ሴት
- እግዚአብሄር እርሱ አምላክ ነው
- ያህዌ ከበአል ተፋለመ
- የእሳት ሰረገላ
- ሱነማዊቷ ሴት
- መዝሙር 130
- ታጠብና ንፃ

## *መግቢያ*

እስራኤል ወርቃማ ከነበረው የዳዊት የከፍታ ዘመን አሁን ወደ ባርነት እና ግዞት አዘቅት ውስጥ ወድቃለች፡፡ እንዴት ዘግናኝ ነገር ነው! የንጉስ ይንገስልን ጥያቄያቸው ወደ ተስፋ አስቆራጭ ዘመን አመጣቸው፡፡ የህዝቡ መሪዎች ህዝቡን በአልንና አስታሮትን እንዲያመልኩ እና እንዲከተሉ በስህተት መንገድ መሯቸው፡፡ ህዝቡ ከክፉ ስራው እንዲመለስ እና ንሰሃ እንዲገባ እግዚአብሄር በተደጋጋሚ ነቢያትን ላከ፡፡ በዚህ በትምህርት 6 ሁለት ነቢያቶችን እንተዋወቃለን ኤልያስ እና ኤልሳ፡፡

ይህ ክፍል እግዚአብሄርን ያመኑ ፣ ያወቁ እና የተከተሉ ሰዎችን ታሪክ የያዘ የትምህርት ክፍል ነው፡፡ የኤልያስ ታሪክ የሰራፕታዋን ሴት ታሪክ የያዘ ነው፡፡ሀሰተኛ ነቢያትን መጋፈጥ እና በእሳት ሰረገላን መነጠቅንም ጨምሮ የያዘ የታሪክ ክፍል ነው፡፡ የኤልያስ ታሪክ የሱነማዊቷ ሴት እና የንእማንን ታሪክ የያዘ ነው፡፡ እግዚአብሄር ለሚከተሉትን እና ለሚታዘዙት ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን እና በነቢያቱ የተላከውን ቃል በእምነት ለሚቀበሉ እንዴት ተአምር እንደሚያደርግ ተመልከቱ፡፡

እግዚአብሄር አምላክ ነው የሚለው እውነት ልንከተለው የተጠራንለት እውነት ነው!

**ክፍል 1**

**መግቢያ፡** ትምህርት 6 ወደ መፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ እና መፅሐፈ ነገሥት ካልዕ ይመልሰናል። በዚህ ትምህርት የሁለት ታላላቅ ሰዎችን ህይወት እንደዚሁም በህይወታቸው ዙሪያ ያሉትን ነገሮች እንቃኛለን፤ እነዚህ ሰዎች ኤልያስ እና ኤልሳዕ ይባላሉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች የኖሩት እስራኤል እና ይሁዳ አመፀኛ በሆኑ ነገስታት በሚመሩበት ዘመን ነበር። ህዝቡ በእግዚአብሄር ፊት በሚኖሩት እርሱን የሚያሳዝን አኗኗር እግዚአብሄር ህዝቡን ሊተዋቸው ግድ ሆኖበታል። የሶርያ እና  የባቢሎን ነገስታት እስራኤልንም ሆነ ይሁዳን እያንዳንዳቸውን ወደ ግዛታቸው ወስደው ባሪያዎቻቸው እና አገልጋዮቻቸው አደረጓቸው።

**የቤት ስራ፡** መፅሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 17 አንብቡ ይህ ምዕራፍ ሶስት ታሪኮችን ይነግረናል። 1)ቁጥር 1-6 ፤2 ። 2) ቁጥር 7-16 እና 3) ቁጥር 17-24 ባሉት ክፍሎች ውስጥ ያሉት ናቸው። እነዚህ ነስታት ይገዙ በነበረበት ወቅት እግዚአብሄር በነቢያቱ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ይልክላቸው ነበር። አክአብ የሰሜናዊው ግዛት ወይንም የእስራኤል ንጉስ በነበረበት ወቅት ኤልያስ ደግሞ ነቢይ ነበር።

- ለንጉስ አክአብ የኤልያስ መልዕክት ምን ነበር?
- እግዚአብሄር ለኤልያስ ያዘጋጀለት ምን ነበር?
- እግዚአብሄር ኤልያስን ወዴት ነበር የላከው?
- የኤልያስ እና የመበለቷ ሁለት ታሪኮች ምን እና ምንድናቸው?
- የሴትዮዋ ንግግር ምን ነበር?

**መልመጃ፡**

1. በመፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 16፡33 ስለ ንጉሥ አክአብ የተነገረን ምንድነው?

___________________________________________

___________________________________________

በመፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፡1 ላይ ኤልያስ ወደ ንጉሥ አክአብ በመምጣት ምን

አለው?___________________________________________________________

___________________________________________________________

2. በቁጥር 2-4 እግዚአብሄር ለኤልያስ የሰጠው መመሪያ ምን ነበር? ___________

___________________________________________________________

ኤልያስም ለሚጠብቀው እና ሁሉን ለሚያዘጋጅለት አምላክ ታዘዘ፡፡

3. ቁጥር 7 ላይ እንደምናነበው ወንዙ ደረቀ፡፡ ዝናብም ሆነ ጠል አልነበረም ፡፡ ከቁጥር 8-9 ባለው ክፍል ውስጥ ምን ነበር ለኤልያስ የነገረው?______________________

___________________________________________________________

ሰራፕታ በፊንቄ የባህር ዳርቻ ከጢሮስ እና ሲዶና መካከል የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት፡፡

4. ኤልያስ ሰራፕታ ሲደርስ ማንን አገኘ? ______________________________

___________________________________________________________

5. የጠየቃት ሁለት ነገሮች ምን እና ምንድናቸው?

ሀ. ቁጥር 10_____________________________________________

ለ. ቁጥር 11_____________________________________________

6. በቁጥር12 ላይ በቤቷ ስለነበረው ሁኔታ ምን ብላ ገለፀችለት ?______________

___________________________________________________________

7. ለልጇ እና ለራሷ ከማብሰሏ በፊት ለእርሱ ምን እንድታደርግለት ነገራት?_________

___________________________________________________________

8. ከቁጥር 14-16 ባለው ክፍል ላይ እግዚአብሄር የሰጣት ተስፋ ምን  የሚል ነበር?__

___________________________________________________________

**ትግበራ፡** ኤልያስ ለሴትዮዋ እና ለልጇ ብቻ የቀረውን ምግብ በቅድሚያ ለእኔ ብቻ ጋግረሽ ሽጪኝ ብሎ ሲጠይቅ እራስ ወዳድ ያስመስለዋል፡፡ ነገር ግን ይህቺ ሴት ዘይቱም ከማሰሮው ዱቄቱም ከማድጋው አያልቅም ያለውን ቃል ማመኗ በተግባር ይገለጥ ዘንድ ነው፡፡ የዚህች ሴት እምነት የሚደነቅ ነው፡፡ ሁለት ጥያቄዎችን እራሳችንን እንድንጠየቅ እንገደዳለን፡

1. እንደዚህ አይነቱ ጥያቄ የቀረበው ለእኔ ቢሆን እግዚአብሄር ያዘጋጅልኛል ብዬ መስጠት ወይንስ ለራሴ ፈርቼ መሸሸግ ፣የእኔ ምርጫ ምን ሊሆን ይችላል? _____

___________________________________________________________

2. እኔስ ያልቅብኛል እቸገራለሁ ብዬ የምፈራው ነገር ይኖር ይሆን? የገንዘብ እጥረት ይገጥመኛል ብዬ እሰጋ ይሆን? በጎተራዬ ያለው የሚበላው እንዲሁም የሚጠጣው፣የምለብሰው፣እንደዚሁም ለህይወቴ ያስፈልጉኛል የምላቸው ነገሮች አልቀው ሁሉ ነገር ባዶ እንዳይሆንብኝ እሰጋ ይሆን?________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**መልመጃ:**

1. ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌላ ነገር ተከሰተ (ቁጥር 17)። የዚህች ሴት ብላቴና ታመመ ወዲያውም ሞተ። እናም ሴቲቱ ቁጣዋ በኤልያስ ላይ ነደደ።በቁጥር 18 መሰረት ለማወቅ የፈለገችው ምንድነው?________________________________________

________________________________________________________________

2. ማወቅ የፈለገችው ኤልያስን የበደልኩት ነገር ምንድነው የሚለውን ነው። ይህ ነቢይ የመጣው ከዚህ በፊት የሰራሁትን ኃጢአት አሳስቦ የኃጢአቴን ዋጋ እንድቀበል ሊያደርገኝ ነውን? በቁጥር 20 እንደምንመለከተው ኤልያስም ብላቴናውን ከእቅፏ ወስዶ በሰገነቱ ወዳለው ክፍል ወስዶ በራሱ አልጋ ላይ አስተኛው። ወደ እግዚአብሄርም ጮኸ: ________________________________________________

________________________________________________________________

3. በቁጥር 21 ላይ ኤልያስ ያደረገው ምንድነው? ____________________________

________________________________________________________________

4. በቁጥር 22 ላይ የሆነው ተአምር ምን ነበር?____________________________

________________________________________________________________

**ትምህርት:** ተአምር ሆነ የብላቴናው ነፍው ተመለሰች በህይወትም ኖረ። ነገር ግን ይህን ያደረገው የእግዚአብሄር ምህረት እና ፀጋ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። ቁጥር 22 ላይ እንደዚህ ይላል: “እግዚአብሔር የኤልያስን ጩኸት ሰማ”። እግዚአብሄር ይሰማል። እግዚአብሄር የህዝቡን ጩኸት ያደምጣል። ሁሉን የሚችል የአብርሀም ፣የይስሃቅ፣የያዕቆብ አምላክ ይሰማል ። “እኔ አምላክ እሆናችኋለሁ እናንተም ህዝብ ትሆኑኛላችሁ” ያለ አምላክ ስሙን ለሚጠሩት ሁሉ መልስ ይሰጣል። እግዚአብሄር ለሞተው እና ህይወት አልባ ለነበረው ብላቴና ህይወት በመስጠት በኤልያስ ህይወት የትንሳኤውን ሃይል ገልጿል።

በቁጥር 23 መሰረትም ኤልያስ ብላቴናውን አቅፎ ከሰገነቱ በመውረድ ለእናቱ አስረከባት፡፡ ይህ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሙት የነበረው ብላቴና አሁን ህያው ሆኗል! ኤልያስ እራሱ በመገረም ሆኖ "እነሆ ብላቴናሽ ህያው ሆኖ ይኖራል!" ብሎ ሲያስረክባት እንመለከታለን፡፡ በዚህን ጊዜ የሚፈጠረውን የደስታ ልክ ልታስቡት ትችላላችሁ?

**ገለፃ፡**

1. በቁጥር 24 ላይ የተረዳችውን ነገር በግልፅ ተናግራለች፡፡ ምን በማለት ነበር የገለፀችው?______________________________________________________

   ________________________________________________________________

2. የረሃቡ ዘመን እስኪያልፍ ድረስ በተአምራት ዱቄቱም ከማድጋው ሳይጎድል ዘይቱም ከማሰሮው ሳይጎድል እለት እለት በተአምራት እየተመገበች ኤልያስ የእግዚአብሄር ሰው መሆኑን አላወቀችም ማለት ነው? በእርግጥ ይህንን ነገር የተረዳችው አሁን ነው ማለቷ ይሆን? አዎን በእርግጥ አሁን አወቀች! ሙት የነበረ ብላቴና አስታቀፈችው እግዚአብሄር ደግሞ ፀሎቱን ሰምቶ ትንሳኤን ሰጠው፡፡ የእግዚአብሄር ቃል እውነት ነው፡፡ እናንተስ በዚህ እውነት ታምናላችሁ የእናንተስ ምላሽ ምን ሊሆን ይችላል?____________________________________________
3. በህይወታችሁ ውስጥ ትንሳኤ ተከናውኗል? በዚህ ምክንያት የቤተሰቦቻችሁ እና የጓደኞቻችሁ ተስፋ ተነቃቅቷል፡፡ የድርቅ እና የረሃብ ወቅት በሆነበት ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሄርን ህልውና ተለማምዳችኋል?______________________________

   ________________________________________________________________

   የእግዚአብሄር ቃል እውነት ነው፡፡

**ክፍል 2**

***መግቢያ፡*** ሌላው በኤልያስ ህይወት ውስጥ ከተከናወኑት ጉልህ ነገሮች ውስጥ አንዱ የሚገኘው በነገሥት ቀዳማዊ 18፡16-14 ውስጥ ነው፡፡ በቁጥር 16 ላይ አብድዩ በንጉስ አክአብ ቤተመንግስት ውስጥ ስፍራ የነበረው ሰው ነው፡፡ ዝናብ ከዘነበ ሶስት አመት ያህል ቢሆነውም ንጉስ አክአብ አብድዩን ለከብቶቹ የሚሆን የግጦሽ ሳር እንዲፈልግ ላከው፡፡ አብድዩም ወደዚያው ሲጓዝ ሳለ (ቁጥር 7) ኤልያስ ደግሞ በእግዚአብሄር ተልኮ እራሱን ለንጉስ አክአብ ሊገልጥ

ሲመጣ በመንገድ ተገናኙ (ቁጥር 1-2)። እንግዲህ ታሪኩ አክአብ ኤሊያስን ሊገናኝ ሲሄድ ይጀምራል ቁጥር 16)።

**መልመጃ:**

1. በቁጥር 17 ላይ አክአብ እንዴት ነበር ሰላም ያለው?________________________

   ________________________________________________________________

2. ኤልያስ ችግር ፈጣሪዎች ያላቸው እነማንን ነው?___________________________

   ________________________________________________________________

3. ቁጥር 18 መሰረት ምን ነበር ያደረጉት?________________________________

   ________________________________________________________________

   ንጉስ አክአብ እና ሚስቱ ኤልዛቤል ያመልኳቸው የነበሩት በአል እና አሼራ የተባሉ የሐሰት አማልክትን ነበር። የእነርሱ ማምለክ ሳያንስ ህዝቡንም እውነተኛ አምላክ የሆነውን ያህዌን ፣የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሄርን ትተው እነዚህ አማልክት እንዲያመልኩ አድርገው ነበር።

4. ኤልያስ ህዝቡን ጠራ። ኤልያስ ለአክአብ የሰጠው መመሪያ ምን ነበር (ከቁጥር 19-20)? በቀርሜሌዎስ ተራራ ማን ነበረ?

   ሀ.______________________________________________________________

   ለ. ______________________________________________________________

   ሐ. ______________________________________________________________

5. በቁጥር 21 ላይ ባለው መሰረት ኤልያስ ህዝቡን ሰብስቦ ምን ነገራቸው?_________

   ________________________________________________________________

6. በቁጥር 21 መሰረት የህዝቡ ምላሽ ምን ነበር ?____________________________

   ________________________________________________________________

7. ኤሊያስ ምን አቀደ ከቁጥር 22-24? __________________________________

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

8. ህዝቡም ሁሉ ተስማማ የበአል ነቢያትም አንዱን በሬ መረጡ በብልት በብልቱም ቆራርጠው አሰናዱ ከዚያም የአምላካቸውን ስም መጥራት ጀመሩ። ሊሆንላቸው

ያልቻለው አንድ ነገር አምላካቸው በእሳት ሊመልስላቸው አለመቻሉ ነው። የ_______________________________ስም ይጠሩ ነበር።

9. ከቁጥር 26 -29 ባለው ክፍል ውስጥ የሆነው ነገር ምን ነበር?_______________

_______________________________________________________________

10. በቁጥር 30 ላይ ኤልያስ ህዝቡ እንዲሰበሰብ አደረገ። በአስራ ሁለቱ የእሰራኤል ነገዶች ቁጥር አስራ ሁለት ድንጋይን ወስዶ የፈረሰውን መሰዊያ ሰራ። በመሰዊያው ዙሪያ የቆፈረው ጉድጓድ ምን ነበር (ቁጥር 32)? __________________________

11. በመሰዊያው ላይ በተከመረው እንጨት ላይ የተቆራረጠውን ስጋ አስቀመጠ። ከቁጥር 33-35 ባለው ክፍል ላይ ቀጥሎ ምን እንዳደረገ ነው የሚነግረን?________ ካስፈለገም መሰዊያው ፣እንጨቱ፣እና መስዋእቱ ውሃ ተደፍቶባቸዋል ። በመሰዊያው ዙሪያ ያለውም ጉድጓድ ውሃ ተሞልቷል!

12. በቁጥር 36 ላይ ኤልያስ ወደማን ነበር የፀለየው?_________________________

_______________________________________________________________

13. ከቁጥር 36-37 ባለው ክፍል ውስጥ ኤልያስ ወደ እግዚአብሄር ፀለየ?

ሀ. ቁጥር 36 ፡አንተ_______________________________________________

ለ. ቁጥር 36፡ እኔ________________________________________________

ሐ. ቁጥር 37፡ እናም______________________________________________

መ. ቁጥር 37፡ እናም ይህ ህዝብ_______________________________________

ሠ.ቁጥር 37፡ እናም______________________________________________

14. በቁጥር 38 ለኤልያስ ፀሎት የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበር?________________

_______________________________________________________________

15. በቁጥር 39 ላይ የህዝቡስ ምላሽ ምን ነበር?______________________________

_______________________________________________________________

16. ኤልያስ ያዘዘው ምን ነበር ህዝቡስ ምን አደረገ (ቁጥር 40)? ________________

_______________________________________________________________

**ገለፃ**፡ደህና አሁን ነገሮች የሚረጋጉ ይመስላል አይመስላችሁም? እግዚአብሄርን ወይንም በአልን ለመከተል መወሰን አቅቷቻ የነበሩ ሰዎች አሁን በፊታቸው መሬት ላይ ተደፍተው "እግዚአብሄር እርሱ አምላክ ነው" "እግዚአብሄር እርሱ አምላክ ነው" ማለት ይኖርባቸዋል ፡፡ ሰዎቹ ፈርተው የነበረ ይመስላችኋል? ለህይወታቸው ፈርተው ይሆን ? መጽሐፉ ላይ በተፃፈው መሰረት ታሪኩን መመልከት ይኖርብናል፡፡ አምላክ እርሱ ብቻ እንደሆነ የገለፀውን አምላክ በአይናቸው ተመልክተውታል ቀድሞ ሲከተሉት የነበረው ይህን አምላክ ነበር፡፡

እርሱ እግዚአብሄር አምላክ መሆኑን እንዳምን ምን ያስፈልገኛል? ምናልባት አንድ የቅርቤ የሆነ ሰው ታሞ እርሱ ሲፈወስ ልመለከት ይገባ ይሆን? ወይንስ በጣም የምፈልገውን ስራ ፣ለእኔና ለቤተሰቤ የሚያስፈልገኝን ነገር ሲሰጠኝ ያኔ አምላክ መሆኑን አረጋግጥ ይሆን? ወይንስ ልክ ለኤልያስ በቀርሜሊዎስ ተራራ ላይ እንዳደረገው ተአምር ማድረግ ይኖርበት ይሆን? ወይንስ ደግሞ እንደ ኤልያስ በቃሉ ውስጥ እግዚአብሄር "ነኝ" ያለውን አሜን "ነህ" ብዬ መቀበል ነው ያለብኝ? ወይንስ ለመወሰን እንደተቸገሩት ሰዎች እቸገር ይሆን? እርሱ አምላክ እንደሆነ አምን ዘንድ እግዚአብሄር ማድረግ ያለበት ምንድነው? የማስበው እና ምላሼ ሊሆን የሚችለው፡ ____

__________________________________________________

__________________________________________________

## ክፍል 3

**መግቢያ**፡ በመፅሐፈ ነገሥት ክልዕ 2 ላይ ኤልያስ ወደ ሰማይ እንደተወሰደ እናነባለን፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሞትን ሳያይ ወደሰማይ የተወሰደ ሌላው ሰው ሄኖክ ነው፡፡ በዘፍጥረት 5፡21-24 ያለው ክፍል ይህንን እውነት እንደዚህ በማለት ይገልፅልናል "ሔኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም እግዚአብሔር ወስዶታልና፡፡" የኤልያስ የመወሰድ ሁኔታ ግን ከዚህ ለየት ይላል፡፡ አሁን ደግሞ ኤልሳዕ የሚባልን ሌላ ሰው ትተዋወቃላችሁ፡፡ ኤልሳዕ ኤልያስን በአገልግሎቱ የሚያግዘው አገልጋይ ነበር፡፡ በነገሥት ቀዳማዊ 19፡21 ስለ ኤልሳዕ እንደዚህ ተብሎ ተፅፏል "እርሱም ተነሥቶ ኤልያስን ተከትሎ ሄደ፥ ያገለግለውም ነበር፡፡"

**የቤት ስራ፡** *ነገሥት ካልዕ* 2፡1-18

***መልመጃ፡***

1. በቁጥር 1 *መሰረት ምን ሊከሰት ነው*?______________________________
2. ኤልያስ ወደ ዮርዳኖስ ከመሄዱ በፊት የነቢያት ልጆችን (የነቢያቶች ትምህርት ቤት) ሊጎበኝ ወደ ቤተልሔም (ቁጥር 3) እና ወደ እያሪኮ (ቁጥር 5) ሄደ ፡፡ በቁጥር 2፤4 እና 6 ኤልያስ ኤልሳዕን እንዳይከተለው ሲነግረው ኤልሳዕ ያልተስማማው በምንድነው ?______________________________

*ማስታወሻ፡* "የነቢያት ጉባኤ" ወይንም "የነቢያት ልጆች" የሚባለው ስብስብ ምሁራንን እንደዚሁም ከነቢያት ጋር ቅርርብ ያላቸውን ሰዎች ያካተተ ጉባኤ ነው፡፡ ትምህርት ቤታቸውም የሚገኘው በሰሜናዊው የእስራኤል ግዛት ነው፡፡

3. ከኤልያስ መለየቱ እንደከበደው የሚያሳየው የኤልሳዕ ንግግር የትኛው ነው?__

   ______________________________
4. ሃምሳ ነቢያቶች መጥተው ራቅ ብለው ቆሙ፡፡ በቁጥር 8 ላይ ምን ብለው መሰከሩ?______________________________

   ______________________________
5. ወንዙን ካቋረጡ በኋላ ኤልያስ ለኤልሳዕ የነገረው ምንድነው (ቁጥር 9)? __

   ______________________________
6. የኤልሳዕ ምላሽ ምን ነበር?______________________________
7. የኤልያስስ ምላሽ እንዴት ነበር (ቁጥር 10)?______________________________

   ______________________________
8. እነዚህ ሁለት ሰዎች ጥቂት ጊዜን አብረው ካሳለፉ በኋላ በድንገት ምን ተፈጠረ?______________________________

   ______________________________
9. ኤልሳዕም ኤልያስ ሲነጠቅ በማየቱ አሸነፈ፡፡ "አባቴ አባቴ ሆይ፥ የእስራኤል ሰረገላና ፈረሰኞች፥ ብሎ ጮኸ፡፡" ሰረገላዎችም ኤልያስን ወሰዱት ፡፡

አስተማሪው፣ጓደኛው፣ እና የአገልግሎት አጋሩ ተወሰደ፡፡ ኤልያስ ምን አደረገ?____________________________________________

10. በቁጥር 13-14 ባለው ክፍል ምን ተፈጠረ?____________________________

    ____________________________________________________________

11. ሲመለከቱ የነበሩት የነቢያት ልጆች ምን ብለው ደመደሙ (ቁጥር 15) _______

    ____________________________________________________________

**ገለፃ፡** ይህ ክስተት በየእለቱ የሚከናወን አልነበረም ይህንን ትእይንት ከተመለከቱት ሰዎች አእምሮም በቶሎ አይጠፋም፡፡ ኤልያስ የዮርዳኖስን ወንዝ በመጎናፀፊያው መታው ወንዙም ተከፈለ ሁለቱም በደረቅ መሬት ተሻገሩ፡፡ ኤልሳዕ ሌላው ያወቀው ነገር ኤልያስ በእሳት ፈረሶች እና ሰረገላ ከእርሱ እንደሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ በኂላ ዳግመኛ ኤልያስን አላየውም፡፡

ኤልሳዕ ከኤልያስ የጠየቀው በእርሱ ላይ ከነበረው እጥፍ መንፈስ እንዲሆንለት ነው፤ ነገር ግን ይህንን ጥያቄ መመለስ የሚችለው እግዚአብሄር ብቻ ነው፡፡ በእርግጥ ኤልሳዕ ከባድ ጥያቄ ነው የጠየቀው የኤልያስን ስፍራ ነበር የፈለገው፡፡ ዛሬ ላይ እኛም ልንጠይቅ የሚገባን እንደ ኤልያስ አይነት የተሳካ አገልግሎት ለማገልገል መሆን ነው ያለበት፡፡ ነገር ግን ኤልያስ ሲነጠቅ ቢያየው ይህ እንደሚሆንለት ለኤልሳዕ ተስፋ ሰጥቶታል፡፡ ኤልሳዕም የኤልያስን መጎናፀፊያ ወስዶ ወንዙን ሲመታው ውሃው ለሁለት ተከፈለ፡፡ በዚህን ጊዜ ይመለከቱ የነበሩት የነቢያት ልጆች መጥተው በፊቱ ተደፉ የኤልያስም መንፈስ እንዳገኘው መሰከሩ፡፡ መሪነት እና ኃላፊነቱ ወደ ኤልሳዕ ተሸጋገረ፡፡

**ትግበራ፡** እነዚህ ሁለት ነቢያቶች ከመለያየታቸው በፊት የተነጋገሩት ንግግር ጠቃሚ የሆነ ንግግር ነው፡፡ ኤልያስም "ከአንተ ሳልወሰድ አደርግልህ ዘንድ የምትሻውን ለምን አለው፡፡" ኤልያስም ከኤልሳዕ ሊለይ ጥቂት ጊዜ እንደቀረው አውቆ ለኤልሳዕ ሊያደርግለት የሚገባውን ለማድረግ ሲጥር እንመለከታልን፡፡ አሁን እየተነጋገሩ ያሉት ሁለቱ ሰዎች ናቸው፡፡ ኤልያስ የኤልሳዕ ምላሽ ምን ሊሆን ይችላል ብሎ ይጠብቅ ይሆን?

ኤልሳዕ “መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ አለ፡፡” ኤልሳዕ የጠየቀውን ጥያቄ ሊመልስለት የሚችለው እግዚአብሄር ብቻ ነው፡፡ የጠየቃቸው ጥያቄዎች እግዚአብሄር ብቻ ሊመልሳቸው የሚችሉ ናቸው፡፡

ከምትወዷቸው ሰዎች የተለያችሁበትን ወቅት አስቡ፡፡ ስትለዩዋቸው ምን ጠየቃችኋቸው? እናንተስ እንደ ኤልያስ “ምን እንዳደርግልህ ትወዳለህ ብላችሁ ታውቃላችሁ?” የበረከት ቃል፣የማበረታቻ ቃል? በእንደዚህ አይነት ቀኖች ምን ማለት ይኖርባችኋል?________________________________________________

ምናልባት ሰዎች ከእናንተ ሲለዩ የሚሰማችሁ ስሜት እንደ ኤልሳዕ ሊሆን ይችላል፡፡ እናንተስ “መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ” ብላችሁ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? እንደዚህ ብላችሁ ጠይቃችሁ የምታውቁ ከሆነ ምን አይነት ምላሽ እንደምታገኙ አስባችኋል?______________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ፀሎት፡** እግዚአብሄር ሆይ በሁሉ ነገር ባርከኸናል፡፡ ከላይ ከሰማይ በሆነው በረከት ባለጠጋ አድርገኸናል፣ መንፈስህን አፍስሰህልናል፡፡ እኛም ያለንን ነገር ያለስስት ማካፈል ይሆንልን ዘንድ በዚህ መንፈስ ባርከን፡፡ በረከትህ ሌሎችን ለሰጠሃቸው ሃላፊነት እንደዚሁም ስራ የሚያበረታ እና የሚያፀናቸው ለሌሎችም በረከት መሆን የሚችሉበትን ሃይል ያስታጥቃቸው ዘንድ በመንፈስህም አማካኝነት ለሌሎች በረከት መሆን የሚችሉበትን ፀጋ እርሱም እጥፍ በረከታችን በሆነው በልጅህ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰጠኸንን የዘላለም ህይወት እውነት ለሌሎች ማካፈል ይሆንልን ዘንድ እርዳን፡፡

<u>**ክፍል 4**</u>

***መግቢያ፡*** ቀጣዩ ታሪክ ደግሞ እግዚአብሄር ለእርሷ እና ለልጇ መልካም ስለአደረገላት አንዲት ሴት ይሆናል፡፡ በዘዳግም 14፡29 ባለው የሙሴ ህግ ላይ አስራት እና የተለያዩ ስጦታዎች ለመበለቶች እና ለወላጅ አልባዎች ጠግበው እንዲያድሩ ለእነርሱ እንዲሆን

ያዛል። ይህንን ቃል በመታዘዝ ከሰጡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር የእጆቻቸውን ስራ ሁሉ እንደሚባርክ ቃል ገብቷል።

**የቤት ስራ፡** *ነገሥት ካልዕ* 4፡1-7 *ያለውን* ክፍል አንብቡ ።

- ሴቲቱ ማናት ?
- ችግሩ ምን ነበር?
- እግዚአብሄር ለእርሷ እና ለሁለቱ ልጆቿ ምን አደረገላቸው?

**መልመጃ:**

1. እሰቲ ታሪኩን በራሳችሁ ቃል ፃፉት :________________________________

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

2. ሁኔታው ለሴቲቱ ከአቅሟ በላይ ነበር። በቁጥር 2 ላይ ኤልሳዕ ምን ብሎ ጠየቃት?

   ሀ. ________________________________________________________

   ለ. ________________________________________________________

**ትግበራ፡**

1. እዳዋን በሙሉ መክፈል ትችል ዘንድ እግዚአብሄር በቤቷ የነበረውን ጥቂት ዘይት ባረከላት ለባለ እዳውም ከፈለችው። እናንተስ ከዚህ ታሪክ ለህይወታችሁ የሚሆን ትምህርት ፈልጉ______________________________________________

   ___________________________________________________________________

2. በእናንተ ህይወት ውስጥ እግዚአብሄር አብዝቶ አትረፍርፎት ለሌሎች በረከት ሊያደርገው የሚችለው ትንሽ ነገር ይኖር ይሆን?____________________________

   ___________________________________________________________________

**የቤት ስራ፡** *ነገሥት ካልዕ* 4፡8-17 *ያለውን* ክፍል አንብቡ።

**መልመጃ:**

1. ሱነማዊቷ ሴት እና ባሏ ለኤልሳ ያደረጉለት ውለታ ምን ነበር (ቁጥር 8-10)?

_______________________________________________

2. ኤልሳዕ ወደ ሱነማዊቷም ሲመጣ ሊያመሰግናቸው ፈለገ፡፡ አገልጋዩን ጊያዝን ሰነማዊቷን ሴት እንዲጠራት ነገሮት ምን አቀረበላት(ቁጥር 13)? __________

_______________________________________________

3. ምላሿ ምን ነበር?_______________________________________

4. ኤልሳዕ አሁንም አልረካም፤ ጊያዝን ጠርቶ ምን ሊደረግላት እንደሚገባ ጠየቀው (ቁጥር 14)፡፡ ምላሹ ምን ነበር?_______________________________

5. ኤልሳዕ ለሱነማዊቷ ሴት ምን ነገራት (ቁርጥ 16)?)____________________

6. እንደሚታወቀው ይህቺ ሴት ልጅ ለመውለድ ያደረገችው ትግል ተስፋ አስቆራጭ ሆኖባታል በዚህ ጉዳይ ላይ ተስፋዋ ተሟጧል፡፡ ነገር ግን በቁጥር 17 መሰረት ትንቢቱ እውን ሆነ፡_______________________________

_______________________________________________

**የቤት ስራ፡** ከቁጥር 18-37 ያለውን ክፍል አንብቡት፡፡ ታሪኩ አሁንም ይቀጥላል፡፡

1. በድንገት ልጁ ታመመ፡፡ ሰራተኛው ልጁን ተሸክሞ ወደ እናቱ ይዞት መጣ በቁጥር 18-20 ላይ ሞተ፡፡ እናትየው ምን ነበር ያደረገችው (ቁጥር 21-25)?_______________________________________

_______________________________________________

2. ለባሏ ሁሉ ነገር ሰላም እንደሆነ ነገረችው፡፡ ለግያዝም እንደዚሁ ፡፡ ነገር ግን ለኤልሳ ምን አለችው (ቁጥር 28)? ______________________________

_______________________________________________

3. ግያዝን ኤልሳዕ ምን አዘዘው (ቁጥር 29)? ____________________

4. ሴቲቱ ከኤልሳዕ ለመለየት እንቢ አለች ኤልሳዕም ተከትሏት ሄደ፡፡ በመንገዳቸው ላይ ግያዝ አገኛቸው፡፡ ምን ነገራቸው (ቁጥር 31)?

5. እቤት ሲደርስ ኤልሳዕ ምን አደረገ (ቁጥር 32-35)?

6. የሞተው ልጅ እንደገና ነፍስ ዘራ፡፡ ከቁጥር 36 እስከ 37 ባለው ክፍል ውስጥ ልጁን ለእናቱ መልሶ ሰጣት፡፡ በወቅቱ ምንም አልተናገረችም ገብታም_______ በ____________ልጅዋንም _________ ወጣች፡፡

**ትምህርት:** በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በዚህ ወቅት እግዚአብሄር በነቢያቶች ለመናገር መምረጡ የሚገርም ነው፡፡ ለንጉስ ዳዊት በነቢዩ ናታን ተናገረው ቀጥሎ ለነገሡት ነገሥታት ቁጥራቸው እጅግ በበዛ ነቢያት ተናገራቸው፤ ህዝቡን ደግሞ ኤልያስንና ኤልሳዕን በመሰሉ ነቢያት ተናገረ፡፡ የእግዚአብሄርን ቃል መታዘዝ እና እርሱን ማምለክ ለሚፈልጉ ሰዎች ነቢያቶች በእርግጥ የህዝቡ ተስፋዎች ነበሩ፡፡

በነገሥት ካልዕ ውስጥ ሆነን ለዚህች ሴት እና ለባሏ የበዛውን የእግዚአብሄርን ምህረት ተመለከትን፡፡ በዚሁ ክፍል በነቢዩ ኤልሳዕ በኩል እርዳታዋ ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደሆነላት ያወቀችን ሴት እናገኛለን፡፡ ጥቂት ሄደን ደግሞ በእግዚአብሄር የማዳን ስራ ከሞት ወደ ህይወት የመጣውን ብላቴና እናገኛለን፡፡ የእስራኤል እና የይሁዳ ነገስታት በእግዚአብሄር ላይ ፊታቸውን ባዞሩበት ዘመን ውስጥ እግዚአብሄር ለዚህ ቤተሰብ ፍቅሩን እና ርህራሄውን ገለፀ፡፡ ምህረቱ አዳናቸው፤ ታደጋቸውም፡፡

በአንድ መልኩ ይህ ታሪክ የእስራኤል ታሪክ ነው፡፡ እግዚአብሄር ወደ እነርሱ መጣ እነርሱም እንደ ነፃ አውጪያቸው ተቀበሉት፡፡ የልባቸውንም መሻት የሆነውን ወደ ተስፋይቱ ምድር የመግባታቸውን ተስፋን ሰጣቸው፡፡ ከብዙ አመትም በኋላ ተስፋቸውን ፈፅሞ በአምላካቸው ጥበቃ ወደሚኖሩባት  ወደ ተስፋይቱ ምድር አስገባቸው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሄርን ትተው በዙሪያቸው እንዳሉት አህዛብ በንጉሥ መመራት ፈለጉ ስለዚህም ሞት እና ውድቀት በመካከላቸው ገባ፡፡ እነዚህም ነገሥታት ደግሞ ይብሱኑ ከእርሱ እያራቋቸው ሄዱ፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሄር ህዝቡን ከፊቱ አስወገዳቸው፡፡ ህግና ነቢያትም ወደ እግዚአብሄር ሊመልሷቸው እንደዚሁም ህይወት ሊሰጧቸው አልቻሉም፡፡ ህጉ ከፍርድ ውጪ ምንም አላስገኘላቸውም፡፡ በነቢያቱም ፍርድ እና ሞት እንጂ ህይወት ሊሆንላቸው አልቻለም፡፡ በመጨረሻም ልክ ነቢዩ በብላቴናው ላይ አይኑን በአይኑ ፣አፉን በአፉ፣እጁን በእሙጁ አካሉን በብላቴናው ላይ በመዘርጋት ህይወት

እንዲያገኝ እንዳደረገው በፍጥረት ጅማሬ የህይወትን እስትንፋስ በአፍንጫው እፍ በማለት ለሰው ህይወትን የሰጠው አምላክ እግዚአብሄር በሰው ምሳሌ ወደ ዓለም በላከው በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ መከራ፣ ሞትና ትንሳኤ ህይወትን ሰጠን፡፡

2 ቆርንቶስ 5፡21 እግዚአብሄር ያደረገውን በትክክል ይነግረናል፡፡ “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው፡፡” የእግዚአብሄር ልጅ እየሱስ ኃጢአትን የለበትም እርሱ ፃድቅ ነበረ፡፡ ከእግዚአብሄር ጋር ሊያስታርቀን የሚችል እርሱ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ እኛን መስሎ በዚህ ምድር ተመላለሰ፡፡ ወደ ኃጢአተኛው ዓለም መጣ፡፡ የእኛንም ኃጢአት በሙሉ ተሸከመ ፡፡ እርሱ በሰራው ስራ ምክንያት በእርሱ ስራ በማመናችን በእግዚአብሄር ፊት ፃድቅ ሆንን፤ ከእርሱ ጋር ህይወትን ሰጠን፡፡ ይህ ቁጥር (ጥቅስ) በካርዳችሁ ላይ ልትፅፉት የሚገባ ቁጥር ነው፡፡

**ማሰላሰል፡** መዝሙር 130 ይሁዳ እና እየሩሳሌም በክፉ መንገዳቸው በመፅናታቸው ምክንያት ወደ እግዚአብሄር የቀረበ የልብ ጩኸት ይመስላል፡፡ ልባቸውን ከእግዚአብሄር ያልመለሱ ከእርሱ ጋር ተስማምተው መኖር የሚፈልጉ ሰዎች የልብ ጩኸት በዚህ መዝሙር ውስጥ ይሰማችኋል ፡፡ የሰራፕታዋ ሴት እንደዚሁም የሱነማዊቷ ሴት ለቅሶ ይሰማችኋል? “አቤቱ፥ አንተን ከጥልቅ ጠራሁህ፡፡አቤቱ፥ ድምፄን ስማ ጆሮህ የልመናዬን ቃል የሚያደምጥ ይሁን፡፡ ……ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና፡፡”

ይህ ጩኸት ምናልባት የእናንተ ጩኸት ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባት እናንተም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ወዴት መመለስ፣ እንዴት መመለስ እንዲሁም እንዴት የእግዚአብሄርን ምህረት እና ይቅርታውን መቀበል እንዳለባችሁ ግራ ገብቷችሁ ይሆናል፡፡ ምናልባት ህይወታችሁ መዋጀት እና ከኃጢአታችሁ መዳን ያስፈልጋት ይሆናል፡፡ እግዚአብሄርን ጠብቁት ተስፋችሁንም በቃሉ ላይ አድርጉ እግዚአብሄር አሁኑኑ እንድትመለሱ እየጠበቃችሁ ነው፡፡ ምንም ሳታቅማሙ በእግዚአብሄር ፊት ንሰሃ ግቡ፡፡ እግዚአብሄር መሃሪ ፣ ቤዛችሁ እና ደህንነታችሁ ነው፡፡

**ፀሎት፡** አ! አምላኬ ሆይ ከጥልቅ ጠራሁህ ፡፡ ነፍሴ የአንተን ፍቅር እና ይቅርታ ተጠምታለች፡፡ እንድትምረኝ ወደአንተ እጮሃለሁ እባክህ ታደገኝ፡፡ ከተያዝኩበት የኃጢአት አዘቅትና ረግረግ ነፃ አውጣኝ፡፡ ኃጢአቶቼ በፊትህ የተገለጡ ናቸው፡፡ አዳኜ፣አለቴ እና ደህንነቴ በሆነው ስለ ልጅህ ስለ ኢየሱስ ክረስቶስ ስትል ከተያስኩበት ባርነት ነፃ አውጣኝ፡፡ ከኃጢአት አዘፅቅት ውስጥ ነጥቀህ አውጣኝ ፣ቅዱስ በሆነው ደምህና ፅድቅህ አጥበህ አንፃኝ፣ለክብርህም እንደገና የምስጋናን መዝሙር እዘምርልህ ዘንድ አስችለኝ፡፡ የሴቲቱ ልጅ እንደሞተ አንተም እንደገና ህይወትን እንደሰጠኸው ቅዱስ የሆነውን ስምህን አመሰግን ዘንድ ለእኔም የትንሳኤን ህይወት ስጠኝ፡፡ ____________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## <u>ክፍል 5</u>

**ትምህርት፤-** ከሆነው ነገር የተነሳ እግዚአብሄር ምናልባት ህዝቡን የተወ ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ የጠራቸው፣ ልጆቹ ይሆኑ ዘንድ የመረጣቸው የእርሱን መልክ ማንፀባረቅ አልቻሉም ይልቁንም የዋናውን ጠላት የክፉውን ማንነት እና ባህሪይ ማንፀባረቅ ጀመሩ፡፡ በእግዚአብሄር ላይ እጅግ ዘግናኝ እና ከባድ ኃጢአትን አደረጉ ክፋትንም ፣ስንፍናንም አደረጉ፡፡ ከእንጨት እና ከድንጋይ ለተሰሩ አማልክቶች ለበአል እና ለሌሎች ጣኦታት ሰገዱ፡፡ እግዚአብሄርም ከእንደዚህ አይነት አመፀኛ እና የማይታዘዝ ህዝብ ጋር ህብረት ማድረግን አልወደደም፡፡ ከመጣው ጋር ለሚነጉዱት ለእነዚህ ህዝቦች እግዚአብሄር ጀርባውን የሰጣቸው መሰለ፡፡ እንደ ጥበበኛ ሳይሆን ስራቸው ሁሉ የሞኝነት ሆነ፡፡ ከሁሉ አብልጠው እግዚአብሄርን መውደድ እና በእርሱ መታመን አልፈለጉም፡፡ በፍፁም ልባቸው ፣ነፍሳቸው፣እና ኃይላቸው እርሱን አልወደዱም፡፡ እግዚአብሄር አምላካቸውን በአደባባይ ከተዉት እርሱስ ከእነርሱ ጋር ምን ይሰራል? ከዚህ የተለየ ነገር ያደርጋል ብላችሁ ታስባላችሁ?እስቲ እግዚአብሄር ምን እንዲያደርግ ትጠብቃላችሁ?___________________________________________

________________________________________________________________

ከባድ ፍቅር እያለን አንዳንድ ጊዜ ከምንወዳቸው እንድንለይ ልንገደድ እንችላለን ። ይህን አይነት ፍቅር የተለየናቸውና የምንወዳቸው ሰዎች በኃጢአት ረግረግ እና አረንቋ ውስጥ እንዲዳክሩ  እስከመፍቀድ ሊያስጨክነን ይችላል። የማይታዘዝ ልጃቸውን ወደመታዘዝ ሊያመጡ የሚታገሉ እናትና አባት አመፀኛ ልጃቸውን ለመመለስ ሲሞክሩ በአመፁ ፀንቶ የራሱን መንገድ ለመከተል ጥሏቸው ሲሄድ ከማየት የበለጠ የሚያሳዝን ትእይንት የለም።

**<u>ክፍል 6</u>**

***መግቢያ*:** *የምናጠናው የመጨረሻ ታሪክ ከለምፁ ለመፈወስ ፈልጎ ወደ ነቢዩ ኤልሳዕ ስለመጣው ንዕማን ስለሚባለው ሰው ነው።*

**የቤት ስራ፡** *ነገሥት ካልዕ* 5:1-19

- *ንዕማን ማነው?*
- እስራኤላዊቱ ብላቴና ለጌቶቿ ምን ነበር የነገረቻቸው ?
- ኤልሳዕ ለንዕማን የሰጠው ትዕዛዛ ምን ነበር?
- *የንዕማን ምላሽ ምን ነበር?*
- *ታሪኩስ የተፈፀመው እንዴት ነበር?*

***መልመጃ*:**

1. ስለ *ንዕማን የተነገረን ምንድነው ቁጥር* 1? ______________________________

   ______________________________________________________________

   ሶርያ በካርታችሁ ላይ ትገኛለች። ከእስራኤል በስተ ሰሜን ባለው ክፍልም ትገኛለች። ደማስቆም የሶርያ አንድ ከተማ ነች፤ በአሁኑ ጊዜ የሶርያ ዋና ከተማ ሆናለች።
2. አንዲት እስራኤላዊት ብላቴና ከሶርያ በተነሱ አደጋ ጣዮች ተማርካ የሶርያውን የጦር አዛዥ የንእማንን ሚስት ታገለግል ነበር። ይህች ብላቴና ለእመቤቷ ምን ነገረ ነገረቻት (ቁጥር 3-4 )? ______________________________
3. ንእማንም ወደ ንጉሱ ሄደ። ብላቴናይቱ የነገረችውን ለንጉሱ ነገረው ወደ እስራኤልም እንዲሄድ ፈቃድ ጠየቀው። የንጉሱ ምላሽ ምን ነበር ምንስ አደረገለት? __________

   ______________________________________________________________

4. ንእማንም ሥጦታ እና ደብዳቤ ይዞ ተጓዘ። የደብዳቤው መልዕክት ምን የሚል ነበር ቁጥር 6)?______________________________________

____________________________________________________

5. ለሶርያው ንጉስ ደብዳቤ የእስራኤሉ ንጉስ ምላሽ ምን ነበር (ቀጥር 7)? _________

____________________________________________________

6. ንጉሱ ያደረገውን ሲሰማ ኤልሳዕ ወደ ንጉሱ ምን የሚል መልዕክት ነው የላከው? _

____________________________________________________

7. ንእማን ከተከታዮቹ ጋር ወደ ኤልሳዕ ቤት ደረሰ ያናገረውም በመልዕክተኛ ነበር። ንእማንን ምን እንዲያደርግ ተነገረው (ቁጥር 10)? ____________________

____________________________________________________

8. ኤልሳዕ አድርግ ያለውን ከማድረግ ይልቅ ንእማን ተቀቆጣ ። ንእማን ምን እንዲደረግለት ነበር የጠበቀው (ቁጥር 11-12)? ____________________________
9. እስቲ በራሳችሁ አገላለፅ ንእማን የተናገረውን ግለፁት? ____________________

____________________________________________________

____________________________________________________

የንጉስ ሰራዊት አዛዥ ነው። አሁንም እንደለመደው እንዴት መፈወስ እንዳለበትም ትእዛዝ ሊሰጥ ፈለገ። ንእማንም እንዲህ አለ " እነሆ፥ ወደ እኔ የሚመጣ፥ ቆሞም የአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ፥ የለምጹንም ስፍራ በእጁ ዳስሶ የሚፈውሰኝ መስሎኝ ነበር።" ንእማን ማድረግ የሚገባው እንደተነገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ሰባት ጊዜ መታጠብ ብቻ እንደሆነ ተረዳ።

10. ንእማን በቁጥር 12 ላይ ምን ጠየቀ?

ሀ. ______________________________________________

ለ. ______________________________________________

እንደዚህ ነበር ያለው "የደማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእስራኤል ውኆች ሁሉ አይሻሉምን? በእነርሱስ ውስጥ መታጠብና መንጻት አይቻለኝም ኖሮአልን?" በቁጥር 13-14 ምን ሆነ? ________________________________________

____________________________________________________

11. ንእማንም ወደ ነቢዩ ቤት ተመለሰ። ለኤልሳእ ምን አቀረበለት? _______________

____________________________________________________

12. በቁጥር 15 ላይ ለኤልሳዕ ስጦታ አቀረበለት ነቢዩ ግን ስጦታውን አልቀበልም አለ ቁጥር 16፡፡ ንእማን ወደቤት ሲመለስ ያሳሰበው ነገር ነበር፡፡ ይህንን በተመለከት ለኤልሳዕ ምን ነበር ያለው (ቁጥር 18)? ________________________________

________________________________________________________________

13. ኤልሳዕ የተናገው ቃል ምን ነበር? ____________________________________

**ትግበራ**:

1. እስቲ እናንተም ለእግዚአብሄር ነገሮችን እንዴት ማድረግ እንዳለበት ልትመሩት የሞከራችሁበትን ጊዜ አስታውሱ: ________________________________________

   ________________________________________________________________

2. እግዚአብሄርን አንድ ነገር በፀሎት ከጠየቃችሁት በኂላ መልሱ ምን ሊሆን እንደሚገባው በልባችሁ አስቀድማችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ ? ___________________________

   ________________________________________________________________

**ትምህረት**: ንእማን ወደ ኤልሳዕ ሲመጣ ፈውሱ በምን አይነት መልኩ መከናወን እንዳለበት በልቡ አስቦ ነው የመጣው፡፡ ይህ ደግሞ አስገራሚ ነገር ነው፡፡ ነቢዩ እጁን በበሽታው ላይ ቢጭንለት መልካም እንደሆነ አስቦ ነው የመጣው፡፡ ነገር ግን የኤልሳዕ ትእዛዝ  ደግሞ ያልተጠበቀ ሆነበት፡ በአጭሩ እንደዚህ የሚል ነው፡፡ "ሄደህ በወንዙ ውስጥ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በል!" የሚል ነበር :የተሰጠው መመሪያ ቆሻሻ ሆነበት፡፡ ይህ የቆዳ በሽታ ሊገድል የሚችል በሽታ ነው፡፡ ንእማን ደግሞ ህመምተኛ እንደሆነ እንጂ እራሱን እንደ ቆሻሻ ቆጥሮ አያውቅም፡፡ በዙሪያው የነበሩ አገልጋዮቹም አስቀድሞ በአእምሮ ውስጥ ይዞት ነበረውን ሃሳብ በመተው ነቢዩ የነገረውን እንዲታዘዝ ያበረታቱት ነበር፡፡ "በቆሸሸው የዮርዳኖስ ውሃ ታጠበህ ንፃ ይሉት!" ነበር፡፡

ንእማን ከቆዳው ህመም ይልቅ ትኩረት የሚፈልግ ነገር ነበረው፡፡ ከእግዚአብሄር ጋር የግንኙነት ችግር ነበረበት፤ የኃጢአት ችግር ነበረበት፡፡ ለለምፁ መድሃኒቱ እንደታዘዘው በውሃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ማለት ነበረበት፡፡ ለኃጢአቱ መድኃኒት የሚሆነው ደግሞ ከእግዚአብሄር ጋር መስማማት ነበር፡፡ ከለምጹ ለመንፃት ወደ ውሃው ሲሄድ በአእምሮአችን እንሳል፡፡ የሚገርመው ግን ውሃ ውስጥ ሲጠልቅ ከእግዚአብሄር ሌላ አምላክ እንደሌለ እንዲረዳ ውስጣዊ የሆነ ፈውስ በህይወቱ ተከናውኗል፡፡ እኛም ያመንን ሁላችን እንደዚሁ ነው የሆነልን፡፡ በክርስቶስ በማመናችን

ምክንያት በደሙ የሆነ ስረየትን አገኘን በጥምቀትም የእግዚአብሄርን ፀጋ ተቀበልን ። ከእግዚአብሄር ከለየንም የኃጢአት በሽታ ተፈወስን። በስጋ ደዌ የታመሙ ሰዎች ዋናው ችግር ከበሽታው አደገኛነት የተነሳ ከሰው ተለይተው እንዲቀመጡ መደረጋቸው ነበር።እኛንም በተመሳሳይ መልኩ ኃጢአታችን ከሰማያዊው አባታችን ለይቶን ብቻችንን አስቀርቶን ነበር። ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ይቅርታን አግኝተን ነፅተናል። በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሄር ጋር ህያው የሆነ ግንኙነት አለን።

**ፀሎት**: እግዚአብሄር ምልካም ነው ስለዚህም አመስግኑት……____________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ከለሳ

# ደህንነታችን የሆነው

# የእግዚአብሄር ምህረት

**ክለሳ**

*"ደህንነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ምህረት"* የሚለውን የጥናት ክፍል ስለ አጠናቀቃችሁ እንኳን ደስ አላችሁ! በዚህ ጥናት ከብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እና ሰዎች ጋር ተዋውቃችኂል አሁን የክለሳ ጊዜ ነው፡፡ ይህ ክለሳ በጥናቱ ውስጥ ምን ያህል መሻሻል በህይወታችሁ እንደሆነ እንድትገነዘቡ ትምህርቱም ምን ያህል ውስጣችሁ እንደቀረ እንድትረዱ ታስበው የተዘጋጁ ጥያቄዎች እንጂ ፈተና እንዳልሆነ አስታውሱ፡፡ እነዚህን ታሪኮች ስታጠኑ የታሪኩን እውነታ እንደዚሁም ስለ እግዚአብሄር እና ስለሰው ልጆች ያለውን እውነት መረዳት እና ማወቅ ትችላላችሁ፡፡ እናንተም በ 21ኛው ክፍለ ዘመን እንደመኖራችሁ እነዚህን እውነታዎች እንዴት በህይወታችሁ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባችሁ ትገነዘባላችሁ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**:

1. እግዚአብሄር እንደልቤ የሆነልኝ ያለው ሰው ማነው? __________ የሐሥ 13:22.
2. የዳዊት እና የጎልያድ ታሪክ የተፃፈው የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ነው?________________________________________________
3. ሳኦል ከዳዊት ጋር የነበረውን ግንኙነት ግለፁ: ______________________________

   ________________________________________________
4. ዳዊት ለሳኦል ያለውን ስፍራ ግለፁ: ______________________________

   ሳሙኤል ካልዕ 26፡9-11 ያለውን ክፍል ተመልከቱ፡፡
5. ዳዊት የእግዚአብሄርን ቤተመቅደስ ለመስራት ጥያቄ ቢያቀርብም እግዚአብሄር ጥያቄውን ውድቅ አድርጎበታል፡፡ ይህንን በተመለከተ እግዚአብሄር የሰጠው ተስፋ ምን ነበር? ሳሙኤል ካልዕ 7፡12-13 ተመልከቱ______________________________

   ________________________________________________
6. የዳዊት እና የቤርሳቤህ ታሪክ የሚገኘው በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው?

   ________________________________________________
7. የዳዊት ኃጢአት ያስከተሏቸው ሶስት መዘዞች ምንድናቸው?

ሀ. ሳሙኤል ካልዕ 12:10 ______________________________________________

ለ. ሳሙኤል ካልዕ 12:11-12 ____________________________________________

ሐ. ሳሙኤል ካልዕ 12:14 ______________________________________________

8. የአቤሴሎምን ታሪክ ግልፅ የሆነ ማጠቃለያ ፃፉ (ሳሙኤል ካልዕ 13:20-18:33): _
________________________________________________________________
________________________________________________________________

9. ንጉስ ሰለሞን እግዚአብሄርን ምን ጠየቀው (ነገሥት ቀዳማዊ 3:9)? ___________
________________________________________________________________

10. የሁለቱ ጋለሞቶች ታሪክ በየትኛው ክፍል ውስጥ ይገኛል? __________________

11. ሰሎሞን ያቀረባቸው ሁለት የህንፃ ውጥኖች ምንድናቸው?

    ሀ. ነገሥት ቀዳማዊ 6 ___________________________________________

    ለ. ነገሥት ቀዳማዊ 7 ___________________________________________

12. የሰሎምን መንግስት ምንን አስገኘ (ነገሥት ቀዳማዊ 11:1-13)? ______________
________________________________________________________________

13. በንጉስ አክአብ ዘመን የነበረው የእግዚአብሄር ነቢይ ማነው (ነገሥት ቀዳማዊ 17:1)? ___________________________________________________________

14. የሰራፕታዋን ሴት ታሪክ ማጠቃለያ ፃፉ(ነገሥት ቀዳማዊ 17:7-24): __________
________________________________________________________________
________________________________________________________________

15. ኤልያስ እና የበአል ነቢያት ያደረጉትን ውርርድ ግለፁ (ነገሥት ቀዳማዊ 18:16-40):_______________________________________________________________
________________________________________________________________

16. ኤልያስን የተካው ነቢይ ማን ይባልላ (ነገሥት ክልዕ 2:1-12): ________________

17. የኤልሳዕን አገልግሎት በተመለከተ የማይረሱት ሁለት ታሪኮች የትኞቹ ናቸው?

    ሀ.ነገሥት ካልዕ 4:1-7 ___________________________________________

    ለ.ነገሥት ካልዕ 5 _______________________________________________

18. የእግዚአብሄር ቁጣ ምን አስከተለ መፅሐፈ ነገሥት ካልዕ 24:20?

_______________________________________________

_______________________________________________

19. የባቢሎን ንጉስ ማን ይባላል (ነገሥት ካልዕ 25:1)? ____________________

20. ከእነዚህ የነገስታት ታሪኮች ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ምህረት ምን ተማራችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

***የመወያያ ጥያቄዎች***: አንድ ሰው የእግዚአብሄር ምህረት በህይወታችሁ ላይ ስላመጣው ለውጥ ቢጠይቃችሁ በምን አይነት ሁኔታ ትመልሱለታላችሁ ____________________

_______________________________________________

_______________________________________________

***ፀሎት***: ጌታ ሆይ ምህረትህ በህይወቴ እንደበዛ ሳስብ በፊትህ በፍርሃት እቆማለሁ፡፡ምህረትህ ህይወት እና ደህንነትን ሰጥቶኛል፡፡ ምህረትህ ለእኔ የማይገባኝን ታላቁን ፍቅርህን ያሳየኛል፡፡ በልጅህ በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ስላደረክልኝ ምህረት እርሱ ኃጢአት ሳይኖርበት እለእኔ ኃጢአት ስለሆነ በእኔ ፈንታ ስለሞተ በእርሱ ሞት እኔ ህይወትን ስለአገኘሁ አመሰግንሃለሁ፡፡ በህይወቴ ስለበዛው ፀጋህና ምህረትህ አመሰግንሃለሁ ቅዱስ የሆንውን ስምህን አወድሰዋለው፡፡____________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________